“ሀረር በቄሮዎች እየተመራች ነው”
ገጽ 3

## አቡበከር አህመድ ም/ ኮሚሽነር ሆኑ

ገጽ 4

ህገ መንግስቱ በኢህአዴግ አመራር አባላት መካከል ልዩነት አስነስቷል
ገጽ 9

## “ዓላማችን ማህበራዊ ፍትህ ነው”

የሺዋስ አሰፋ
ኢዜማ ፓርቲ
ገጽ 12




# ኢትዮጲስ

1ኛ ዓመት | ቁጥር 035 ግንቦት 11 ቀን 2011 ዓ.ም ዋጋ ብር 9.90


# “ጠ/ሚ/ር ዐቢይን ይቅርታ እናደርግላቸዋለን”



## ዶክተር ገመቺስ ማሞ የኢትዮጵያ ህክምና ማህበር ፕሬዝዳንት

## የህክምና ባለሙያዎች የስራ ማቆም አድማ አደረጉ

ገጽ 2




የህክምና ባለሙያዎች
ድምፃቸውን ሲያሰሙ

# የህክምና ባለሙያዎች በአዲስ አበባ፣ በአሰላና በጅማ የስራ ማቆም አድማ አደረጉ

## አድመኞቹ ፣ በፅኑ ህሙማን (ICU) በማዋለጃ ክፍል (labor ward) በድንገተኛ ክፍል (EOPD) የሚሰጡትን አገልግሎት እንደማያቋርጡ ገልፀዋል

## "ጠ/ሚ/ሩን በሙሉ ልብ ይቅርታ እናደርግላቸዋለን" ዶክተር ገመቺስ ማሞ

## የጤና ባለሙያዎች ሥራ ማቆም ህጋዊነት ጥያቄ አስነስቷል

### የስራ ማቆም ውሳኔው

ከጥቂት ሳምንታት በፊት "መብታችን አልተከበረም" በማለት እንቅስቃሴ የጀመሩት የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ድህረ ምረቃ (residency) ተማሪዎች ከግንቦት 7 2011 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ጀምሮ የስራ ማቆም አድማ አድርገዋል:: እጩ ዶክተሮቹ እርምጃውን ለመውሰድ ያስገደዳቸውን ሁኔታ አስመልክተው ባወጡት መግለጫ፣ "...መንግስት ጥያቄዎቻችን ለመመለስ ዝግጁ አለመሆኑን ተረድተናል:: በዚህም ምክንያት፣ ዛሬ ግንቦት 06 ቀን 2011 ዓ.ም ሁላችንም ተገናኝተን በካሄድነው ውይይት ላይ፣ ሰላማዊ ጥያቄወቻችን ተገቢው ትኩረት ተሰጢቷቸው እንዲመለሱልን እያሳሰብን፣ ከግንቦት 07 ቀን 2011 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡00 ጀምሮ ጥያቄዎቻችን እስከሚመለሱበት ዕለት ድረስ በስራ ቦታ ላይ ላለመገኘት የወሰንን ሲሆን፡ ሆስፒታሉ በቂ ዝግጅት እስኪያደርግ ድረስም (ለሁለት ሳምንታት) የጽኑ ህሙማነን (ICU) የማዋለጃ ክፍል(labor ward) እና ድንገተኛ ክፍል ( EOPD)ን ብቻ በተረኛ (duty) መርሃ ግብር መሰረት የምንሸፍን ይሆናል::

በመሆኑም፣ የሁሉም የትምህርት ክፍል ሀላፊዎች፣ የሆስፒታላችን የአስተዳደርር ሰራተኞች፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አመራሮች እና ሎሎች ችግሩ የሚመለከታችሁ አካላት ድምጻችንን ለማሰማት የሄዴንበትን ውጣ ውረድ ግምት ውስጥ በማስገባት፣ ከጎናችን ትቆሙ ዘንዴ በአክብሮት እንጠይቃለን" ብለዋል::

በአቋሙ መሰረትም፣ ከግንቦት 7 ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት አንስቶ የስራ ማቆም አድማው የጀመረ ሲሆን፣ ከጥቁር አንበሶቹ ተለማማጅ ሀኪሞች በተጨማሪ የጎንደር፣ የአርሲ፣ የጅማ አቻዎቻቸውም ቀደም ብለው የስራ ማቆም አድማ አድርገዋል::



የህክምና ባለሙያዎች ድምፃቸውን ሲያሰሙ

### ለስራው ማቆም መነሻ የሆነው

ሀኪሞቹን ተስፋ አስቆርጦ ወደ ስራ ማቆም አድማ የወሰዳቸው፣ በወዲያኛው ሳምንት ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ ከጤና ባለሙያዎች ጋር በነበራቸው ቆይታ የተነሱትን ጥያቄዎች አቃለው በማለፋቸው መሆኑ ታውቋል:: ተማሪዎቹ ባወጡት መግለጫ፣ "መንግስት ጥያቄዎቻችንን ለመመለስ ዝግጁ አለመሆኑን ተረድተናል" እስከ ማለት የደረሱት ጠ/ሚ/ሩ ተስፋ አስቆርጠዋቸው መሆኑን ይናገራሉ::

ጠ/ሚ/ሩ፣ ከጤና ባለሙያዎቹ ጋር በነበራቸው ቆይታ ባደረጉት ንግግር፣ "እናንተ ሐኪሞች አሁን የምላችሁን ብቻ ፃፉና፣ ስብሰባችንን እንቋጭ፤ ሐኪም ንፅሕናውን አይጠብቅም ፤ ጋውኑን እንኳን በስርዓት አይዝም፤ ስንቶቻችሁ ነው ሰዓት የምታከብሩት? ሲኒየሩ ሐኪም ስራውን ሙሉ ለሙሉ ለነርስ አይደል እንዴ ጥሎ የሚሄደው? ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ተመንዝሮ የማያልቅ ተስፋ እንጂ ብር የላትም፤ ምን አልባት ለዘይትና ሽንኩርት 500ብር እንጨምርላችሁ ይሆናል፤ ለሁለት ሰዓት በሆስፒታል ውስጥ ለማይቆይ ሲኒየር ሐኪም 9,000ብር ሲበዛበት ነው፤ በሬ እየታረሰበት፣ ስጋውም እየተበላ፣ ቆዳውም ለጅማት ክር እየዋለ፣ ይሄ ሁሉ ሲደረግበት ምንም ነገር አይናገርም፤ ሐኪምም እንደዚህ በሬ ነዉ መሆን ያለበት፤ "መኪና መኪና ላላችሁት፣" አንድ መኪና እንግዛላችሁና፣ መንዳት በጣም ቀላል ስለሆነ ተራ በተራ ትነዳላችሁ:: ዛሬ አንደኛው በር ላይ(መኪናዋ) ከቆመች፣ ነገ ሌላኛው በር ላይ ... ፤ እኔም (እራሳቸው ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ) የ ICT ባለሙያ ነኝ፤ ወደ ውጪ መውጣት አቅቶኝ አይደለም፣ "ሀገሬን ላገልግል" ብዬ ነው (ከሀገር ያልወጣሁት) ፤ለምንድን ነው ሚኒስትሮች ለጉንፋን እንኳን ውጨ ሀገር ሄደው የሚታከሙት? ሲባል፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ሕክምናም ሐኪምም ስለሌለ እና ለsecurity ሲባል ነው፤ ሰሞኑን ሐኪሞች ስላኮረፋችሁ፣ ለኩርፊያችሁ የሚሆን ምሳ ብሉና፣ ቤተ-መንግስቱን ጎብኝታችሁ ወደ ስራችሁ ተመለሱ፤ በአክቲቪስቶች እንዳትጠለፉና የፖለቲካ መጠቀሚያ እንዳትሆኑ ተጠንቀቁ" ማለታቸው ይታወሳል::

የጠ/ሚ/ሩን ንግግር ተከትሎ፣ ገለልተኛ የነበሩ የህክምና ባለሙያዎች ሳይቀሩ ተቃውሞ አሰምተዋል:: ከእነዚህ መካከል አንዱ የሆኑት፣ ዶ/ር ካሳው ከተማው በማህበራዊ ሚዲያ ሲፅፉ፣ "በጠቅላይ ሚ/ጽ/ቤት በተደረገ ስብሰባ ጥያቄዎችን ከመመለስ ይልቅ የተሰጠው ስድብና ማንቋሸሽ የተቀላቀለበት መልስ እጅጉን አሳዝኖናል ፤ የስራ ሞራላችንም ጎድቶታል" ብለዋል፤ አባባላቸው የብዙዎቹን አመለካከት እንደሚወክል ብዙዎች ይስማሙበታል::

### የኢትዮጵያ ህክምና ማህበር ጋዜጣዊ መግለጫ

የስራ ማቆሙን አድማ ተከትሎ፣ መንግስት ስራ ባቆሙት ላይ ህጋዊ እርምጃ እንደሚወስድ፣ አብዛኞቹም አድመኞቹን እንዳልተቀላቀሉ በመግለፅ አጣጥለዋቸዋል ፡ በዚህ ድባብ ሀሙስ ግንቦት 8 የኢትዮጵያ ህክምና ማህበር ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥቷል:: ጋዜጣዊ መግለጫውን የማህበሩ ፕሬዘዳንት ዶክተር ገመቺስ ማሞና ምክትላቸው ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ዓለሙ መርተውታል::

ዶ/ር ገመቺስ ማሞ በመግቢያነት ባሰሙት ንግግር፣ የሀኪሞች ችግር ከ30 ዓመታት በላይ መቆየቱን፣ ችግሩን ማህበሩ በተደጋጋሚ ለመንግስት ሲያቀርብ መቆየቱን፣ ችግሩ መፍትሄ ማግኘት ስላልቻለ ግን፣ ከፍተኛ የባለሙያዎች ፍልሰት መከተሉን፣ ለዚህም በአብነት የሚጠቀሰው በአንድ ወቅት በሀገር ውስጥ 600 የህክምና ዶክተሮች ብቻ ሲቀሩ፣ በአንፃሩ በአሜሪካ ብቻ 2000 ሀኪሞች ተሰድደው መሄዳቸውን ተናግረዋል:: በዚህም ሳቢያ፣ መንግስት ጥራትን መስዋዕት አድርጎ የጤና ባለሙያዎችን በብዛት ማስመረቅን እንደ መፍትሄ መውሰዱን፣ በዚህም ዘመቻ በቂ ዝግጅት ሳይደረግ 5 ብቻ የነበሩት የመንግስት የህክምና ትምህርት ቤቶች ወደ 28 ከፍ ማለታቸውን፣ በግል ዘርፉ ደግሞ ከዜሮ ወደ 8 ማደጋቸው፣ በዚህም ሳቢያ፣ ብዛት ያላቸው ተማሪዎች እየተመረቁ ሥራ ለማግኘት መቸገራቸውን ገልፀዋል::

ከ4 ወራት በፊት ማህበሩ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር ስምምነት ደርሶ እንደ ነበር፣ ስምምነቱ ግን ተግባራዊ ሳይሆን መቅረቱን ተናግረዋል:: ነገሮች በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያሉ፣ በአርሲና በጅማ የህክምና ባለሙያዎች ሰልፍ መውጣታቸውንና፣ ይህን ተከትሎ ማህበሩ ለጠ/ሚ/ሩ ደብዳቤ አስገብቷል ብለዋል::

ሚያዝያ 26 ከጠ/ሚ/ሩ ጋር በተደረገው ውይይት፣ ማህበሩ እንደ ማህበር ለጠ/ሚ/ሩ ጥያቄ እንዳያቀርብ እንደተከለከለ ዶ/ር ገመቺስ ተናግረዋል:: የህክምና ባለሙያዎች በተደራጀ መልክ ጥያቄ እንዳያቀርቡ በታፈኑበት በዚያ ስብሰባ ማጠናቀቂያ፣ ጠ/ሚ/ሩ፣ "አንድም የሚጠቀስ የህምና ባለሙያ (ድጋፍ) ማጣታቸው ልባችንን ሰብሮታል" ብለዋል::

### ለጠ/ሚ/ሩ የተደረገላቸው ይቅርታ

በስብሰባው ጊዜ ጠ/ሚ/ሩ አንድም በአርያነት የሚጠቀስ የህክምና ባለሙያ ማጣታቸው ትክክል አለመሆኑን፣ እውነታው ግን፣ ሀገሪቱ በርካታ በአርያነት የሚጠቀሱ የህክምና ባለሙያዎች እንዳሏት፣ ጠ/ሚ/ሩ ስላልጠቀሷቸው የህክምና ባለሙያዎች ቂም እንዳልያዙባቸውና ይቅርታ እንደሚያደርጉላቸው ዶክተር ገመቺስ ሲናገሩ እንዲህ ብለዋል፡-

ወደ 23 ዞሯል

# ሀረርና የ50፡50፡0 ቀመር
# “ሀረር በቄሮዎች እየተመራች ነው”

## የሀረር ነዋሪዎችን መብት ለማስከበር በመቋቋም ላይ ያለ የሲቪክ ተቋም አመራር አባላት

ሀረር በቄሮዎች መታመስ ከጀመረች ይሄው አንድ ዓመት ሆኗታል:: ባለፈው ዓመት ችግሩ እንዲባባስ ያደረገው፣ ቄሮዎች ከሞላ ጎደል የጥላ መንግስት መስርተው እንዲንቀሳቀሱ በመደረጉ መሆኑን ነዋሪዎች ይናገራሉ:: ይህ ሂደት ህዝባዊ ተቃውሞን እየወለደ ሲሆን፣ የዜጎች መብት በእኩልነት እንዲከበር የሚታገል አንድ የሲቪክ ተቋም በመቋቋም ሂደት ላይ ይገኛል:: የእንቅስቃሴው አመራር አባላት ከኢትዮጲስ ጋር ቆይታ አድርገዋል፤ ለደህንነታቸው ሲባል ግን ስማቸውና ምስላቸው እንዳይወጣ ተደርጓል::



### በመቋቋም ላይ ያለው የሲቪክ ተቋሙ ሰብሳቢ

የመጣነው ከሀረር ነው:: ሀረር ላይ ባሉ መሰረታዊ ችግሮች መደራጀት እንዳለብን ተማምነን ለህዝቡ ሁሉ መብት የቆመ የሲቪክ ተቋም በማቋቋም ላይ ነን:: ይህ ማህበር በቅርቡ ይፋዊ እንቅስቃሴ ይጀምራል ብለን ተስፋ እናደርጋለን:: በመጀመሪያ አነሳሳችን ለበጎ አድራጎት ተግባር የነበረ ቢሆንም፣ ሌሎች መሰረታዊ ጥያቄዎችንም ማሰማት የግድ በማለቱ፣ ዓላማችንን ከፍ አድርገነዋል::

በድሬድዋ በስራ ላይ ካለው 40፡ 40፡ 20 የስልጣን ክፍፍል ጋር በሚመሳሰል መልኩ፣ በሀረር ላይ በይፋ ያልታወጀ፣ በተግባር ግን 50፡50፡0 የሚባል አሰራር አለ::በዚህ ቀመር፣ በሀረር ውስጥ ያለው የስልጣንና የመብት ክፍፍል 50 ከመቶው ለሀረሪ፣ 50 ከመቶው ለኦሮሞ፣ 0 ከመቶው ደግሞ ለሌላው የማህበረሰብ ክፍል ተደልድሏል:: በሀረሪ ዜሮ ከመቶ እንዲሆን የተፈረደበት የህብረተሰብ ክፍል፣ በአፓርታይድ ዘመን ጥቁሮች በደቡብ አፍሪቃ ሁሉንም መብቶች እንደተነፈጉት ሁሉ፣ እሱም በሀገሩ ሁለተኛ ዜጋ ለመሆን ተገድዷል:: አፓርታይድ በደቡብ አፍሪቃ ቢፈርስም፣ በሀገሪ ግን በሁለት እግሩ ቆሞ ይገኛል፤ ይህን ቀንበር ጥሎብን የሄደው ህወሓት ነው፤ ዓላማውም ህዝቡን ከፋፍሎ መግዛት ነበር:: የህወሓት አገዛዝ ተገርስሷል፣ አሰራሩን ግን የሀረር ህዝብ አሁንም ድረስ ተሸክሞት ይገኛል::

ሀረር በምትተዳደርበት በዚህ ፍፁም አድሏዊ ቀመር፣ ወጣቱ ተምሮ የመንግስት ስራ ለመቀጠር ሲሄድ፣ መስፈርቱ እውቀት ሳይሆን፣ ብሄርና ቋንቋ መለያ እየሆነበት ሥራአጥ መሆን በትውልዱ የተጫነበት እጣ ፋንታው ሆኖ ይገኛል:: በዚህ ሳቢያ ወጣቶች እትብታቸው የተቀበረበትን ቀያቸውን በስደት እየለቀቁ፣ እንጀራ ፍለጋ ወደ ሌላ አካባቢ ለመሄድ ተገድደዋል:: ማህበራችን እነዚህንና ተያያዥ ጉዳዮችን ለመታገል እንቅስቃሴ ያደርጋል፤ ሀረር የሁሉም ነዋሪዎቿና የመላው ኢትዮጵያዊያን ናት::

ሀረር ላይ የሚፈፀም ድርጊትን ሚዲያዎች ለምን ሽፋን እንደማይሰጡ ለመረዳት ተቸግረናል:: እስከ ለውጡ ድረስ፣ በጣም አናሳው ማህበረሰብ፣ ክልሉን በበላይነት እንዲመራ ነበር የተደረገው:: ከለውጡ በኋላ ደግሞ፣ የአመራሩ አክሲል ከዚህ አነስተኛ ቁጥር ካለው ማህበረሰብ እጅ ወጥቶ፣ ህጋዊ ሰውነት፣ ህጋዊ መሪ፣ የምታወቅ ዓላማና ግብ የሌለው ቄሮ ወስዶታል:: በአዋጅ ደረጃ ባይሆንም፣ በተግባር ግን፣ በይፋ የሚታወቀው የክልሉ መስተዳድር፣ ቄሮ በሚባል ጥላ መንግስት ተተክቷል::

በዚህ አካሄድ እንዴት ነው ወደፊት የምንቀጥለው? በሚል እየተነጋገርን እንገኛለን:: በሀገር አቀፍ ያለው ለውጥ፣ ሀረር ላይ አይደርስም ወይ? በሚል ተደራጅተን ጥያቄዎችን ለማቅረብ እየተዘጋጀን ነው::

መከላከያ ሰራዊቱ ወደ ሀረር ከገባ በኋላ የነበረው ረብሻ ቀንሷል፤ በፊት ግጭቶች ነበሩ:: ዋናው የምንቃወመው ነገር፣ 50፡ 50፡ 0 የሚባለውን የአፓርታይድ አሰራር ነው:: ይህ ሲተነተን 50 በመቶው ስልጣን ሀደሬ፣ የቀረውን 50 በመቶ ደግሞ ኦሮሞው፣ ቀሪው ህብረተሰብ ደግሞ፣ ባዶ እጁን፣ ወይም ያለምንም ውክልና ይቀራል ማለት ነው:: ከ37 ከመቶው በላይ የክልሉ ነዋሪ ግን፣ ሀደሬም ኦሮሞም እንዳልሆነ የህዝብ ቆጠራ ውጤቶች ያሳያሉ:: አናሳው ብዛት ባለው ላይ ነው መብት ያለው፤ በየትኛው የዲሞክራሲ መስፈርት ነው ይህ አግባብነት የሚኖረው? አፓርታይድ የሚባለው እኮ ይህ ነው፤ አናሳው በብዙሃኑ ላይ የበላይ ሲሆን:: የአንድ ሀገር ልጆች ሆነን ይህ መሆኑ አግባብነት የለውም፤ በህግ ፊት ሁላችንም እኩል መሆን ይገባናል::

50፡ 50፡ 0 የሚባለው ቀመር፣ አንዱን የአባወራው ልጅ፣ አንዱን የእንጀራ ልጅ ስለሚያደርግ መቅረት አለበት፤ ሁላችንም የኢትዮጵያ ልጆች ነን፤ በብሄርና በኃይማኖት መበላለጥ የለብንም:: ብሄርና ኃይማኖት የግል ናቸው፤ ሀገር የጋራ ናት፤ በሰላም እንድንኖርባት ሁላችንም እኩል መሆን አለብን:: መመዘንና መገምገም ካለብን፣ በእውቀትና በችሎታ እንጂ፣ ኃይማኖታዊም ሆነ ሳይንሳዊ መሰረት በሌለው ዘራችን መሆን የለበትም፤ ቋንቋ ነው እንጂ የሚለያየን፣ በዘር ሁላችንም የሰው ዘር ነን፤ እንዴት ዜሮ ከመቶ እንደረጋለን? ለውጥ እኛ ጋር ገና አልመጣም የምንለው ለዚህ ነው:: ለውጥማ ቢመጣ በሰውነታችን እኩል መሆናችን የህግ እውቅና ያገኝ ነበር::

### በመቋቋም ላይ ያለው የሲቪክ ተቋሙ ሁለተኛ አመራር አባል

ሀረርን ተቀራምተው ሲያስተዳድሯት የኖሩት የሀረር ብሄራዊ ሊግ (ሀብሊ) እና ኦህዴድ/ኦዴፓ ነበሩ:: የገጠር አካባቢ ቀበሌዎችን የሚያስተዳድረው ኦህዴድ/ኦዴፓ ሲሆን፣ መሀል ከተማው ደግሞ ለሀብሊ ተትቶለት ኖሯል:: ሌላው ተመልካች እንዲሆን ነው የተደረገው:: ይህን ነው አፓርታይድ የምንለው:: ከሁለቱ የፖለቲካ ድርጅቶች ሌላ እንዲኖር አይፈለግም:: በዚህ መልኩ መብት ያለውና መብት የሌለው ዜጋ ተብለን እንድንኖር የተደረገ ቢሆንም፣ የዕለት ተዕለት ኑሯችን ግን የስጋት ነበር ማለት አይቻልም:: ከገዢው ህወሓት ውጭ ላለነው ሁሉ፣ ሀገራችን ሰፊ እስር ቤት ነበረች::

ከለውጡ በኋላ ግን፣ ቄሮ ተብሎ የተደራጀው አካል፣ የመንግስት ጥላና ስውር ኃይል ሆኖ፣ ከተማዋን እያስተዳደረ ይገኛል:: በይፋ የሚታወቀው የመንግስት መዋቅር እያስተዳደረን አይደለም:: ሰው ተጣልቶ እንኳን ፖሊስ ጣቢያ ሲሄድ፣ ምንም የሚደረገው በቄሮዎች ፈቃድ ነው፤ ፖሊስ ያለ ቄሮ ፈቃድ ህግን ለማስከበር ይፈራል፤ ፈቃድ ይጠይቃል:: ለምሳሌ፣ የሀረርን ቧንቧ የሚያሰብሩት ይታወቃሉ፤ አሰባሪዎቹ ጥቅም ፈላጊ ባለሀብቶች ሲሆኑ፣ ሰባሪዎቹ ቄሮዎች ናቸው:: ማንነታቸው ቢታወቅም ግን፣ ሁለቱንም ህግ አይጠይቃቸውም:: ቆሻሻ እንዳይደፋ ተብሎ፣ ስለ 60 ሚሊዮን ብር ክፍያ ተደራድረዋል፤ የእነዚህም ማንነት ሚስጥራዊ አይደለም:: ስማቸው ከቄሮ ጋር ስለተቆራኘ ማንም ሊጠይቃቸው አይችልም:: ታዲያ፣ “ሁለት መንግስት አለ” ያለው ዝም ብሎ ነው ማለት ይቻላልን?

ህወሓት የሾመቻቸው ሰዎች ናቸው አሁን ድረስ መንግስት መዋቅር ላይ ያሉት:: እነሱ ቄሮን ቢፈሩ ምኑ ይገርማል? ብዙ ጣጣ ከጀርባቸው አለ:: “ለውጥ መጣ” ተብሎ፣ “ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ” ሲባል ደስ ብሎን ካጨበጨብን በኋላ፣ ለውጡ በቄሮ በኩል የነውጥ ኃይል ሆኖ መጣ::

አሁን ባለው የአፓርታይድ ድባብ፣ ብዛት ያለው የሀረር ህዝብ ስጋት ላይ ነው:: በተላይ፣ የብሄር አስተሳሰብ ተማሪዎች ላይ የፈጠረው ተፅእኖ በጣም ከባድ ነው:: ህፃናት የብሄራቸውን ስም ሲጠየቁ፣ እስከ መቀየር የደረሱበት ጊዜ ላይ ደርሰናል:: ይህን ለመቋቋም፣ የግድ ተደራጅቶ መታገል ያስፈልጋል:: ቄሮ የሚባልው ቡድን መፈጠሩ የህግ ልዕልናን ጥያቄ ውስጥ እየከተተው ይገኛል፤ ውሃ ቆርጦ “ገንዘብ አምጡ፣” “ቆሻሻ አትደፉም” ብሎ “ገንዘብ አምጡ፣” እየተባለ ይገኛል:: የት ሀገር ነው እንደዚህ የተደረገው?

ቄሮዎች እስር ቤት ድረስ እየሄዱ የፈለጉትን እያስፈቱ፣ የጠሉትን እስከማሳሰር የደረሱበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር፤ ትራንስፖርት ተሳፍረው ከመክፈል ይልቅ፣ የሹፌሩን ብር ይነጥቃሉ፤ እነሱን መክሰስ አይቻልም፤ እንደመብታቸው ይታይላቸዋል፤ ይህ ሁሉ በቄሮዎች ጉልበት ብቻ የሚሆን አይደለም፤ በኦህዴድ/ኦዴፓ ውስጥ ባሉ ደጋፊዎቻቸው የሚታገዙ ናቸው:: ዋናው ኃይላቸውም ይሄው የውስጥ ድጋፍ ነው::

### በመቋቋም ላይ ያለው የሲቪክ ተቋሙ ሦስተኛ አመራር አባል

አሁን ያሉት የሀረር ባለስልጣናት ለሚቀጥለው ምርጫ እንዳይመረጡ መስራት አለብን፤ ይህ ነው እያቋቋምነው ያለው የሲቪክ ተቋም ግብ:: ህዝቡ የምርጫ ካርዱን በተደራጀ መልክ ከተጠቀመ፣ የክልሉ ባለቤት ይሆናል:: አብዛኛው የክልሉ ህዝብ በሰላምና በፍቅር መኖር ነው የሚፈልገው፤ የሚከፋፍለውን አይፈልግም፤ የአንድነት፣ የአብሮ መኖር፣ የፍቅር መልዕክት ይዞለት የሚመጣን እጁን ዘርግቶ ይቀበለዋል::

ህወሓት ህዝቡን ለመከፋፈል ያልፈነቀለው ድንጋይ ባይኖርም፣ ህብረተሰቡ ግን አሁንም ድረስ አንድ ላይ እየኖረ ነው:: የሀረር ህዝብ መከፋፈልን አይፈልግም፣ ባህሉ አብሮ መኖርን ነው የሚያስተምረው:: ቄሮ ነን ብለው ችግር የሚፈጥሩብን አብረውን የሚኖሩ አይደሉም:: ራቅ ካለ አካባቢ እየመጡ ነው ችግር የሚፈጥሩብን፤ በከተማዋ ውስጥ ግን የሚያስተባብሯቸውና የሚደግፏቸው ባለሀብቶችና ባለስልጣናት አሉ:: እነዚህ ትራንስፖርትና አበል እያቀረቡ ነው ዱላ የሚይዙ ቄሮዎች ወደ ከተማዋ እየገቡ ሁከት ሲፈጥሩ የነበሩት:: አወቁትም አላወቁትም፣ ቄሮዎች የተወሰኑ ብልጥ የፖለቲካ ሰዎች ዓላማ ማስፈፀሚያዎች ናቸው::

# የህክምና ባለሙያዎች ጥያቄ ፍትሃዊና ወቅታዊ ነው

በያዝነው ሳምንት የህክምና ባለሙያዎች ብሶት ጫፍ ደርሶ የስራ ማቆም አድማ እስከማድረግ ደርሰዋል:: የህክምና ባለሙያዎቹን ለተቃውሞ ያነሳሷቸው ጉዳዮች በቅርብ የተፈጠሩ አይደሉም፤ ለረዥም ጊዜ የቆዩ መሆናቸው በውል ይታወቃል:: እነዚህን ጥያቄዎች ሶስት ዋና ዋና ጭብጦች አሏቸው ማለት ይቻላል:: ከሁሉ አስቀድሞ፣ መንግስትም ሆነ ህብረተሰቡ፣ ለህክምና ሙያም ለመምህራን እንደተሰጠው ዓይነት እውቅናና ክብር ሊሰጠው ይገባል የሚል አቋም አላቸው:: የህክምና ሙያ ብዙ ፈርጆች አሉት:: ከእነዚህ መካከል፣ በተለምዶ ሀኪሞች ወይም ዶክተሮች ለሚባሉት ህብረተሰቡ የሚሰጠው ክብር ከፍተኛ እንደሆነ ቢታወቅም፣ እንደ ነርስ፣ ጤና ረዳት፣ ላብራቶሪና የራጅ ቴክኒሻን የመሳሰሉት ተገቢውን እውቅናና ክብር ተሰጥቷቸዋል ማለት አይቻልም:: በመንግስት በኩል፣ ዶክተር፣ ነርስ፣ ጤና ረዳት፣ ወዘተ ብሎ ሳይለይ የመምህራንን ያህል እንኳን ትኩረት ሊሰጣቸው ፈቅዶ አያውቅም፤ ይህ የቆየ አስተሳሰብ በዚህ የለውጥ ወቅትም እንዳልተለወጠ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ ባለፈው ሳምንት ከጤና ባለሙያዎቹ ጋር ባደረጉት ቆይታ ፍንትው ብሎ ታይቷል::

በሁለተኛ ደረጃ ሊባል በሚችል መልኩ፣ የስራ ደህንነታቸው ሁሌም የተጓደለ በመሆኑ፣ መድኃኒት በሌላቸው ተላላፊ በሽታዎች የተጠቁ ህሙማን በርከት ባሉበት በዚህ ዘመን፣ በየዕለቱ ከአደጋ ጋር ለመፋጠጥ ተገድደዋል:: ይህ ችግር መንግስታዊ ትኩረት አግኝቶ በቂ በጀት ከተመደበለት በቀላሉ ሊቀረፍ እየቻለ፣ በስጋት ውስጥ ለመኖር መገደዳቸው አግባብ አለመሆኑን ነው የሚናገሩት፤ ይህ ደግሞ፣ ቀደም ብሎ ከተነሳው እውቅናና ክብር ከማግኘት ጋር የሚቆራኝ ነው::

በመጨረሻም፣ በሚሰጡት አገልግሎት ልክ ያለመከፈሉ ጉዳይ አለ:: ይህ አጠቃላይ ሀገራዊ ችግር ነው ማለት ቢቻልም፣ በህክምና ባለሙያዎች ዘንድ ያለው ሁኔታ በሌሎች ዘርፎች ካለው የባሰ መሆኑን የተለያዩ ጥናቶች በተጨባጭ አሳይተዋል:: ሀገሪቷ ባላት ውስን አቅምም ቢሆን፣ “የክፍያ ማሻሻያ ይገባናል” የሚል ፅኑ አቋም አላቸው::

በየጊዜው እየተባባሰ የሚገኘው የኑሮ ውድነትና ሀገሪቱ ያለችበት የለውጥ ሂደት ግምት ውስጥ ሲገቡ፣ የህክምና ባለሙያዎቹ ስለ ደምወዝም ሆነ ስለክብራቸውና ስለ ሥራ ከባቢ ደህንነታቸው ጥያቄዎች ማንሳታቸው በራሱ ሊያስወቅሳቸው አይችልም:: ለውጡ ሃሳባዊ ብቻ ሆኖ፣ “ለውጡ እንዳይደናቀፍ” እየተባለ የሽግግር ዘመኑ ሊጠናቀቅ አይችልም፤ አንድ ቦታ ላይ የለውጡ ቱሩፋት መሬት ላይ ውሎ፣ ህዝብ ተጨባጭ የሆኑ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጥያቄዎቹን ማንሳትና ለምላሻቸው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማድረግ መቻል አለበት፤ የጫጉላው ዘመን ከአንድ ዓመት በላይ ሊዘልቅ አይችልም:: የለውጡ ዕድሜ የአንድ ዓመት መስመሩን ካለፈ በኋላ፣ ማንም ጥያቄውን ቢያቀርብ በችኩልነትና በለውጥ አደናቃፊነት ከቶ ሊከሰስ አይችልም::

በዚህ መለኪያ፣ በተገቢው ጊዜ የመብት ጥያቄ ያነሱት የጤና ባለሙያዎቹ ያጋጠሟቸው ተግዳሮቶች አሳሳቢ ሆነው አግኝተናቸዋል:: ጥያቄያቸውን በሰላማዊ መንገድ በሰላማዊ ሰልፍ ለማቅረብ የተንቀሳቀሱ የጤና ባለሙያዎች፣ ተደብድበውና ተፈንክተው የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተፈፅሞባቸዋል:: ህወሓት ከቤተ መንግስት ተሰናብቷል፣ አሰራሩ ግን አሁንም እንደነገሰ ነው:: እውነተኛ ለውጥ የግለሰቦች መቀያየር አይደለም፤ የአስተሳሰብ ለውጥ ነው::

በሌላ በኩል፣ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ ከጤና ባለሙያዎቹ ጋር በነበራቸው ቆይታ ያደረጉት ንግግር፣ በሽግግር ዘመኑ ላይ ያንዣበበውን አደጋ ያመላክታል:: ጠ/ሚ/ሩ ባደረጉት ንግግር፣ “እናንተ ሀኪሞች፣ አሁን የምላችሁን ብቻ የፃፉና፣ ስብሰባችንን እንቋጭ” ያሉት፣ ከዚህ በፊት ስለ ሽግግር መንግስት መቋቋም ተጠይቀው፣ “የሽግግር መንግስት አያስፈልግም፣ እኔ አሸጋግራችኋለሁ” ያሉት አባባል ቅጥያ ነው:: በሁለቱም አባባሎች፣ ጠ/ሚ/ሩ ብቸኛ አዋቂ፣ ብቸኛ አድራጊ ፈጣሪ፣ ብቸኛ ሰጪ ሆነው ቀርበዋል፤ የሽግግሩን ዘመን የመጀመሪያ ዓመትም በዚህ መንፈስ ሆነው ሄደውበታል:: ከዚህ ሂደት እንደ ሀገር ያተረፍነው ፓለቲካዊ አለመረጋጋትን፣ የሶስት ሚሊዮን ህዝብ መፈናቀልን፣ በብሄር ግጭቶች ደም መፋሰስንና የኢኮኖሚ መቀዛቀዝን ሆኗል:: ከጤና ባለሙያዎቹም ጋር አዛዥና ታዛዥ ሆኖ ሁኔታዎችን ለማስኬድ የተደረገው ሙከራ የስራ ማቆም አድማን አስከትሏል፤ ቤተ መንግስት የገቡት አዳዲሶቹ መሪዎቻችን ይህን እውነታ ልብ ሊሉት ይገባል::

ዘመኑ ተለውጧል፤ ይህ የድርድር፣ የውይይት፣ የሰጥቶ መቀበል፣ የመጋራት (ስልጣንን ጨምሮ፣) ዘመን ነው:: የህክምና ባለሙያዎቹ እምቢተኝነት በአየር ላይ የተፈጠረ አይደለም፤ ህወሓትን በመታገል ሂደት ፍርሃትን ማሸነፍ እንደሚቻል ያየ ህዝብ አዲስ አስተሳሰብ መገለጫ ነው:: ባለንበት ዘመን፣ የሰልጣን ወንበር ላይ የተቀመጡ መሪዎች የሚሉትን በፀጥታ እያደመጠ ማስታወሻ የሚይዘው የህዝብ ቁጥር በጣም ቀንሷል:: ይህችን ሀገር ከህዝብ የተነጠለ መንግስት እንደልብ የሚጋልብበት ዘመን ላይመለስ አክትሟል::

የህክምና ባለሙያዎች ጥያቄ ፍትሃዊና ወቅቱን የጠበቀ ነው፤ አፋጣኝ ምላሽ ሊሰጣቸው ይገባል::



# ኡስታዝ አቡበከር አህመድ የወሰንና ማንነት ምክትል ኮሚሽነር ሆኑ

የተወካዮች ምክር ቤት የአስተዳደር ወሰን እና የማንነት ጉዳዮች ኮሚሽን ኮሚሽነር እና ምክትል ኮሚሽነር ሹመትን አፀደቀ።

ምክር ቤቱ የኮሚሽነር እና ምክትል ኮሚሽነር ሹመትን ያፀደቀው፣ በጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ በቀረበለት የውሳኔ ሃሳብ መሰረት ነው፡፡ በዚህ መሰረትም፣ ዶክተር ጣሰው ገብሬ የአስተዳደር ወሰን እና የማንነት ጉዳዮች ኮሚሽን ከሚሽነር፣ እንዲሁም፣ ኡስታዝ አቡበክር አህመድ ደግሞ፣ የኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነር ሆነው ተሹመዋል።

ኡስታዝ አቡበከር አህመድ የሙስሊሞች መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ ሰብሳቢ በመሆን የሚታወቁ ሲሆን፣ ህወሓት ስልጣን ላይ በነበረበት ጊዜ ለእስር ተዳርገው ለበርካታ ወራት ታስረው በለውጡ ሳቢያ መለቀቃቸው ይታወሳል፡፡ በጊዜው በፌድራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አራተኛ የወንጀል ችሎት በአቡበከር አህመድ የክስ መዝገብ የተካተቱ 18 ተከሳሾችን፣ ከ7 እስከ 22 ዓመታት የሚደርስ ፅኑ እስራት በይኖባቸው ነበር፡፡ በሀሰት የሽብር ክስ የ22 ዓመት እስር ከተወሰነባቸው መካከል አቡበከር አህመድ፣ አህመዲን ጀበል፣ ያሲን ኑር እና ከሚል ሽምሱ ይገኙበት ነበር፡፡ ከሽብር ክሱ በተጨማሪ፣ በአቡበከር አህመድ ላይ ሌላ የሀሰት ክስ ተመስርቶ የነበረ ሲሆን፣ የክሱ ጭብጥ ሀምሌ 8/2004 ዓ.ም በተለምዶ ሱማሌ ተራ በሚባለው አካባቢ በንብረትና በሰው ህይወት በመኪና ጉዳት አድርሰዋል የሚል ነበር፡፡ ከእስር ከተፈቱ በኋላ፣ አብበከርና ጠ/ሚ/ር ዐቢይ ጥሩ መግባባት መፍጠር እንደቻሉ ይነገራል፡፡

ምክር ቤቱ የኮሚሽኑን ኮሚሽነር እና ምክትል ኮሚሽነር በ25 ተቃውሞ በአብላጫ ድምፅ ማፅደቁም ታውቋል። ተውቃሞው የተሰነዘረው ከምክር ቤቱ የህወሓት አባላት ሲሆን፣ የትግራይ ክልላዊ መስተዳድር፣ “የኮሚሽኑ መቋቋም ኢ- ህገ መንግስታዊ ነው” በማለት ለፌዴሬሽን ምክር ቤት አቤት እንደሚል ማስታወቁ ይታወሳል፡፡ ኮሚሽኑ በቀዳሚነት ከሚመለከታቸው ጉዳዮች መካከል የሲዳማ፣ የወልቃይትና የራያ ጉዳዮች ይሆናሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

የአስተዳደር ወሰን እና የማንነት ጉዳዮች ኮሚሽን አባላት 41 አባላት ያሉ ሲሆን፣ ከእነዚህ መካከል በቅርቡ ህይወታቸው ያለፈው ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ፣ የቀድሞው ፕሬዘዳንት ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ፣ ዶ/ር አረጋዊ በርሄ፣ ሌንጮ ለታ፣ ፕ/ር መረራ ጉዲና፣ አንዳርጋቸው ፅጌ፣ የሽዋስ አሰፋ፣ በለጠ ሞላ፣ ፕ/ር ካሳሁን ብርሃኑ፣ ዘገዬ አስፋው፣ ፕ/ሮ ፍስሃ ፂዮን መንግስቱ የመሳሰሉ ተዋቂ ግለሰቦችንም ያካተተ ነው፡፡

በተመሳሳይ መልኩ፣ ምክር ቤቱ የእርቀ ሰላም ኮሚሽን ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ ሹመትንም አጽድቋል። በዚህም መሰረት ካርዲናል ብርሃነ እየሱስ ሱራፌል ሊቀ ጳጳሳት ዘካቶሊካውያን የኮሚሽኑ ሰብሳቢ፤ ወይዘሮ የትነበርሽ ንጉሴ ምክትል የኮሚሽኑ ሰብሳቢ ሆነው ተሹመዋል። ምክር ቤቱ የእርቀ ሰላም ኮሚሽን ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ ሹመትን በአብላጫ ድምፅ ያጸደቀው ሲሆን፥ 10 ድምፅ ተአቅቦና አራት ተቃውሞ ቀርቦበታል።

የእርቀ ሰላም ኮሚሽን አባላትም 41 ሲሆኑ፣ ከእነዚህ መካከል አቡነ አብርሃም፣ ሃጂ ኡመር እድሪስ፣ ዶ/ር ምህረት ደበበ፣ የዓለም ሎሬት ዶ/ር ጥበበ የማነብርሃን፣ ፕ/ሮ በየነ ጴጥሮስ፣ ልዑል ራስ መንገሻ ስዩምና የቀደሞው የደቡብ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አባተ ኪሾን የመሳሰሉ ታዋቂ ግለሰቦችን ያካተተ ነው፡፡

**ሥራ አስኪያጅ፡- እስክንድር ነጋ**
ጉለሌ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 03 ፣
የቤ.ቁ.434

**ዋና አዘጋጅ፡-** ጌጤ ታደሰ
አዲስ ከተማ ክ/ከተማ፣
ወረዳ 04፣ ቤ.ቁ.273

**አዘጋጅ፡-** ቢኒያም አሊ

**የዚህ ሣምንት የአምድ ተስተናጋጆች**
ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ
ረዳት ፕሮፌሰር ለገሠ ጥጋቡ
ዶክተር አጥላው ዓለሙ
ተባባሪ ፕሮፌሰር ፔይተን ኖፐፍ
አብርሃም ቲ. ዘርኼ
ገበየሁ ዋለልኝ
ዳንኤል አኬች ቲዮንግ

**ኮምፒውተር ጽሁፍ**
ፍቅሬ ታደሰ

**ሌይ አውት ዲዛይን**
ሀብታሙ መኮንን

መስከረም 12/2011 ዓ.ም ተመሰረተ፡፡
ዘወትር ቅዳሜ የሚታተም ሳምንታዊ ጋዜጣ
አሳታሚ፡- ናሠእ ኃ.የተ.የግ.ማ
አታሚ፡- ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣
አራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 17/የቤት ቁ.984

**አድራሻ**
አዲስ አበባ፣ አራዳ ክ/ከተማ
ወረዳ 09፣ አራት ኪሎ፣
ቤት.ቁ 3-13 ሦስተኛ ፎቅ፣
ስልክ 0930 59 44 88
email- ethiopis27@gmail.com



**ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ**
**ደራሲ፣ ተርጓሚ፣ የታሪክ አጥኚና የቋንቋ ሊቅ**
**አሜሪካ**

# የነፃነት ጮራ



## "እስከ መገንጠል ድረስ"

ክቡር ዶክተር ዐቢይ አህመድ ሥልጣን እንደያዙ፥ የኢህአዴግ ህገ መንግሥት መከበር እንዳለበት ማብሰራቸውን እናስታውሳለን። ህገ መንግሥቱ የፈቀደው በአንድ በኩል የተባበሩት መንግስታት ድርጅት (Organization of United Nations) እንዲከበር ያወጀው የግለሰብ መብት፣ በሌላ በኩል ደግሞ፣ የትም ሀገር የሌለውን "እስከ መገንጠል ድረስ" የሚለውን የሀገር መበታተንን ቀመር ነው። የግለሰብ መብት መከበር ስለታወጀልን፥ የፖለቲካ እስረኞች ነፃ ወጡ፤ ታስሮ የነበረው የመናገርና የመጻፍ መብታችን ስለተለቀቀልን፥ መንግሥትን እየተቸን እንጽፋለን። ይኸ ዓይነት ፈቃድ መምዕላይ (dictator) በሚገዛበት ሀገር የማይታሰብ ነው፤ ያዝልቅልን። የተለቀቀው የመሰብሰብ መብታችን ግን የእግር ብረቱ ሰንሰለት ረዘመልን እንጂ፥ ገና አልተበጠሰልንም፤ አሁንም እንደታሰርን ነን። "እስከ መገንጠል ድረስ" የሚለው የሀገር መበታተን መብት ተብዬ ልዩ ትኲረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው።

ያም ሁሉ ሆኖ፥ የነፃነት ጮራ ፈንጥቋል። ዋናው ምልክት፣ ከላይ የጠቀስኳቸው መብቶች መለቀቅ ሳይሆን፥ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት የአስተዳደሩን ጥፋት ሲነቅፉ መሰማቱ ነው። የተፈናቃዮችን ሁኔታ ሊያጠና የወጣው ቡድን ጥናቱን በ25 ገጽ አጠናቅቆ፥ ለምክትል ጠቅላይ ሚንስትር አቶ ደመቀ መኰንን ያስረክባል፤ ዘገባው የመንግሥት ባለሥልጣኖችን ይወነጅላል። ሁለት ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን የተፈናቀሉት መንግሥት ህግ ባለማስከበሩ፥ እንዲያውም ሽፋን እየሰጠ የወንጀሉ ተሳታፊ በመሆኑ እንደሆነ ይመሰክራል፤ ምክትል ጠቅላይ ሚንስትሩ ዘገባውን በተራቸው ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቀረቡ፤ ይኸ ሁሉ አዲስ ባህል ነው። ገዢው መለስ ዜናዊ ቢሆን ኖሮ፥ የጥናቱን ቡድን አስጠርቶ፥ ዘገባቸውን "እንዲያስተካክሉ" ያዝዛቸው ነበር።

## አዲሱ ነገር

አዲሱ ነገር፥ መንግሥት ዘገባውን መቀበሉ ብቻ ሳይሆን፥ መጸጸቱ ጭምር ነው። እነሱ በሚያስተዳድሩበት ዘመን ይኸን ዓይነት አሠቃቂ ወንጀል በመፈጸሙ፣ ምክትል ጠቅላይ ሚኔስትሩ ማፈራቸውንና፣ አንገታቸውን የሚያስደፋ ስህተት መሆኑን አምነዋል፤ የሰላም ሚንስትሯም ደግፈዋል።

የምክር ቤቱ አባላት ዘገባው ሲደርሳቸው፥ ሁሉም ያስለመዱንን ዝምታቸውን አላሳዩንም። ሦስት ሰዎች ቁጣቸውን ሲገልጹ፥ "ማፈር ብቻ አይበቃም፤ መጠየቅ አለበት"፤ "እርምጃ መወሰድ አለበት" ሲሉ ተሰምተዋል። እርግጥ፥ ሁሉም ድፍረት አላሳዩም። ግን የፍርሀት ጉብዝናው ሲፈሩት ነውና፥ እንዲህ ከተደፈረ፥ ፈሪ ነው፤ ጠበል እንደተረጨበት እርኩስ መንፈስ ተንኖ ይጠፉና ሌሎችም ይዳፈራሉ። ሲዳፈሩ፥ በውስጥ በድብቅ የሚያምኑት አደባባይ ወጥቶ ይፋ ይሆናል። ከወቀሳ አልፈው ምን መደረግ እንዳለበት ውሳኔ ያሳልፋሉ። ኃላፊነቱን ያጐደለው ባለሥልጣን እንዲባረር ይጠይቃሉ፤ የተፈናቀሉት ሳይውል ሳያድር እንዲካሱ ይደረጋሉ፤ ወደቀድሞ ህይወታቸው ተመልሰው ያላንዳች ሥጋት እንዲኖሩ ዋስትና ይሰጣቸዋል። ዳኛ ሳያስፈቅድ ህዝብ አያስገድድም። በዚህ ጊዜ በመንግሥታችን ላይ ያለን ጥርጣሬ ይደበዝዝና እምነታችን ሥር መስደድ ይጀምራል። ምሁራን ወቀሳቸውን ትተው ለችግር መፍትሔ የሚሆን ምክር ይሰጣሉ።

አሁን እንግዲህ፥ ከዚህ የሚቀጥሉት ዋና ዋና እርምጃዎች ሁለት ናቸው። እነሱም የህዝብ ህገ መንግሥት መጻፍና ተቀባይነት ያለው ርቱዕ ምርጫ ማካሄድ ናቸው። የህዝብ ቈጠራን ሦስተኛው አስፈላጊ እርምጃ የሚያደርጉ አሉ። ግን የህዝብ ቈጠራ ብዙ ዝግጅት ስለሚያስፈልገው፥ አሁን ይጀመር ከተባለ የምርጫውን ዘመን ያርቀዋል። የህዝብ ቈጠራውን ከምርጫው ጋር ማገናኘት አያስፈልግም። የመራጩን ቍጥር ለማወቅ ከሆነ፥ በተሰጠው የምርጫ ካርድ ይታወቃል። ጎሳውንና ጾታውን ለማወቅ ከሆነ፥ በአሁኑ ሁኔታችን እንደዋና ጉዳይ የሚታይ አይደለም። እርግጥ በተራቀቁት ሀገሮች ቢሆን፥ ምን ዓይነት ህዝብ ማንን መረጠ ለማለት፥ ጾታ፥ ጎሳ፥ እድሜ፥ ትምህርት፥ የዓመት ገቢ . . . ይጠየቃል።

## የህገ መንግሥት ጉዳይ ሲነሣ

ወሳኙ አዲሱ ህገ መንግሥቱ ነው። የህገ መንግሥት ጉዳይ ሲነሣ፥ ሊደረግ የሚገባው ካለው የህወሓት/ኦነግ ህገ መንግሥት ውስጥ የሚሻሻሉትን አንቅጽ ማሻሻል ብቻ ነው የሚሉ ሰዎች አሉ። የጠላት ህገ መንግሥት ወዲያ ይጣላል እንጂ፣ እንደጠላት ንብረት አሻሽሎ የሚያስቀሩለት ነገር አይኖርበትም። አዲስ ህገ መንግሥት ማርቀቁ ግዴታ ነው። ሲረቀቅ እርግጥ አንዳንድ አንቅጽ በጠላት ህገ መንግሥት ውስጥ ያሉትን ሊመስሉ ይችላሉ፤ የአጋጣሚ ጉዳይ ነው።

አዲሱን ህገ መንግሥት የሚያረቅቀው የባለሙያዎች ቡድን መጀመሪያ በህጉ ውስጥ ምን ምን መካተት እንዳለበት በንድፍ ደረጃ ለራሱ ያቀርባል። በረቂቁ ውስጥ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና የኢትዮጵያውያንን በህግ ፊት እኩልነት ይካተቱበታል። የመንግሥቱ አወቃቀር አሃዳዊ ይሁን? ወይስ ፌዴራል ይሁን? የሚል ክርክር አለ። ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን አሃዳዊ መንግሥት ለምን ፌዴራል ማድረግ እንዳስፈለገ በገለልተኝነት መተቸት አለበት። የፌዴሬሽን ፅንሰ ሃሳብ የተወለደው የራሳቸው መንግሥት ያላቸው ህዝቦች መንግሥታቸውን ጠብቀው አንድ መንግሥት የሚሆኑበት ዘዴ ሲፈልጉ ነው። አንድን አሐዳዊ መንግሥት በፌዴሬሽን ለማዋቀር ከተፈለገ፣ መጀመሪያ አንዱን መንግሥት ወደ ብዙ መንግሥታት መከፋፈል ያስፈልጋል። ግን ለምን? ደግሞስ እምን ላይ የተመረኰዘ ክፍፍል ይደረጋል? ሰብሮ መጠገን ይመስላል።

ይኸም ሆኖ፥ ፌዴሬሽንን የሚፈልጉት ድምፃቸው መሰማት አለበት። ፌዴሬሽኑ ይጠበቅ የሚሉት ምን አግኝተውበት ነው? የአሐዳዊ መንግሥት አስተዳደር የነፈጋቸውን ፍላጎት የፌዴራል ሥርዓት ይሰጣቸዋል ወይ? የሚፈልጉት የፌዴራል ሥርዓት ቢዋቀር ሁላችንንም በእኩል መብት ያስተዳድራል ወይ? የእነዚህ ጥያቄዎች መልሳቸው አዎን ከሆነ፥ ለሚፈልጉት ስንል ልንቀበለው ይገባል።

አሁን ያለው የፌዴራል ሥርዓት ግን ለብዙዎች የራስ ምታት ሆኗል። ለያይቶናል፤ ራሳቸውን የቻሉ ህዝቦች አድርጎናል፤ በተሰጠን ድምበር ላይ እያጣላን ነው። ከተዘረጋ ጀምሮ እንዲሰበሰብ እንደጨቀጨቅነው ነው። አንድ ጣራ ካፈሰሰ፥ መፍትሄው የጣራውን ቀዳዳ መድፈን እንጂ፥ በዘነበ ቍጥር ውሃውን በማሰሮ መቀበል አይደለም። ሆኖም፥ እንዳይለወጥ የሚፈልጉ ብዙዎች ናቸው። ሥርዓቱ ብዙዎችን እንደሚበድል ሲያሳዩዋቸው በውይይት በመርታት ፈንታ፥ የሚሰጡት መልስ "እንዳይበድል እናደርገዋለን" ነው። ይኼ ቅቡልነት የሌለው መልስ ነው። እምነታችን በእግዚአብሔርና መብታችንን በሚያስጠብቅ ህገ መንግሥት እንጂ፥ በሰው ላይ አይደለም። ሀገር በአደራ አይተዳደርም።

## ሚዛኑ ወይም ዳኛው ሰብአዊ መብት ነው

ሆኖም፥ አሃዳዊ መንግሥትን የሚደግፈው ወገን ፌዴሬሽንን የሚደግፈው ወገን የሚሰጠውን ምክንያት መረዳት ይኖርበታል። ሚዛኑ ወይም ዳኛው ሰብአዊ መብት ነው። በየትኛውም የአስተዳደር ሥርዓት የማንም ሰው ሰብአዊ መብት እንዲነካ አንፈልግም። ብዙዎች ያለውን የጎሳ ፌዴሬሽን ሥርዓት የሚቃወሙት ሀገሪቱን ይከፋፍላታል ብለው ነው፤ እውነትም ነው። ሌላውና ዋናው የተቃውሞ ምክንያታችን ግን ሰብአዊ መብትን ስለሚጥስ ነው። የኢትዮጵያን አንዱን ክፍል ቈርሶ፥ ቍራሹን እዚያ ለሚኖረው ለትልቁ ነገድ እንዲያስተዳድር

ወደ 20 ዞሯል



ረዳት ፕሮፌሰር ለገሠ ጥጋቡ
የህግ መምህር
በፍርድ ቤቶች ጠበቃና አማካሪ

# የአዲስ አበባ ህዝብ ራሱን በራሱ እያስተዳደረ ነው ማለት አይቻልም

## አዲስ አበባ

የአዲስ አበባ ጉዳይ ትልቅ ሀገራዊ አጀንዳ ነው:: አሁን ትልቅ ፖለቲካዊ አጀንዳ ሆኖ መጣ እንጂ፣ ምሁራን፣ በተለይ የህግ ምሁራን፣ ሲፅፉበት ቆይተዋል:: ከህግ ትንታኔ አኳያ፣ መነሻው የህጎች ሁሉ ምንጭ ከሆነው ህገ መንግስት ነው:: የአንድ ህገ መንግስት ህልውና የሚያውጠነጥነው፣ ከሁሉም አስቀድሞ፣ ከይዘቱ ይልቅ በቅቡልነቱ (Legitimacy) ዙሪያ ነው::

ከዚህ አኳያ ሲመዘን፣ አሁን በሀገራችን ያለው ህገ መንግስት የቅቡልነት ችግር (Legitimacy problem) ያለው ነው:: ህገ መንግስቱን በማውጣቱ ሂደት፣ በተለይ በተቃውሞ ጎራ ያሉት ማበረሰቦች ተገለው ስለነበር፣ የአብዛኛው ህዝብ አመለካከት አልተወከለበትም ማለት ይቻላል:: በዚህም ሳቢያ፣ "በጭራሽ በህገ መንግስቱ ዙሪያ አንደራደርም" የሚሉ እንዳሉ ሁሉ፣ "ህገ መንግስቱ ሲረቀቅም ሆነ ሲፀድቅ አልተወከልንበትምና፣ በጭራሽ አንቀበለውም" የሚሉ አካላት አሉ:: ባለፈው አንድ ዓመት ደግሞ፣ "በሂደቱ ባንሳተፍም፣ የተለያዩ ጥቅማ ጥቅም አግኝተንበታል፣ ስለዚህ እንቀበለዋለን፣" የሚሉ ብቅ ብቅ ብለዋል:: ሆኖም፣ "በሂደቱ ስላልተወከልን አንቀበለውም" የሚሉት ወገኖች (በኦሮሚያ (በኦነግና ደጋፊዎቹ)፣ በዐማራ፣ በአዲስ አበባ፣ በደቡብ፣ በአፋር፣ በሱማሌ፣ ወዘተ) ቁጥራቸው በርካታ መሆኑ ህገ መንግስቱ ላይ በቀላሉ ሊታይ የማይችል የቅቡልነት ችግር እንዳለ ያሳየናል:: በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ፣ ህገ መንግስቱ ገዢ ሰነድ ሆኖ በውስጡ የተካተቱ ህጎች አስገዳጅ ሆነው እየተፈፀሙ መገኘታቸው ችግር ማስከተሉ አይቀርም ማለት ነው:: በቅርቡ እንኳን፣ የገዢው ግንባር አካል በሆነው አዴፓ ውስጥ "ህገ መንግስቱ መሻሻል አለበት" የሚል አቋም እየተወሰደ ይገኛል:: የአዲስ አበባ ጉዳይ በቀዳሚነት የሚታየው ከህገ መንግስቱ ቅቡልነት ጋር በተያየዘ ነው::

ሁለተኛ፣ "ህገ መንግስቱ የቅቡልነት ችግር የለበትም" ቢባል እንኳን፣ ይዘቱ ሲነበብ፣ አዲስ አበባ የህዝቧና የመላው ኢትዮጵውያን መሆኗን ይጠቅሳል፤ አንቀፅ 49 በግልፅ ያስቀምጠዋል፤ ምንም የተወሳሰበ ነገር የለውም:: ራሷን በራሷ የምታስተዳድርና ተጠያቂነቷም ለፌድራል መንግስቱ መሆኑ በግልፅ ሰፍሯል::

ይህ ምን ማለት ነው? ለብሄር ብሄረሰቦች የተሰጠው ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ለአዲስ አበባም ተሰጥቷል ማለት ነው:: "ተጠያቂነቷ ደግሞ፣ ለፌደራል መንግስቱ ነው" ይላል:: እያንዳንዱ ክልል ተጠያቂነቱ ለክልሉ ህዝብ ነው:: በሌላ በኩል፣ እንያንዳንዱ የከተማ አስተዳድር ተጠያቂነቱ ለክልሉ አስተዳደር ነው:: አዲስ አበባ ግን፣ ተጠያቂነቷ ለክልል ህዝብም አይደለም፣ ለክልል አስተዳደርም አይደለም፣ በግልፅ ለፌድራሉ መንግስት ነው ተብሏል:: ህገ መንግስቱ፣ ከክልሎች ለይቶ አስቀምጧታል:: ከዚህ አንፃር፣ አዲስ አበባ ለማንኛውም የክልል ህዝብም ሆነ አስተዳደር ተጠያቂ እንዳልሆነች፣ የሁሉም ህዝብ ወኪል ለሆነው ለፌድራል መንግስቱ ተጠያቂ መሆኗን ያስረዳል:: አዲስ አበባ ልዩ የሆነች የፌድራሉ አባል ነች::



አንዳንዶች፣ "በአንቀጽ 47 የፌደሬሽኑ አባሎች፣ ወይም ክልሎች፣ ሲጠቀሱ፣ ስሟ ስላልተጠቀሰ ራሷን የቻለች የፌደሬሽን አባል አይደለችም የሆነ ክልል አካል መሆን አለባት" ይላሉ፤ ይህ በጣም የተሳሳተ አተያይ ነው:: አንቀፅ 47 የሚያወራው ክልል ስለሆኑ አባላት ብቻ ነው:: በፌድራል ስርዓት አባላት ክልሎች ብቻ አይደሉም፤ ትልልቅ የከተማ አስተዳደሮች ራሳቸውን ችለው የፌደሬሽን አባላት መሆን ይችላሉ:: ለምሳሌ፣ የአሜሪካንን ፌደሬሽን ብንወስድ፣ 50 ክልሎች ሲኖሩት አንድ ዋና ከተማው፣ ዋሽንግተን ዲሲ፣ የፌደራል ዲስትሪክት (District of Colombia) አለ፤ 16 ደግሞ፣ ክልል ያልሆኑ አባል ግዛቶች (ቴሪቶሪስ የሚሏቸው) አሉ:: በብራዚልም አንድ የፌደራል ዋና ከተማ የሆነ ዲስትሪክት ሲኖር፣ 26 ክልሎች አሉት:: ሜክሲኮም እንዲሁ ዋና ከተማዋ የፌደራሉ ዲስትሪክት ናት፣ 31 ክልሎች ደግሞ አሉ:: ከኢትዮጵያ በጣም ተቀራራቢ የሆነው የህንድ ፌደራሊዝም ደግሞ፣ 29 ክልል ሲኖራቸው፣ 7 ራሳቸውን የቻሉ ዲስትሪክቶችና ራሳቸውን የቻሉ ግዛቶች (ቴሪቶሪስ የሚሏቸው) አሉ:: ከዚህ አንፃር፣ የአዲስ አበባ ህጋዊ አቋም፣ ክልል ያልሆነ ልዩ ቁመና ያለው የፌደራሹኑ አካል ነው፤ ለማንም ክልል ተጠያቂ ያልሆነ፣ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ተጠያቂ ለሆነው ለፌድራሉ መንግስቱ ተጠያቂ ነው::

ከዚህ በተጨማሪ፣ ስለ ኢትዮጵያ ግዛት ወሰን የሚናገረውን አንቀጽ ሁለትን ጠቅሰው፣ "አዲስ አበባ የኦሮሚያ ክልል አካል ነች እንጂ፣ ራሷን የቻለች አይደለችም" ብለው የሚከራከሩ አሉ፤ ይህም ፍፁም ስህተት ነው:: ይህ አንቀፅ ስለ ሀገሪቱ አለማቀፋዊ የግዛት ወሰን የሚያወራ ሲሆን፣ የክልሎችን የግዛት ወሰን የሚያጠቃልል መሆኑን ያገለፃል:: ይህ ስለ ውጫዊ ወሰን፣ ዓለም አቀፍአዊ እውቅና ስላለው ወሰን የሚናገር እንጂ፣ ከአዲስ አበባ ጋር የሚያገኘው ነገር የለም:: ይህ በሀገር ውስጥ በክልሎች መካከል ስላለው የአስተዳደር ወሰን ጋር የሚምታታ አይደለም::

በመጨረሻም፣ አዲስ አበባ ራሷን የቻለች ስለመሆኗ ህገ መንግስቱ በግልፅ ሲያስቀምጥ፣ "አዲስ አበባ የኦሮሚያ አካል ነች" አይልም:: ህገ መንግስቱ የሚለው፣ "አዲስ አበባ በኦሮሚያ ክልል መሃል ናት፣" በእንግሊዝኛ within ነው የሚለው እንጂ፣ in አይልም:: ሁለቱ የእንግሊዝኛ ቃላት ለህገ ባለሙያዎች ግልፅ ናቸው፤ ትርጉማቸው በጣም የተለያየ ነው:: የቃላት አመራረጡና አቀማመጡ፣ ሙያዊ በሆነ መንገድ የተለያየ ነው:: ጆግራፊካል ቦታዋ (የተፈጥሮ መገኛዋ፣) የኦሮሞ አስተዳደር አካል አለመሆኗን በግልፅ ለያይቶ አስቀምጦታል:: በአጠቃላይ፣ በአዲስ አበባ ባለቤትነት ጉዳይ ዙሪያ፣ ህገ መንግስቱ የቅብልነት ችግር ቢኖርበትም፣ በባለቤትነቷ ዙሪያ የኦሮሚያ ናት ሊያስብል የሚችል አንቀፅ የለውም::

## የፌዴሬሽን ምክር ቤትና አዲስ አበባ

የህገ መንግስት ትርጉም የሚያስፈልገው ነገር ወደ ፌዴሬሽን ምክር ቤት ነው የሚመራው፤ በፌዴሬሽን ምክር ቤት ደግሞ አዲስ አበባ ውክልና የላትም፤ ይህ አሁን ያለው አሰራር መሰረታዊ ችግር እንዳለበት ያመለክታል:: ለላይኛው ምክር ቤት ህገ መንግስት የመተርጎም ስልጣን የሰጠችው ብቸኛዋ ሀገር ኢትዮጵያ ናት፤ ይህ መሆኑ ትልቅ ውዝግብ እንዲነሳ አድርጓል:: ለምሳሌ፣ ደቡብ አፍሪካና ጀርመን የህገ መንግስት ፍርድ ቤት አላቸው:: በአሜሪካና ሌሎች ሀገሮች፣ መደበኛ ፍርድ ቤቶች ይህን ስልጣን ይይዛሉ:: በሀገራችን ግን፣ የፖለቲካ ተቋም ነው ህገ መንግስቱን እንዲተረጉም ስልጣን የተሰጠው:: ህጉ በትክክል በባለሙያ ተተርጉሞ ሳይሆን፣ ፖለቲካኞች በመሰላቸው በድምፅ ብልጫ ነው የሚወስኑት:: ይህ የህግ ትርጉም ሳይሆን፣ ፖለቲካዊ ውሳኔ ነው ሊባል የሚችለው::

ከዚህ በተጨማሪ፣ አዲስ አበባ ራሷን ችላ በፌደሬሽኑ ምክር ቤት ውስጥ አለመወከሏ ሌላው ችግር ነው፤ በሌለችበት ይወሰንባታል ማለት ነው:: በዚህ መንገድ የተላለፈ ውሳኔ የቅቡልነት ችግር ይኖረዋል::

ፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ በዓመት ሁለት ጊዜ እየተሰበሰበ በየቀኑ የሚፈፀሙ የህገ መንግስት ጥሰቶችን እንዲተረጉም መታጨቱ፣ ሊወጣው የማይችለው ኃላፊነት ነው:: ሌላ ከፖለቲካ ገለልተኛ የሆነ ተቋም ነበር ስልጣኑን መያዝ የነበረበት::

## አዲስ አበባና የከንቲባ ሹመት

"የአዲስ አበባ ተጠያቂነት ለፌድራሉ ነው" ሲባል፣ "ሪፖርት ታደርጋለች፣ ይከታተሏታል፣ አብራ ትሰራለች" ማለት ነው እንጂ፣ "አስተዳደሯን የፌዴራል መንግስቱ ይወስንላታል፣ የፈለገውን አምጥቶ ይሾምባታል" ማለት አይደለም:: ሙሉ የሆነ ራስን በራስ የማስተዳደር መብት በህጉ ተሰጥቷታል::

አሁን ኢንጅነር ታከለ ኡማን በሚመለከት የተደረገው ሹመት፣ ችግር ያለበት አካሄድ ነው:: ህዝቡ ያልመረጣቸው ከመሆናቸው ባሻገር፣ ምክትል ከንቲባ ሆነው የከንቲባውን ቦታ ነው ሸፍነው እየሰሩ ያሉት:: ህግ ቀይረው፣ አሰራሩን በሚመቻቸው መልኩ ጠምዝዘው፣ ከንቲባ መሆን የማይችልን ሰው ምክትል ከንቲባ አድርገው የከንቲባውን ቦታ እንዲይዝ ነው የተደረገው:: በዚህ መልክ ነገሮች ተጠምዝዘው፣ "የአዲስ አበባ ህዝብ ራሱን በራሱ እያስተዳደረ ነው" ማለት አይቻልም::

ወደ 21 ዞሯል



**ዶክተር አጥላው አለሙ**
**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**
**የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ መምህርና ኃላፊ**

# የዶላር እጥረት፣ የዋጋ ግሽበትና፣ የእዳ ጫና

የዶላር እጥረት በምንም ይምጣ በምን፣ የሸቀጥ አቅርቦት እጥረት ስለሚፈጥር፣ ዋጋ መጨመሩ የሚጠበቅ ነው። የዋጋ ግሽበት ችግር፣ ከዚህ የዶላር እጥረት መነሻ ባለፈ፣ በመሰረቱ መዋቅራዊም ነው። ጊዜያዊ ችግር ብቻ ሳይሆን፣ የአመራረታችንና የአቅርቦታችን መጠን ያመጣው ችግር ነው። ለምሳሌ ያህል፣ የኢንዱስትሪው ዘርፍ በጣም ደካማ ስለሆነ፣ ከዓመታዊ ምርቱ(GDP) የሚሸፍነው ገቢ ከ5 – 7 በመቶ ብቻ ነው። ይህ መሆኑ ብዙ ዕቃ ከውጭ በዶላር አንድናመጣ ያስገድዳል። ገበያ ላይ ካለው ሸቀጥ አብዛኛው፣ ቻይናና ሌሎች ሀገራት ያመረቱት ነው።እነዚህን በአብዛኛው በሀገር ውስጥ ልናመርታቸው የምንችላቸው ናቸው።

ይህንን ችግር ለመቅረፍ ያለው መፍትሄ ወደ ውጭ የምንልከውን መጨመር ብቻ ሳይሆን፣ የምናመጣውን በመቀነስ ነው። የሀገር ውስጥ ገበያውን ለማሸነፍ፣ ውጭ ባለው ገበያ ተፎካካሪ መሆን የሚችል የአምራች ዘርፍ መገንባት አለብን። የምናስመጣውን መቀነስና የምንልከውን መጨመር የተያያዙ ጉዳዮች ናቸው።

መንግስት "ኢንዱስትሪ መር" በማለት የሚናገረውን እቅድ በአብዛኛው መሬት ላይ ማውረድ አልቻለም። ተጨባጭ የሆነ ነገር ገና በበቂ ሁኔታ አልተሰራም፤ አሁንም ቢሆን የውጭ ንግዱ ግብርና ላይ ላይ ነው የሚተማመነው። ግብርናው ግን ኋላ ቀር ስለሆነ አያዛልቅም።

## የውጭ ምንዛሬ እጥረት እንዳለ በመንግስት መነገር አስፈላጊ ነበር ወይ?

መንግስት ስለዶላር ክምችት የሚያወጣው መረጃ ምን ያህል እንድምታ እንደሚኖረው ለመረዳት፣ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ በአንድ ወቅት የሰጡት አስተያየት ያሳደረውን ተፅዕኖ ማየቱ ይበቃል። ጠ/ሚ/ሩ ከውጭ ገንዘብ አፈላልገው በማስመጣት፣ "አሁን የውጭ ምንዛሬ ችግር የለም" ስላሉ፣ ምንዛሬው በአንድ ጊዜ መውረድ ጀምሮ ነበር፤ ለአንድ ዶላር የሚከፍለው የብር መጠን፣ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ቀንሶ ነበር፤ የሸቀጦች ዋጋም እንደ መረጋጋት ብሎ ነበር። ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣"ከእንግዲህ እጥረት ስለማይኖር ያከማቻችሁትን የውጭ ምንዛሬ አስገቡ" ብለው ማስጠንቀቂያና ማሳሰቢያ በመስጠታቸው፣ የዶላር ዋጋም ቀንሶ ነበር።የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት ከፍተኛ ነው ሲባል ምንዛሬው ወዲያውኑ ይረክሳል፣ በተቃራኒውም ሲነገር ይጨምራል።

ከብሄራዊ ባንክ በቅርቡ በወጣ መረጃ፣ ሀገሪቷ ያላት የውጭ ምንዛሬ ክምችት አነስተኛ በመሆኑ፣"ለነዳጅና ለመድሃኒት ነው ቅድሚያ የሚሰጠው" ተብሏል። የውጭ ምንዛሬ እጥረት እንዳለ በመንግስት በግልፅ ሲነገር፣ በጥቁር ገበያ የሚጠቀሙ ሰዎች ምንዛሬውን ከፍ ማድረጋቸው አይቀርም፤ በተለምዶ፣ እንዲህ ዓይነት እጥረት ቢኖር እንኳን፣ ለህዝብ በይፋ አይገለፅም። በመንግስት በኩል የውጭ ምንዛሬ እጥረት መኖሩ ከተረጋገጠ፣ ከችግሩ የሚገኘን ጥቅም በመገመት (Speculation) ምንዛሬው የበለጠ ያድጋል። የምንዛሬው መናር፣ "ለውደፊት የእቃዎች ውድነት ከፍ ያለ ይሆናል" ለሚል ግምት በር ስለሚከፍት፣ ነጋዴዎችን "ዕቃዎችን ከፍ አድርጌ ልሸጥ" ወደሚል ሃሳብ ይወስዳቸዋል። ስለዚህም፣ በፍላጎትና በዋጋ ላይ ትልቅ ተፅዕኖ በማሳደር ኢኮኖሚው ላይ አሉታዊ እንድምታ ይኖረዋል።

ብዙ ጊዜ፣ ብሄራዊ ባንክ እንዲህ ዓይነት ወሳኝ የሆኑ አንገብጋቢ ጉዳዮችንና መረጃዎችን ይፋ አያደርግም። ባንኩ ይህን ጉዳይ አሁን ይፋ ማድረጉ፣ ለምን ዓላማ እንደሆነ ግልፅ አይደለም። የውጭ ምንዛሬ እጥረት መኖሩ የሚታወቅ ቢሆንም፣ ይፋ ባያደርገው ይሻል ነበር። በተለይ፣"ለመድሃኒትና ለነዳጅ ብቻ ነው ያለው" ማለታቸው፣ ችግሩን ሲያባብሰው ታይቷል። ብዙ ዋጋዎች ላይ ከወዲሁ የዋጋ ጭማሪ እየታየ ነው።

አንዳንድ ሰዎች፣ መንግስት ባልተለመደ መልኩ ይህን መረጃ ይፋ ያደረገው፣ ነጋዴው ገና ለገና እጥረት ይከሰታል ብሎ ዕቃ ማከማቸቱ ስለማይቀር፣ እርምጃ ሊወስድበት አስቦ ነው ሲሉ ይደመጣሉ።ይህ የሚባለው በድብቅ የተጠነሰሰ ሴራ ( conpiracy) አለ ከሚል ግምት ነው። "ዓላማቸው ሌላ ነው" እየተባለ በተለያየ መንገድ ይነሳል፣ እኔ ግን፣ ፣ባለማስተዋል ነው ብዬ አገምታለሁ። ነጋዴውን ለማጥቃት ተወጥኖ ነው ብዬ አላስብም። መረጃው አስቀድሞ በመውጣቱ መንግሥት ምንም ጥቅም አያገኝም። የመንግስት ዓላማ፣ የህብረተሰብን ደህንነት መጠበቅና ኢኮኖሚውን ማረጋጋት ነው። እንደ ወሬው ሆኖ እንኳን፣ መረጃውን አውጥቶ ጥቂት ነጋዴዎችን አስሮ ከሚያገኘው ጥቅም፣ በዋጋ ንረት በኢኮኖሚው ላይ በሚደርሰው ጉዳት የበለጠ ይጎዳል።

## የቻይናው ዕዳ መሰረዝና የውጭ ምንዛሬ

የብድር ጫናን ለመቀነስ ከቻይና ጋር ተስማምተናል ተብሏል። ዕዳው እውነት ከተሰረዘ፣ ሀገሪቷ ለመክፈል የሚያስፈልጋት የዶላር መጠን ቀነሰ ማለት ነው። ወጪያችን ቀነሰ ማለት ግን፣ ሌላ አዲስ ገቢን አስገኘን ማለት አይደለም። የውጭ ብድርን በጥንቃቄ መያዝ ያስፈልጋል። መበደር በጣም አስፈላጊ ቢሆን እንኳን፣ ከበዛ መክፈል የማይቻልበት ደረጃ ይደረሳል። ይህን ደግሞ የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በቅርቡ ነው የሚከታተለው ነው። ጤናማ ኢኮኖሚ ስለመኖሩና አለመኖሩ ትልቅ መጠቆሚያ ነው።

የብድር ጫና በጨመረ ቁጥር ታማኝነት ይሸረሸራል። ታማኝነት ሲዳከም ደግሞ፣ ከውጩ ዓለም ጋር የንግድ ልውውጥ ለማደረግ ችግር ይፈጥራል፤ "አይከፍሉንም፣ አንከፈልም" የሚል ስጋት ይፈጥራል። ሀገራት ብድር የመክፈል አቅማቸው በየዓመቱ እየተለካ ደረጃ ይወጣላቸዋል፤ በዚህ ደረጃ አቅሙ ተዳክሟል የሚባል ከሞላ ጎደል ከዓለም አቀፍ የፋይናስ ተቋማት የሚኖረው ትስስር ያሽቆለቁላል።

ለአንድ ሀገር ወሳኙ ጉዳይ፣ ብድር መብዛትና ማነስ ሳይሆን፣ የመክፈል አቅም አለ ወይ? የሚለው ነው። አሜሪካና ጃፓን የመሳሰሉት ሀብታም ሀገራት፣ ከአጠቃላይ ምርታቸው (GDP) ከመቶ ፐርሰንት በላይ የሆነ ብድር ቢኖርባቸውም፣ የመክፈል አቅም ስላላቸው እንደኛ ስጋት የለባቸውም። የእኛ ብድር አሁን ባለበት ደረጃ፣ከGDP ወይም ከዓመት ምርታችን ከ50 እስከ 60 በመቶ አካባቢ ቢሆንም፣ የመክፈል አቅማችን ከፍ ያለ አይደለም።በአጠቃላይ፣ የተበደርነው ከሌሎች ሀገራት አንፃር ብዙ ነው ሊባል ባይችልም፣ ከመክፈል አቅማችን አኳያ ሲታይ ግን ብዙ ነው ማለት ይቻላል።

ወደ ውጭ የምንልካቸው ምርቶች ጥሩ ደረጃ ላይ ቢሆኑ ኑሮ፣ ዕዳችን ቢበዛም መክፈል ስለምንችል ስጋት አይኖርም ነበር፤ ገቢና ብድር ዝምድና አላቸው። ከዚህ አኳያ፣ ኢትዮጵያ ወደ ውጭ የምትሸጣቸው ምርቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሱ ሄደዋል። ይህም ሆኖ ግን፣ ከውጭ መንግስታትና ከዲያስፖራ የምታገኘው ዶላር በመጨመሩ የተወሰነ ፋታ ሰጥቷታል። ከውጭ መንግስታት የሚገኘው ዶላር በአብዛኛው እዳ ስለሆነ ፣ ወደ ውጭ የሚላከው ምርቶች ላይ ማተኮር የግድ ነው ። አሁን ባለው ሁኔታ፣ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚና የኬኒያ ኢኮኖሚ በጥቅል ዓመታዊ ምርታቸው ተቀራራቢ ቢሆኑም፣ ኬንያ ወደ ውጭ የምትልካቸው ምርቶቿ የምታገኘው ገቢ ከፍተኛ ብልጫ አለው። የኢትዮጵያ የውጭ ንግድ ዘርፍ የራሱ የሆነ አብዮት ይፈልጋል።

## ብድርና ነጭ ዝሆን

በሀገሪቱ ውስጥ ገንዘብንና ብድርን በተመለከተ ኃላፊነት ያለባቸው፣ የገንዘብ ሚኒስቴርና የእቅድ ኮሚሽን፣በአንድነት የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒሰቴር (MOFEC) ይባሉ የነበሩት፤ ተቋማት ናቸው። ብሄራዊ ባንክም ገንዘብንና የውጭ ምንዛሬን በተመለከተ ኃላፊነት አለበት።:::

እነዚህ ሦስት ተቋማት የሀገሪቱ ብድር እንዴት እንደሚከፈል አቅደውና ተቀናጅተው ካልተንቀሳቀሱ፣ መበደሩና መክፈሉ አስቸጋሪ ይሆናል። እስካሁን ብዙ ፕሮጀክቶች በብድር ይሰራሉ፤ ቻይና ካበደረች ኩባንዎቿ እንዲሰሩት ይደረጋል፣ የተበዳሪው ሀገር ድርጅት ሲሰሩት አይታይም ። በተበደርነው ገንዘብ ልምድና ዕውቀት አግኝተን ራሳችንን ለመቻል የሚፈቅድ አሰራር አይደለም። ከሚሰራው ፕሮጀክት የሚገኘው ጥቅምና በዕዳው የሚፈጠረው ጫና ተመጣጣኝ አይደለም። ለምሳሌ፣ በብድር የተሰራው የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ፕሮጀክትን ብናይ፣ ምን ያህል እዳውን የመክፈል አቅም እንዳለው የሚውያውቀው መንግሥት ነው።ሲበላሹም ከቻይና ጥገና በስተቀር በሀገር ውስጥ በለሙያ ያለመታደሳቸው፣

ወደ 20 ዞሯል



# በአዲስ አበባ በ5 ክፍለ ከተሞች ድንገተኛ ፍተሻ ተደረገ

የአዲስ አበባ ፖሊስ ባለፈዉ ሳምንት ለሁለት ሰዓታት ብቻ ባደረገዉ ፍተሻ ብቻ ከ200 በላይ ሕገ-ወጥ አሽከርካሪዎችን መያዙን ገለፀ። ፍተሻው የተደረገው ባለፈው ቅዳሜ፣ ከ10 እስከ 12 ሰዓታት በነበረዉ ጊዜ ሲሆን፣ በተመሳሳይ ጊዜ በአምስት ክፍለ-ከተሞች በድንገት የተደረገ ነበር። በፍተሻዉ ሕገ-ወጥ መድሃኒቶችና የህግ መስፈርቶችን ያላሟሉ ሞተር ብስኪሌቶችም ይዟል። በዚያኑ ቀን ሌሊቱን ቦሌ ክፍለ-ከተማ በሚገኙ የራቁት ጭፍራ ቤቶች በተደረገ አሰሳ፣ አደገኛ ዕፅ፣ ለአደገኛ ዕፅ ሽፋን የሆኑ የሺሻ ማጤሲያዎች፣ አንድ ሽጉጥና 8 ተጠርጣሪ ሰዎችም መያዛቸው ታውቋል።

በተያያዘ ዜና፣ ከመስከረም አንስቶ ወደ አዲስ አበባ ሊገቡ የነበሩ ከ10ሺህ በላይ ሽጉጦች፣ 30 ክላሽንኮቭ ጠብመንጃዎች፣ 4 መትረየስ እና ከ19ሺ በላይ ጥይቶችና ከ180ሺ በላይ የአሜሪካና የልዩ ልዩ ሀገራት ገንዘብ መያዛቸውን ፖሊስ አስታወቀ፡፡ ሆኖም፣ ካለፈው ተመሳሳይ ዓመት ጋር ሲነፃጸር፣ ከባድ ወንጀሎች በቁጥር መቀነሳቸውን ፖሊስ አስታውቋል፡፡ በፖሊስ አባባል ዙሪያ የህብረተሰቡን አስተያየት የጠየቀው የኢትዮጲስ ዝግጅት ክፍል፣ አብዛኛው ተጠያቂ በፖሊስ አባባል እምነት እንደሌለው ለመረዳት ችሏል፡፡

# የብሄራዊ ባንክ ገዢ በቂ የውጭ ምንዛሬ እንዳለ ተናገሩ

“ኢትዮጵያ የመጠባበቂያ የውጭ ምንዛሬ ክምችቷን እንድትጠቀም የሚያስገድድ ሁኔታ አይደለችም” ሲሉ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ዋና ገዥ ዶክተር ይናገር ደሴ ተናገሩ:: በተያዘው ዓመት ሀገሪቷ በቂ የመጠባበቂያ የውጭ ምንዛሬ ክምችት አላትም ብለዋል:: “አንድ ሀገር የውጭ ምንዛሬን በመጠባበቂያነት የምታስቀምጠው፣ ሀገሪቷ ችግር ሲገጥማት ልትጠቀምበት እንጂ፣ ለዕለት ተዕለት ፍጆታ አይደለም:: የሀገሪቷ የዕለት ተዕለት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚመራው ከወጪ ንግድ ፣ ከብድርና እርዳታ ፣ ከውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት እንዲሁም ከዳያስፖራው በሀዋላ ከሚላከው ነው:: በየጊዜው የሚከፈሉ የውጭ ዕዳ ክፍያዎች፣ ለግል ዘርፉ ሌተር ኦፍ ክሬዲት፣ ለነዳጅና ለመድሃኒት ግዥና ለመሳሰሉት ወጪዎችም በዚሁ ይሸፈናሉ” ብለዋል:: ዶክተር ይናገር በሰጡት ገለፃ፣ በአሁኑ ጊዜ ሀገሪቷ ከላይ የተጠቀሱት የውጭ ምንዛሬ ምንጮች ያልተቋረጡ በመሆኑ የመጠባበቂያ ክምችቷን እንድትጠቀም የሚያስገድድ ሁኔታ የሌለ መሆኑን፤ በተያዘው ዓመት ከተለያዩ የውጭ ሀገሮች ምንጮች የተሻለ የውጭ ምንዛሬ በመገኘቱ፣ ከባለፉት ዓመታት በተሻለ የውጭ ምንዛሬ መጠባበቂያዋ ክምችት ያለ መሆኑን፤ በተለያዩ ምክንያቶች አምራች ኢንዱስትሪው የሚፈልገውን ያህን የውጭ ምንዛሬ ማቅረብ ባይችልም፣ ኢኮኖሚውን አሁን ባለበት ሁኔታ ማስቀጠል የሚያስችል በቂ የውጭ ምንዛሬም ያለ መሆኑን ተናግረዋል::

የተቀዛቀዘውን የወጪ ንግድ ማሳደግ ግን ዋነኛው የውጭ ምንዛሬ እጥረትን ለመፍታት የሚያስችል በመሆኑ፣ በግብርናው ዘርፍ ላይ መሰረታዊ ለውጥ ማምጣት ይገባልም ብለዋል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ ስለውጭ ምንዛሬ ያነጋገርናቸው ነጋዴዎች በበኩላቸው፣ ችግሩ ከመቼውም ጊዜ በላይ መባባሱን የገለፁ ሲሆን፣ በጥቁር ገበያ ላይ ያለውም የብር ዋጋ በአስደንጋጭ ሁኔታ እያሽቆለቆለ እንደሚገኝ ገልፀውልናል:: የኢህአዴግ ሥራ አስፈፃሚ ኮሜቴ ባለፈው ሳምንት ባደረገው ስብሰባ ኢኮኖሚውን አስመልክቶ ሰፊ ውይይት ካደረገ በኋላ ባወጣው መግለጫ፣ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ መቀዛቀዙን፣ የውጭ ምንዛሬ እጥረት መኖሩንና አፋጣኝ መፍትሄ እንደሚያስፈልግ ማተቱ ይታወሳል::

# በአፋር ክልል ታጣቂዎች በባጃጅ ላይ ተኩስ ከፈቱ

በአፋር ክልል ገዋኔ አካባቢ በባጃጅ ይጓዙ የነበሩ ሰዎች ላይ ተኩስ ተከፍቶ አንድ ሰው መሞቱ ተገለፀ፡፡ ጥቃቱ የተፈጸመው በባለሦስት ጎማ ተሽከርካሪ (ባጃጅ) ሲጓዙ በነበሩ የግብርና ኮሌጅ መምህራን ላይ ነው። ታጣቂዎቹ በጥቃቱ አንድ ሰው ሲገድሉ ሌላኛውን አቁስለዋል። ጥቃት አድራሽዎቹ በአፋርና ኢሳ መካከል ግጭት አስነስተዋል ተብለው የሚፈለጉ ናቸው ተብሏል፡፡ ከጥቂት ጊዜ በፊት፣ ታጣቂዎች ገዋኔ ከተማ ገብተው አንድ ሰው ገድለው፤ አንድ ሰው አቁስለው፣ አንድ የስምንት ዓመት ህፃን ደግሞ አግተው መውሰዳቸው ይታወሳል፡፡ ገዋኔ አካባቢ በርካታ ጥቃቶች እየደረሱ ሲሆን፣ በአካባቢው በርካታ የፀጥታ ኃይሎች ተሰማርተው ይገኛሉ፤ ከፀጥታ ኃይሎቹ መካከል የመከላከያ ሰራዊት አባላትም እንደሚገኙበት ታውቋል፡፡ የፀጥታ ኃይሉ መኖር ግን፣ በአካባቢው ተደጋጋሚ ጥቃቶች መደረጋቸውን ሊገታ አልቻለም፡፡

# ኢትዮጵያ የገንዘብ ዝውውርን የሚከታተለው ኢግሞንት ልትቀላቀል ነው

ኢትዮጵያ የዓለም አቀፉ ኢግሞንት ግሩፕ አባል ልትሆን ነው፡፡ ተቋሙ በዓለም ዙሪያ ያሉ የገንዘብ ልውውጦችን የሚከታተል ሲሆን፣ በህገወጥ መንገድ የተቀመጡ ወይም የተዘዋወሩ ገንዘቦችን እየተከታተለ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው የሚያደርግ ነው፡፡

159 ሀገራትን በአባልነት የያዘው ኢግሞንት ግሩፕ፣ ሙስናን ጨምሮ በሕገወጥ መንገድ ከሀገር የወጡ ገንዘቦችን ለማስመለስ በአባላት መካከል የመረጃ ልውውጥ እንዲደረግ ያስገድዳል፡፡ ከሙስና ሌላ፣ በሽብርተኛነት ዙሪያም ከፍተኛ ትኩረት እንደሚሰጥ ይታወቃል፡፡ ኢትዮጵያ የተቋሙ አባል ሀገር እንድትሆን ምዕራብዊያን፣ በተላይ አሜሪካ፣ ከፍተኛ ፍላጎት እንደነበራቸው ይነገራል፡፡

ኢትዮጵያ የተቋሙ አባል መሆኗ፣ በህወሓት መራሹ መንግስት ዘመን በውጭ ሀገራት ባንኮች የተከማቹ ገንዘቦችን ለማስመለስ የሚያስችል አቅም ይፈጥርላታል ተብሎ የተገመተ ቢሆንም፣ ገንዘቦቹን ለማስመለስ የሚያስችል መረጃ እንደሌለ ግን የውስጥ አዋቂ ምንጮች ይናገራሉ፡፡ ጌታቸው አሰፋ የደህንነት ኃላፊ በነበሩበት ጊዜ፣ “አብዛኞቹ ከፍተኛ የኢህአዴግ ባለስልጣናት በህንድና በቻይና ገንዘብ ማስቀመጣቸው በማስረጃ ተደግፎ ተደርሶበታል” ብለው ዜና አስለቅቀው የነበረ ቢሆንም፣ አባባሉ በወቅቱ ሲቃወሟቸው የነበሩትን የኢህአዴግ አመራር አባላት ለማሸማቀቅ ሆን ብለው የፈጠሩት ነው ተብሎ ብዙም ትኩረት ሳይስብ ቀርቷል፡፡ ጉዳዩን እንከታተላለን እንደሚሉ ወገኖች ከሆነ፣ ጌታቸው በአዲሱ የደህንነት ኃላፊ ከተተኩ በኋላ በተደረገ ፍተሻ፣ አለኝ ያሉት መረጃ በደህንነት መስሪያ ቤቱ ውስጥ አልተገኘም፡፡ ሆኖም፣ ጌታቸው በርካታ ሰነዶችን ይዘው ወደ ትግራይ የሸሹ በመሆናቸው፣ አሉ የተባሉት ማስረጃዎች ሙሉ ለሙሉ የሉም ተብለው መናገር እንደማይቻል ለማወቅ ተችሏል፡፡ ማስረጃዎቹ በእርግጥ በአቶ ጌታቸው እጅ ካሉ፣ የለውጡን ሂደት ተቃውመው እያደረጉ ናቸው ለሚባሉት እንቅስቃሴዎች ሊጠቅሟቸው እንደሚችሉ ጉዳዩን በቅርብ የሚከታተሉ የፖለቲካ ታዛቢዎች ይናገራሉ፡፡

# “ህገ መንግስቱ ለወላይታ ህዝብ የእንጀራ እናት መሆን የለበትም”

ወላይታ ክልል እንዲሆን የሚጠይቀው ሰልፍ በብዙ ውጣ ውረድ የተፈቀደ መሆኑ አስተባባሪዎች ገለጹ፡፡ የሰልፉ አስተባባሪዎች የወላይታ ሀገር ሽማግሌዎች፣ ዬላጋዎች፣ ንግዱ ማህበረሰብና፣ ምሁራንና ተመላሽ ሠራዊቶች መሆናቸው ታውቋል፡፡ በአንፃሩ፣ በሀዋሳና በሌሎች ከተሞች ሲዳማ ክልል እንዲሆን የሚጠይቁ ሰላማዊ ሰልፎች በተደጋጋሚ ሲደረጉ መሰንበታቸው ይታወሳል፡፡ በዚህም ሳቢያ፣ ከሲዳማ ውጭ ያሉ “የክልል እንሁን” ጥያቄዎች መንግስታዊ ጫና እየተደረገባቸው ይገኛል የሚል ቅሬታ እየተደመጠ ይገኛል፡፡ እስካሁን ድረስ፣ ከወላይታ ሌላ በጉራጌ፣ በጋሞ፣ በከፊቾና በሌሎች የደቡብ ዞኖችም “የክልል እንሁን” ጥያቄ ተነስቷል፡፡

በወላይታ የቀረበው ጥያቄ፣ “ክልል እንሁን” የሚለው ብቻ ሳይሆን፣ በክልሎች መካከል ፍትሃዊ፣ ሚዛናዊና ለሁሉም ተደራሽ የሆነ ልማት መኖር አለበት የሚል መሆኑን አስተባባሪዎቹ ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም፣ በአጎራባች ዞኖች ካሉ ህዝቦች ጋር በሰላም ለመኖር ያለውን ህዝባዊ ፍላጎትን ማካተቱን ተናግረዋል፡፡ የወላይታ ህዝብ፣ “ህገ መንግስቱ ለወላይታ ህዝብ የእንጀራ እናት መሆን የለበትም፣ የክልልነት ጥያቄያችን ይመለስልን” እያለ መሆኑን አስተባባሪዎቹ በማህበራዊ ድረ ገፅ ባስተላለፏቸው መልዕክቶቻቸው ሲገልፁ ሰንብተዋል፡፡

# ሰላማዊ ሰልፍ ተደረገ “ጉራጌ ፍቅር እንጂ እስር አይገዛውም”


ከጉራጌ ዞን መስቃን ወረዳ የተወጣጡ የህብረተሰብ ክፍሎች በዛሬው ዕለት በአዲስ አበባ ከተማ ሠላማዊ ሰልፍ አካሂደዋል:: ሰላማዊ ሰልፈኞቹ ልደታ በሚገኘው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ደጃፍ ላይ የተለያዩ መልዕክት ያላቸውን መፈክሮች በመያዝ ድምፃቸውን አሰምተዋል:: ሰልፈኞቹ ካሰሟቸው መፈክሮች መካከል ፍትህ ለጉራጌ ሕዝብ፣ የክልልነት ጥያቄ በሕገ መንግስትና በሕዝበ ውሳኔ እንጂ በደኢህዴን ሕግ የጣሰ ጥናት አይመለስም፣ ጉራጌ ፍቅር እንጂ እስር አይገዛውም፣ የራስን ወንጀል ለመሸፈን ንፁህንን ማሰር ይቁም፣ በፖሊስ አባላት የጉራጌን ወጣት እየገደሉ ማሸማቀቅ ከትግሉ አያስቆመንም፤ የታሰሩት ወንድሞቻችን በፖለቲካ የሀሳብ ልዩነት እንጂ በወንጀል ተጠርጥረው አይደለም የሚሉት ይገኙባቸዋል::

በደቡብ ክልል የሲዳማን ጨምሮ በርካታ ዞኖች የክልልነት ጥያቄ ያነሱ ቢሆንም፣ ክልሉን እያስተዳደረ የሚገኘው ኢህአዴግ፣ የሲዳማዎችን ጥያቄ ብቻ በማስቀደም በሌሎቹ ላይ ፊቱን አዙሯል ሲሉ የክልሉ ነዋሪዎች ያማርራሉ:: ከጉራጌ ሌላ በወላይታ፣ በከፋ፣ በጋሞና በሌሎች አካባቢዎች የክልልነት ጥያቄ ተነስቷል::

# ጉዞ መቅደላ የ320 ኪ.ሜ የእግር ጉዞ አደረገ

በንጋት መልቲሚዲያና በነፍ ሚዲያ አዘጋጅነት፣ “ጉዞ መቅደላ ፩ ተከፍሎልናል” በሚል መሪ ቃል፣ የዳግማዊ አፄ ቲዎድሮስ የ151 የሙት ዓመትን ለመዘከር፣ መነሻውን ጋፋት የኢንዱስትሪ መንደር፣ መድረሻውን መቅደላ አምባ ተራራ ያደረገ የ320 ኪ.ሜ የእግር ጉዞ ተደረገ።

ጉዞው ከአዲስ አበባ 4፣ ከደብረ ታቦር 1፣ ከጎንደር 3፣ ከባህርዳር 4፣ ከወሎ መቂት2 ተጓዦችን ያሰባሰበ ሲሆን፣ 4 ሴቶች፣ 9 ወንዶች፣ በጥቅላላ 13 ተጓዦችን አካቷል:: አፄ ቲዎድሮስ የሴቫስቶፓል መድፍን እየገፉ የሄዱባቸውን መንገዶች በመጓዝ፣ የፍታውራሪ ገብርዬን ያረፉበትን ቀን (በተንታ) በመዘከርና፣ የአፄ ቲዎድሮስ



እረፍትን በፀሎት በመዘከር፣ በመጨረሻም ዝግጅቱ ጧፍ በማብራት ስነ-ስርዓት ተጠናቋል። የጉዞው ዋና አስተባባሪ ወጣት ምኒልክ ፈንታሁን፣ “ጉዞው አባቶቻችን የከፈሉልንን ዋጋ ለማሰብና አንድነታችንን ለማጠናከር የተደረገ የሠላም ጉዞ ነው:: በቀጣይም በየዓመቱ ይካሄዳል” ብሏል:: በጉዞው ወቅት ከጎንደር እስከ ተንታ ህብረተሰቡ ላሳየው ትብብርና እንግዳ ተቀባይነትም ተጓዦቹ ምስጋና ማቀርባቸውን ወጣት ምኒልክ ገልፆል:: በቀጣዩ ዓመት በሚደረገው ጉዞ ላይ መሳተፍ የሚፈልጉ በማህበረዊ ገፅ ንጋት መልቲ ሚዲያ ገፅ ላይ ሙሉ መረጃ ማግኘት እንደሚቻል ለማወቅ ተችሏል::

# የአዲስ አበባ መምህራን ግንቦት 11 ሰልፍ ለማድረግ እየተነጋገሩ ናቸው

የአዲስ አበባ መምህራን ግንቦት 11/2011 ዓ.ም ሰላማዊ ሰልፍ ለመውጣት ውስጥ ውስጡን እየተነጋገሩ መሆኑን የውስጥ አዋቂ ምንጮች በተላይ ለኢትዮጲስ ጋዜጣ ገልፀዋል፤ እንቅስቃሴው በተላይ በኮልፌ ቀራኒዮ የተጠናከረ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል:: መምህራኑን ለሰላማዊ ሰልፉ ያነሳሳቸው ቀዳሚ ምክንያት፣ "ቤት ይሰጣችኋል" ተብሎ በከንቲባው ጽህፈት ቤት የተገባው ቃል ባለመከበሩ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በመምህራኑ ዘንድ ቅሬታ ካስነሱት ጉዳዮች መካከል፣ ሐምሌ 10/2010 ዓ.ም በአዲስ አበባ ካቢኔ ውሳኔ ከኦሮሚያ ክልል ወደ አዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ እንዲተላለፉ በተወሰኑ የአፋን ኦሮሞ ትምህርት ቤቶች ያሉ መምህራን የሚያገኙት ጥቅማ ጥቅም፣ ከአዲስ አበባ መምህራን በላይ መሆኑ ነው፡፡ ወደ አዲስ አበባ መስተዳድር እንዲተላለፉ የተወሰኑት የአፋን ኦሮሞ ትምህርት ቤቶች፣ ጉለሌ ክፍለ ከተማ የሚገኘው የጀኔራል ታደሰ ብሩ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፣ ኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ የሚገኘው ጀኔራል ዋቆ ጉቱ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት የካ ክፍለ ከተማ የሚገኘው ጉሪ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ናቸው፡፡

በእነዚህ ት/ቤቶች የተመደቡ መምህራን፣ በወር 6000ሺህ ብር ደምወዝ የሚያገኙት፣ የሚከፈላቸው አበል በአማካይ 3000 ሺህ ብር ሲሆን፣ በአንፃሩ በአዲስ አበባ በተመሳሳይ የደምወዝ ደረጃ ያለ መምህር የሚከፈለው አበል 850 ብር ነው የሚል ቅሬታ እየተደመጠ ይገኛል፡፡ ይህንንም አስመልክተው በኮልፌ ቀራኒዮ ያሉ መምህራን ለክፍለ ከተማው ስራ አስፈፃሚ ፊርማ የተሰባሰበት አቤቱታ ማስገባታቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

# በወልደያ ዩኒቨርሲቲ በተነሳ ግጭት በሰውና በንብረት ላይ ጉዳት ደረሰ

ባለፈው ሳምንት መግቢያ፣ በወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ከመጠጥ ውሃ አቅርቦት እጥረት ጋር በተያያዘ በተቀሰቀሰ ግጭት አንድ ተማሪና ስድስት የፀጥታ ኃይሎች መጠነኛ ጉዳት ደረሰባቸው:: በዚህም ሳቢያ የመማር ማስተማር ሂደቱ ለቀናት ተዘግተዋል:: ግጭቱ የተቀሰቀሰው፣ በዩኒቨርሲቲው የማደሪያ ክፍሎች ሁሌም በሚከሰተው የውሃ እጥረት ሲሆን፣ በእጥረቱ ሳቢያ ውሃ በቦቴ መኪና እየተጫነ ሲከፋፈል መቆየቱን ለማወቅ ተችሏል:: ችግሩ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በጣም እየተባባሰ በመሄዱ፣ ተማሪዎቹን ለአንግልትና ለብስጭት ዳርጎ፣ በሳምንቱ መግቢያ ላይ ውሃው በቦቴ ሲከፋፈል በተነሳ ረብሻ በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ የሚገኙት ህንፃዎች ተሰባብረዋል:: ረብሻውን ተከትሎ ፖሊስ ወደ ጊቢው እንዲገባ የተደረገ ሲሆን፣ በዕለቱ ሁኔታዎችን ማረጋጋት የተቻለ ቢሆንም፣ በማግስቱ ተማሪዎች በጊቢው ውስጥ ሰላማዊ ሰልፍ የመሰለ እንቅስቃሴ አድርገዋል ተብሏል:: በዚህም ሳቢያ፣ ስድስት ፀጥታ ኃይሎች በድንጋይ ተመትተው ጉዳት እንደደረሰባቸው፣ አንድ ተማሪ ደግሞ ወድቆ በደረሰበት ጉዳት ሆስፒታል መግባቱን የመንግስት ባለስልጣናት ተናግረዋል:: ተማሪዎቹ ከግቢው ውጭ ያሉ የመንግስት ባለስልጣናትን እንዲያነጋግሯቸው ጥያቄ ማቅረባቸውን ለማወቅ ተችሏል::

# ቦይንግ የ737 አውሮፕላኖችን ችግር ቀደም ብሎ ያውቅ እንደነበር አመነ

አውሮፕላን አምራቹ ቦይንግ፣ 737 ማክስ አውሮፕላኖች ከመከስከሳቸው አንድ ዓመት በፊት ችግር እንደነበረባቸው ያውቅ እንደነበር አመነ:: አውሮፕላኖቹ ችግር እንዳለባቸው በታወቀ ጊዜ የጥንቃቄ እርምጃዎች ከመውሰድ ይልቅ፣ ነገሮችን በማቃለል የአደጋ ጊዜ መጠቆሚያዎችን ብቻ ማዘጋጀቱን ገልጿል::

149 መንገደኞችንና 8 የበረራ ሰራተኞችን አሳፍሮ ወደ ናይሮቢ ይጓዝ የነበረው ET 302 ቦይንግ 737 ማክስ 8 አውሮፕላን፣ ከቦሌ አለም አቀፍ አውሮፕላን ከተነሳ ከ6 ደቂቃዎች በኋላ ደብረ ዘይት አካባቢ መከስከሱ ይታወሳል:: ይህንን ተከትሎም 387 የሚሆኑ ቦይንግ ማክስ 737 አውሮፕላኖች በረራ እንዲያቆሙ ተደርጓል:: ባለፈው ጥቅምት ወርም፣ የኢንዶኔዢያ ላየን አየር መንገድ ንብረት የሆነ ተመሳሳይ አውሮፕላን በመከስከሱ የ189 ሰዎች ሕይወት ጠፍቷል::

ሆኖም፣ ቦይንግ አሁንም እንደሚለው ከሆነ፣ ሁለቱም 737 አውሮፕላኖች ላይ አደጋ ከሚጋጠሙ ከወራት በፊት ችግር እንዳለባቸው ቢያውቅም፣ አደጋው ያጋጠማቸው በዚሁ ችግር ምክንያት ነው የሚለው ገና በምርመራ የሚታወቅ ነው::

ቦይንግ እንደሚለው ከሆነ፣ ችግሩን ካወቀው በኋላ አፋጣኝ እርምጃ ባይወስድም፣ ችግሩን ሊፈታ የሚችል ሶፍትዌር እያዘጋጀ እንደነበረና፣ ለአብራሪዎች ስልጠና ለመስጠት እንቅስቃሴ ላይ ነበር:: አደጋዎቹ ይህንን ከማድረጉ በፊት መከሰታቸው አሳዛኝ አጋጣሚ ነው ብሏል::

የአሜሪካው የፌደራል አቪዬሽን ቁጥጥር ባለስልጣን በበኩሉ፣ ቦይንግ ስለችግሩ የኢንዶኔዥያው አየር መንገድ አውሮፕላን ከተከሰከሰ አንድ ወር በኋላ ነው ያሳወቀኝ ብሏል::

# የታሪክ ትምህርት ክለሳው በውዝግብ ተወጥሯል

አሁን ላይ በትምህርት ሥርዓቱ የሚሰጠው የታሪክ ትምህርት ፖለቲካዊ ይዘት ያለው መሆኑ፣ ይዘቱም የተመረጡ የፖለቲካ ትርክትን ብቻ ማቀፉን፣ የህዝቡን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ እሴትን መዘንጋቱን፣ ይህም ተማሪዎች የኢትዮጵያን ህዝብ ታሪክ በተዛባ መንገድ እንዲረዱ ማድረጉን፣ አካባቢያዊ አስተሳሰቦች እንዲስፋፉ ምክንያት መሆኑን በትምህርት ሚኒስቴር እንደተማነበት ለማወቅ ተችሏል:: በዚህም ሳቢያ፣ የታሪክ ትምህርት ክለሳ እንዲደረግ ግብረ ኃይል ተቋቁሞ በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛል:: ሆኖም፣ የግብረ ኃይሉ እንቅስቃሴ ቀላል እንዳልሆነለትና በውዝግብ መወጠሩን የውስጥ አዋቂ ምንጮች ይናገራሉ:: በጉዳዩ ዙሪያ አስተያየታቸውን የሚሰጡ የታሪክ ምሁራን፣ በሀገሪቱ የታሪክ ትምህርት መዳከሙን፣ መንግስት በታሪክ ትምህርት ውስጥ እጁን ከትቶ እንደነበር፣ የጨቋኝ ተጨቋኝ ትርክት ለትውልዱ እንዲደርስ መደረጉና መጥፎ እንድምታ ማስከተሉን ይናገራሉ::

በሌላ በኩል ግን፣ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አለመካተታቸውን የሚገልጹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጥያቄያቸው ተገቢነት እንዳለው የሚናገሩ ምሁራንም አሉ:: ይህም መስተካከል እንዳለበት በሁሉም ዘንድ ስምምነት እንዳለ ለማወቅ ተችሏል::

አዲስ የሚዘጋጀው የታሪክ ትምህርት፣ የጥንታዊት ኢትዮጵያ፣ የመካከለኛው ዘመን ኢትዮጵያ፣ የዘመናዊት ኢትዮጵያ ታሪክ፣ ከኢኮኖሚ፣ ከማህበራዊ፣ ከፖለቲካና ሌሎች ጉዳዮች አኳያ ተመዝኖ ይቀረፃል ተብሏል:: ሆኖም፣ በልሂቃን ዘንድ በታሪክ አተያይና አተረጓጎም ሰፊ ልዩነት ስላለ፣ በመጨረሻ የሚወጣው ሰነድ ከብዙ ክርክር በኋላ እንደሚሆንና፣ ከዚያም በኋላም የአንዳንዶቹ ቅሬታ ይቀረፋል ተብሎ እንደማይጠበቅ ለማወቅ ተችሏል::

# ህገ መንግስቱ በኢህአዴግ አመራር አባላት መካከል ልዩነት አስነስቷል

የብአዴን/አዴፓ አመራር አባል የሆኑት አቶ ዮሃንስ ቧያለው፣ በያዝነው ሳምንት የኢህአዴግ ይዞታ ከሆነው ዋልታ ቴሌቪዥን ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ፣ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ "ለአንድ ክልል ተብሎ ሀገ መንግስት አይሻሻልም" ያሉት አግባብ እንዳልሆነ ተናገሩ፡፡ አቶ ዮሃንስ በሰጡት አስተያየት፣ "ሕገ መንግስቱ ምንም ጥርጥር መሻሻል አለበት... ከመግቢያው ጀምሮ አንድን ሕዝብ እንደ ጨቋኝ የሚያይ ነው... "የተዛባውን ግንኙነታችን" ሲል ማንን እንደሆነ ግልፅ ነው... ከዚህ ጀምሮ መስተካከል ያለባቸው ብዙ አንቀፆች አሉት... ይህ የሕዝብ ጥያቄ ነው..... ሕገ መንግስቱን ማን ነው የመሰረተው? የሚለው ላይ እንደሚቀርበው አነጣ፣ ሕወሓትና ኢሳያስ ናቸው ይባላል..... ማን ከማን ጋር ነው የተዛባው? ከዚህ ጀምሮ መስተካከል አለበት....... ሕገ መንግስቱ የማይሻሻልበት ምክንያት የለም፡፡ "ለአንድ ክልል ተብሎ አይሻሻልም" የሚባለው ደግሞ ትክክል አይደለም። የትኛው ሕብረተሰብ ተሳትፎበት ነው? ቃለ ጉባኤው ቢታይ መረዳት ይቻላል..... የትኛው አካል 10 ጊዜ ተናግሮ ጫና (እንዳሳደረ በግልፅ ይታያል)...... ቃለ ጉባኤውን ብዙ ሰው አያውቀውም..... መቶ ጊዜ የተናገሩ ሰዎች አሉ..... አንድ ጊዜ ያልተናገሩ የሕዝብ ወኪሎች አሉ..... ስለዚህ አቅም ያላቸው አካላት በሌላው ላይ ጭነዋል ማለት ነው...... የአንድን ኃይል ፍላጎት ለመጫን የተደረገ ጥረት ነው። ይህ ሕገ መንግስት የማይሻሻል አይደለም፣ መፅሐፍ ቅዱስ አይደለም...." ብለዋል፡፡

በረከት ስምዖን

# "ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰት እየተፈፀመብኝ ነው"

ባለፈው ሳምንት፣ "የእምነት ክህደት ቃሌን አልሰጥም" ያሉት የቀድሞው ብአዴን/አዴፓ ከፍተኛ አመራር አባል፣ በያዝነው ሳምንት "የፈፀምኩት ወንጀል የለም፤ ጥፋተኛ አይደለሁም" በማለት ችሎት ቀርበው ተናገሩ:: ከታደሰ ካሳ ጋር የተከሰሱት በረከት ስምዖን፣ ባለፈው ሳምንት በሰጡት የእምነት ክህደት ቃላቸው፣ "ምንም ዓይነት ጥፋት አልፈፀምኩም" ማለታቸው ይታወሳል:: በረከት ስምዖን እንዳሉት ከሆነ፣ ጠበቃ መንግስታዊ ጥበቃ ይደረግላችዋል ከተባለ በኋላም ቢሆን፣ ጠበቃ ለማቆም እየተቸገሩ ይገኛሉ:: ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት አቤቱታ፣ "ክልሉ ህግ የማስከበር አቅም አጥቷል፤ በጠበቃ የመከራከር መብቴን የሚጋፉት በህግ ይጠየቁ፤ ማረሚያ ቤት እና ፍርድ ቤት አስደባለሁ፤ ህግ አለ እዚህ ክልል? ሕገ-መንግሥቱ ይከበራል? ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰት እየተፈፀመብኝ ነው፤ ይህ የፍትህ መጨናገፍ ነው" ብለዋል::

ታደሰም፣ ከበረከት ጋር የሚመሳሰል ሃሳብ ያቀረቡ ሲሆን፣ "ጠበቆች በሚደርስባቸው ዛቻ ምክንያት አልቆሙልኝም፣ ጥበቃ ይደረግላቸዋል ቢባልም ምንም አልተከናወነም" በማለት ተናግረዋል:: ፍርድ ቤቱ በበኩሉ፣ ተከሳሾቹ ጠበቆቻቸውን ለይተው በስም ለፍርድ ቤት ሲያሳውቁ፣ ስለሚደረግላቸው ጥበቃ ይወስናል ብሏል:: ይህንንም ለማድረግ፣ ቀጣዩ ቀጠሮ ከመድረሱ በፊት፣ የጠበቆቹን ማንነት በጽ/ቤት በኩል ያሳውቁ ብሏል:: የምስክሮችን ቃል ለመስማትም፣ ለግንቦት 21 ቀጠሮ ሰጥቷል::

# በኤርትራ ማህበራዊ ድረ ገጾች ተዘጉ

በኤርትራ ውስጥ ማህበራዊ ድረ ገጽ ተቋረጠ:: ከያዝነው ሳምንት መግቢያ አንስቶ ፌስቡክና ሜሴንጀር ያሉ ማህበራዊ መድረኮችን መጠቀም እንዳልተቻለ ነዋሪዎች እየተናገሩ ናቸው:: የኤርትራው ገዢው ፓርቲ የሆነው ሻዕቢያ፣ በሱዳን ውስጥ በተነሳው ህዝባዊ ተቃውሞ በእጅጉ ተደናግጦ እንደሚገኝ ከተለያየ አቅጣጫዎች እየተገለፀ ይገኛል::

ኤርትራ ከኢትዮጵያ ከተገነጠለችበት ጊዜ አንስቶ የምትመራው በኢሳያስ አፈወርቂ ሲሆን፣ ያለፉትን ሶስት አስርታት ዓመታት ምንም ዓይነት የዲሞክራሲ ጭላንጭል እንዳይታይ አድርገዋታል:: አገዛዛቸውም በአፍሪካ አህጉር ካለው እጅግ አስከፊ ስርዓቶች መካከል የቀዳሚነት ስፍራ እንዳለው የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ተቋማት ይገልፃሉ::

በዓለም አቀፉ የኢንተርኔት ስርጭት መረጃ መሰረት፣ ባለፈው ዓመት ኤርትራ ወስጥ 71 ሺህ የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ሲኖሩ፣ ይህም ከአጠቃላይ የህዝብ ብዛት 1.3 በመቶውን ብቻ የሚሸፍን ነው፤ ይህም እውነታ፣ ኤርትራ በዓለማችን ውስጥ ዝቅተኛ የኢንተርኔት ተደራሽነት ካለባቸው መካከል አስፍሯታል::

እንደ ብዙዎች ግምት ከሆነ፣ በ70 ዎቹ የአድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙት ኢሳያስ፣ ስልጣናቸውን አብርሃም ለተባለ ትልቁ ልጃቸው የመስጠት ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው:: ይህንንም እውን ለማድረግ ለአብርሃም ቁልፍ የስልጣን ቦታ ተሰጥቶት ይገኛል::

ሴቶዲስ



አብርሃም ቲ. ዘርኧ
ስደተኛ ጋዜጠኛ
የፔን ኤርትራ ዋና ዳይሬክተር

# የአሜሪካ ልዑካንና የዐቢይ አህመድ የአሰመራ ጉብኝት በንፅፅር

### እንደመግቢያ

ከ14 ዓመታት በኋላ ወደኤርትራ የተጓዘው እና ኢልሃን ኦማርን ያካተተው የዩ.ኤስ. አሜሪካ የልዑካን ቡድን በመገናኛ ብዙኃን ዘንድ ብዙም ትኩረት አላገኘም። ይህ የሆነበት ምክንያት ምን ይሆን?

ከሚኒያፖሊስ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተመረጠችው ትውልደ-ሶማሊያዊቷ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባሏ፣ ኢልሃን ኦማር፣ እስራኤል በዩ.ኤስ. አሜሪካ የውጭ ፖሊሲ ላይ እያሳረፈች ስላለችው ተጽዕኖ በኮንግሬስ ውስጥ በምታደርገው ንግግር የመነጋገሪያ ርዕስ ሆና ቆይታለች። ያም ሆኖ፣ አሜሪካ አፍሪቃን በተመለከተ በምትከተለው ፖሊሲ ዙሪያ እያቀረበች ያለችው አስተያየት እምብዛም የብዙኃን መገናኛዎችን ትኩረት ሳይስብ ቀርቷል።

### የአሜሪካውያኑ ባለሥልጣናት ኤርትራ ጉብኝት

ኦማር በመጋቢት 2019 (እ.አ.አ.) መግቢያ ኤርትራን የጎበኘችው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባሏ፣ ካረን ባስ፣ ከተመራው የዩ.ኤስ. አሜሪካ ኮንግሬስ ልዑካን ቡድን ጋር ነበር። ከቀሩት የልዑካን ቡድኑ አባላት መካከል፣ ከኮሎራዶ ግዛት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአባልነት የተመረጡት ትውልደ-ኤርትራዊው፣ ጆ ንጉሠ፣ አንዱ ናቸው።

ካረን ባስ በዩ.ኤስ. አሜሪካ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በውጭ ጉዳይ ኮሚቴ የአፍሪቃ፣ የዓለም ዓቀፍ ጤና፣ የዓለም ዓቀፍ ሰብዓዊ መብቶች እና ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ንዑስ ኮሚቴ ሊቀ-መንበር ናቸው። ስለዚህም፣ ወደኤርትራ ያመራው የዩ.ኤስ. አሜሪካ የልዑካን ቡድን ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም።

የዋሽንግተን አስተዳደር ይህን መሰሉን ከፍተኛ የልዑካን ቡድን ወደኤርትራ የላከው በአሁኑ ወቅት በአፍሪቃ ቀንድ ባለው ተለዋዋጭ ጂኦፖለቲካ እና የዓለማች ኃያላን ሀገራት በክልሉ እያደረጉት ባለው ፉክክር ምክንያት ሳይሆን እንደማይቀር የብዙዎች ግምት ነው፤ ይህም ሁኔታ ላለፉት 27 ዓመታት ኤርትራን ለመሩት ፕሬዚዳንት ኢሳይያስ አፈወርቂ እና ለአገዛዛቸው አንድ ተጨማሪ የድጋፍ መግለጫ ሊሆን ይችላል። በእርግጥ፣ ከዩ.ኤስ. አሜሪካው የልዑካን ቡድን ተጠቃሚው ወገን ማን እንደሚሆን ግልጽ አይደለም፤ ከጉብኝቱ በቀዳሚነት የሚጠቀሙት ዩ.ኤስ. አሜሪካ፣ ኤርትራ፣ አሊያም የኤርትራ ኃያሏ አጐራባች ሀገር፣ ኢትዮጵያ፣ እንደሚሆኑ ግን፣ ምንም ጥርጥር የለውም።

በባሕር ማዶ በስደት የምንገኝ ኤርትራውያን፣ ጉብኝቱ ትውልደ-ሶማሊያዊቷ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል፣ ኦማር፣ ስለእስራኤል የሰጠችው አስተያየት በብዙኃን መገናኛዎች ያገኘውን ያህል ትኩረት ይስባል የሚል እምነት የለንም።

ኦማር በትዊተር ገጿ ስለጉብኝቱ ባሰፈረችው አስተያየት፣ "ከጥቂት ዐሥርተ-ዓመታት በኋላ ኤርትራን የጎበኘ የመጀመሪያ የዩ.ኤስ. አሜሪካ የልዑካን ቡድን ነው" ብላለች። ቀደም ሲል እንደተገለጸው፣ ጉብኝቱ ከ14 ዓመታት በኋላ የመጀመሪያው ነው። ዩ.ኤስ. አሜሪካ በአሁኑ ግዜ ጉቡኝቱን ያደረገችው በአፍሪቃ ቀንድ ያላትን የዋነኛ አጋሯን፣ ኢትዮጵያ፣ ፈለግ ተከትላ ሊሆን ይችላል።

የኦማር በልዑካን ቡድኑ ውስጥ መካተት ትልቅ ትርጉም አለው። የአፍሪቃ ቀንድ ሀገር በሆነችው ሶማሊያ የተወለደችው ኦማር፣ ከቤተሰቧ ጋር ወደ ዩ.ኤስ. አሜሪካ የተሰደደችው ኬንያ በሚገኝ አንድ የስደተኞች ካምፕ በኩል ነበር። በቀጣይነትም፣ በዐሥራዎቹ የዕድሜ ክልል ውስጥ እያለች ኑሮዋን በሚኒያፖሊስ ከተማ አድርጋለች። ኦማር በዩ.ኤስ. አሜሪካ ኮንግረስ ውስጥ ባሳለፈችው አጭር ጊዜ ከጥቂት የዋሽንግተን አስተዳደር የውጭ ፖሊሲ ተቺዎች መካከል አንዷ ሆና ብቅ ብላለች። ይሁን እንጂ፣ የኤርትራ ጉብኝቷ ከዚህ ለየት ያለ ትርጉም ያለው ይመስላል።

ኦማር በኤርትራ ጉብኝቷ በትዊተር ገጿ ስለኤርትራ ቆይታዋ የተድበሰበሰ መልዕክት አስተላልፋለች። ከዚህ በተጨማሪም፣ የልዑካን ቡድኑ አባል በመሆኗ የተሰማትን ደስታ ገልጻለች። ኦማር በትዊተር ገጿ ያሰፈረችውን አስተያየት ያጠናቀቀችው፣ "ለሰላም እና ለፍትሕ የምታገለው፣ የሰላምን ጣዕም የሚያውቁት የጦርነትን ገፈት የቀመሱት ብቻ ስለሆኑ ነው" በማለት ነው።

የልዑካን ቡድኑ መሪ ካረን ባስ በበኩላቸው፣ ፕሬዚዳንት ትራምፕ ከሰሜን ኮሪያው አምባገነን መሪ ጋር ተገናኝተው መነጋገራቸውን የተቃወሙ ናቸው። ኤርትራ ደግሞ፣ "የአፍሪቃ ሰሜን ኮሪያ" በሚል መጠሪያ በተደጋጋሚ ስትጠራ ቆይታለች። ይህን መጣረዝ የተመለከቱ ጥቂት የማይባሉ ኤርትራውያን ደግሞ፣ ባስ የአፍሪቃ ሰሜን ኮሪያ ወደሆነችው ኤርትራ ያመራውን የልዑካን ቡድን በመምራታቸው፣ የወቀሳ ቃላት ሰንዝረውባቸዋል።

ወላጆቻቸው በወቅቱ በኢትዮጵያ ቁጥጥር ሥር ከነበረችው ኤርትራ በ1980 (እ.አ.አ.) የተሰደዱት ጆ ንጉሠም እንዲሁ፣ በጉብኝቱ ዙሪያ ብዙም ያሉት ነገር የለም። እንዲያውም፣ ባስ ፊርማቸውን ባኖሩበት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ፣ "በአፍሪቃ ቀንድ ክልል በሰላም፣ በጸጥታ፣ በሰብዓዊ መብቶች እና በዴሞክራሲያዊ ለውጦች ዙሪያ ከሥራ ባልደረቦቼ እና ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ጋር እወያያለሁ" የሚል ጽሑፍ አክለውበታል።

የኤርትራ የማስታወቂያ ሚኒስትር፣ የማነ ገብረ መስቀል፣ የትዊተር ገጽ፣ የካረን ባስ ጋዜጣዊ መግለጫ እና የኤርትራ መንግሥት ሌሎች ባለሥልጣናት የትዊተር መልዕክቶች እንዳስታወቁት፣ የልዑካን ቡድኑ አባላት ከኤርትራ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ጋር "ተከታታይ ውይይቶችን" አድርገዋል።

ባስ ወደ ዩ.ኤስ አሜሪካ ባደረጉት የመልስ ጉዞ በአዲስ አበባ በኩል ሲያልፉ፣ ጉብኝቱን አስመልክተው ከአሶሲየትድ ፕሬስ የዜና ወኪል ጋር ቃለ-ምልልስ አድርገው ነበር። ባስ በዚሁ ወቅት በሰጡት አስተያየት፣ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር የገባችበትን ፍጥጫ ከፈታች ወዲህ እምብዛም ለውጥ ያላሳየች "ምሥጢራዊ ሀገር" ናት ብለዋል። ያም ሆኖ፣ በእስር ላይ የሚገኙ የቀድሞ የዩ.ኤስ. አሜሪካ ኤምባሲ ሠራተኞችን ጨምሮ፣ "ሌሎች በእስር ላይ የሚገኙ ግለሰቦች" በቅርቡ እንደሚለቀቁ ያላቸውን ተስፋ ገልጸዋል።

ኤርትራ ውስጥ ነጻ ሚዲያ ባለመኖሩ፣ በተለይም በኤርትራ መንግሥት በኩል ምንም ዓይነት ጋዜጣዊ መግለጫ ባለመሰጠቱ፣ ስብሰባዎቹ በምን ጉዳይ ዙሪያ እንዳጠነጠኑ አይታወቅም። የኤርትራ መንግሥታዊ ብዙኃን መገናኛም ቢሆን በጉዳዩ ዙሪያ ዝምታን መርጧል። ከማስታወቂያ ሚንስትሩ የትዊተር መግለጫ በስተቀር፣ የኤርትራ መንግሥት ስለስብሰባዎቹ ምንም ዓይነት ፍንጭ አልሰጠም። በዚሁ ጊዜ ኤርትራን የጎበኘ አንድ የፈረንሳይ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የልዑካን ቡድንም ቢሆን፣ ከማስታወቂያ ሚኒስትሩ የትዊተር መልዕክት በስተቀር ሌላ መግለጫ አልተሰጠበትም። ይሁን እንጂ፣ በወቅቱ አንድ የሩሲያ የልዑካን ቡድን ጉብኝት ሰፊ የመንግሥታዊ ሚዲያ ሽፋንን አግኝቷል።

### ኤርትራ እና ሌሎች የአፍሪቃ ሀገራት

በአንጻሩ፣ በመንግሥታዊ ብዙኃን መገናኛዎች ሰፊ ሽፋን እያገኘ የሚገኘው ፕሬዚዳንት ኢሳይያስ አፈወርቂ

ወደ 20 ዞሯል



የአሜሪካ ልዑካን በአስመራ



ፕሮፌሰር አሊ ቨርጂ
አሜሪካ ሰላም ኢንስቲትዩት
የአፍሪቃ ጉዳዮች አማካሪ



ተባባሪ ፕሮፌሰር ፔይተን ኖፕፍ እና
አሜሪካ ሰላም ኢንስቲትዩት
የአፍሪቃ ጉዳዮች አማካሪ

# "ኢትዮጵያ ወደቀድሞው አፋኝ ሥርዓት አትመለስም ከሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ጊዜው አሁን አይደለም"

የ42 ዓመቱ ፖለቲከኛ፣ ዐቢይ አሕመድ፣ አዲሱ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ከሆኑ አንድ ዓመት አልፏቸዋል። ዐቢይ የመራሄ መንግሥትነትን ሥልጣን የጨበጡት 105 ሚሊዮን ያህል ሕዝብ ያላት ኢትዮጵያ በተለያዩ ብሔሮች መካከል በተፈጠሩ ግጭቶች በታመሰችበት እና ለበርካታ ዓመታት በሕዝቡ ዘንድ ሲንተከተኩ የቆዩ ቅሬታዎች በገነፈሉበት ወቅት ነበር። አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር የሥልጣን እርካቡን እንደተረከቡ የተለያዩ የለውጥ እርምጃዎችን ወስደዋል። ያም ሆኖ፣ ሀገሪቷ አሁንም ድረስ ለሦስት ዐሥርተ-ዓመታት እየተንከባለሉ ከመጡ ተግዳሮቶች ካለመላቀቋም ባሻገር፣ እነኝህ ችግሮች የሀገሪቷን ህልውና አደጋ ላይ ሊጥሉት እንደሚችሉ አንዳንድ የፖለቲካ ታዛቢዎች ሥጋታቸውን እየገለጹ ነው። የዩ.ኤስ. አሜሪካ ሰላም ኢንስቲትዩት በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ከተቋሙ የአፍሪቃ ጉዳይ አማካሪዎች ፔይተን ኖፕፍ እና አሊ ቨርጂ ጋር አጭር ቆይታ አድርጓል። እኛም ይህንኑ ቃለ-ምልልስ ወደአማርኛ በመመለስ ለአንባቢያን አቅርበነዋል።

**ጥያቄ፦ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ሥልጣን ከያዙ ወዲህ በሀገሪቷ ምን ዓይነት ተጨባጭ ለውጦች ታይተዋል?**

**ቨርጂ፦** የፖለቲካ ተንታኞች በአብዛኛው የሚያቀርቡት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥልጣን እንደያዙ ያስመዘገቧቸውን ውጤቶችን ነው፤ ከእነኝህ የለውጥ እርምጃዎች መካከል፣ የፖለቲካ እስረኞች መፈታት፣ ከኢትዮጵያ ቀንደኛ ጠላት፣ ኤርትራ፣ ጋር የተደረሰው ዕርቅ፣ በሲቪል ማህበረሰቡ ላይ ተጥሎ የቆየው ገደብ መነሣት፣ እንዲሁም ሴቶችን በተመጣጠነ መልኩ በመንግሥት ከፍተኛ የኃላፊነት ቦታ ላይ ማስቀመጥ ዋነኞቹ ናቸው። እነኝህ የለውጥ እርምጃዎች በሚሊዮኖች ለሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ጠቃሚ እና አስፈላጊ መሆናቸው ምንም አያጠያይቅም።

ይሁን እንጂ፣ በቅርቡ አንዲት ኢትዮጵያዊት ወዳጄን በሕይወቷ ላይ ከፍተኛ ለውጥ ያመጣው የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢያ እርምጃ ምን እንደሆነ ላቀረብኩላት ጥያቄ የሰጠችኝ ምላሽ፣ መንግሥታዊው ኢትዮ-ቴሌኮም ኩባንያ በመስከረም 2018 (እ.አ.አ.) በስልክ ጥሪ ላይ ያደረገው የተመን ማሻሻያ እንደሆነ ነግራኛለች። የወዳጄ ምላሽ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ለውጥ ሁለት ገጽታዎች የሚያሳይ ነው፤ በፖለቲካው መስክ ፈጣን ለውጦች እንደተመዘገቡ ሁሉ፣ ከፍተኛ ድኽነት እና የሀብት አለመመጣጠን ባለባት ሀገር ውስጥ ኢኮኖሚያዊ ማሻሻያዎችም ትልቅ ትርጉም አላቸው።

በእርግጥ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚህ አንድ ዓመት ውስጥ ሊጨበጨብላቸው የሚገቡ ለውጦች እውን ሆነዋል፤ ይሁንና፣ በአሁኑ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሽግግር አንዳንድ ምቾት የሚነሡ ነገሮች ተስተውለዋል። በመጀመሪያ ደረጃ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ፈጣን የለውጥ እርምጃዎችን መውሰድ የቻሉት የፈለጉትን ውሳኔ ያለምንም ተቀናቃኝ ተግባራዊ ማድረግ ስለሚችሉ ነው። የጠቅላይ ሚኒስትሩ አሠራር፣ በተወሰነ መልኩ በዙሪያቸው የሚገኙ ሌሎች ፖለተከኞችን ሳያማክሩ ያሻቸውን ውሳኔ እንደሚያስተላልፉ ጠቋሚ ነው። የጠቅላይ ሚኒስትሩ ውሳኔዎች ብዙ ውጤቶችን ሊያስከትሉ ቢችሉም፣ ዘላቂነት የሌላቸው ይመስላሉ።

በሁለተኛ ደረጃ፣ ለውጡ ሁሉንም የኅብረተሰቡን ክፍል ያቀፈ አይደለም። በተለያዩ የብሔር ቡድኖች መካከል በተካሄዱ ግጭቶች ለውጡ ዕንቅፋት ገጥሞታል፤ ለምሳሌ ያህል፣ በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልል በሚገኘው የጌዴዎ ዞን እና በአዋሳኙ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል በሚገኘው የምዕራብ ጉጂ ዞን መካከል በተፈጠረው ግጭት ብቻ 620,000 ኢትዮጵያውያን ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል። በመላው ሀገሪቷ ደግሞ፣ ከሁለት ሚሊዮን የሚበልጡ ዜጎች ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል።

**ኖፕፍ፦** ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በውጭ ፖሊሲያቸውም ዙሪያ አዲስ አካሄድ መከተልን መርጠዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወደሥልጣን ከመጡ ወዲህ ባለው አንድ ዓመት የተለያዩ የዓለማችንን ሀገራት ጐብኝተዋል። ባለፈው አንድ ወር ውስጥ ብቻ የአፍሪቃ ቀንድ ሀገራትን አዳርሰዋል፤ በዚህም ጉብኝታቸው የኤርትራው ፕሬዚዳንት ሁለት ጊዜ ከጐናቸው የነበሩ ሲሆን፣ የተባበሩት ዐረብ ኤሚሬቶችን እና ኳታርን ጐብኝተዋል። ዳሩ ግን፣ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ዲፕሎማሲያዊ ጥረቶች እንዴት እንደሚቀናጁ ግልጽ አይደለም።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በኢትዮጵያ፣ በኤርትራ እና በሶማሊያ መካከል የተፈጠረው አዲስ አጋርነት የክልሉ ፖለቲካ እና ኢኮኖሚ ማዕከል እንደሆነ ተናግረዋል፤ ይሁንና፣ ይኸው አጋርነት ምን ያህል ውጤታማ እንደሚሆን እና ኢትዮጵያ ግብጽ፣ ሱዳን፣ ኡጋንዳ እና የተባበሩት ዐረብ ኤሚሬቶች ከመሰሉ ሌሎች የክልሉ ተዋናዮች ጋር በሚኖራት ግንኙነት ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ በጊዜ ሂደት የሚታይ ይሆናል።

የአፍሪቃ ቀንድ ቢያንስ ለአንድ ትውልድ ለሚሆን ጊዜ በክልሉ መጻኢ ዕጣ ፈንታ ላይ ወሳኝ በሆነ የለውጥ ጊዜ ላይ ይገኛል። በኢትዮጵያ የታየው የፖለቲካ ሽግግር፣ የሱዳን መፈንቅለ-መንግሥት እና ሕዝባዊ ንቅናቄ፣ የፋርስ ባሕረ-ሰላጤ ሀገራት በክልሉ እየተጫወቱ ያለው ሚና የዚህ ለውጥ አንድ ቁልፍ አካል ናቸው። እዚህ ላይ አንድ ነገር በእርግጠኝነት ማስቀመጥ ይቻላል፤ የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ሽግግር የሚከተለው አካሄድ፣ በአጭር እና ረዥም ጊዜ የአፍሪቃ ቀንድ መረጋጋት እና ደኅንነት ላይ ወሳኝ ከሆኑ ነገሮች መካከል አንዱ ነው።

**ጥያቄ፦ ኢትዮጵያ እና ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በቀጣይነት ሊፋጠጧቸው የሚችሉ ተግዳሮቶች ምንድን ናቸው?**

**ኖፕፍ፦** ሀገሪቷን እና ጠቅላይ ሚኒስትሩን ወደፊት ሊፋጠጧቸው ከሚችሉ ተግዳሮቶች መካከል ይበልጥ አንገብጋቢዎቹ፣ ከደኅንነት እና ከኢኮኖሚ ጋር የተያያዙ ናቸው። ቀደም ሲል እንደተገለጸው፣ በአብዛኛው በፖለቲካዊ ሁከት ሳቢያ ባለፈው ዓመት ከቤት ንብረቱ የተፈናቀለው ሕዝብ ብዛት፣ እንዲሁም 150,000 ኢትዮጵያውያን በጦርነት እየታመሰች ወዳለችው የመን መሰደዳቸው ከባድ የማስጠንቀቂያ ደወሎች ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም፣ በተለያዩ የሀገሪቷ ክፍሎች የተደራጁ ሚሊሺያዎች እጅ እየገባ ያለው የሕገ-ወጥ ጦር መሣሪያ ብዛት ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ መምጣቱ አሳሳቢ ነው።



በማንኛውም ፖለቲካ ሽግግር ወቅት እንደሚስተዋለው፣ ኢትዮጵያም ውስጥ ያሉት አደጋዎች እና መልካም ዕድሎች ብዙ ናቸው። በኢትዮጵያ ያለውን የለውጥ እርምጃ ፍጥነት እና መጠን፣ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ጥረት፣ እንዲሁም የሀገሪቷን የቆዳ ስፋት እና ውስብስብ ገጽታ ስንመለከት ደግሞ፣ አደጋዎቹ እና መልካም ዕድሎቹ በዚያው መጠን ብዙ እንደሚሆኑ እንረዳለን። አንድ በቅርቡ የወጣ ሐተታ እንዳስነበበው፣ በእርግጥም "ታፍና የቆየችው ኢትዮጵያ ፋታ አግኝታለች።"

ይሁን እንጂ፣ መሠረታዊ የመንግሥት አወቃቀርን፣ በፌደራሉ መንግሥት እና በክልሎች መካከል ያለውን ግንኙነት፣ በመንግሥት እና በኢኮኖሚው መካከል ያለውን ግንኙነት፣ እንዲሁም በተለያዩ ማኅበረሰቦች መካከል ያለውን ግንኙነት በመሰሉ መሠረታዊ ጥያቄዎች ዙሪያ በኢትዮጵያውያን መካከል መግባባትን በሚፈጥር መልኩ ምላሽ የሚሰጥ ዝርዝር ዕቅድ ስለመኖሩ ግልጽ አይደለም። በተለይም፣ በአሁኑ ወቅት ሀገሪቷ ውስጥ ያለው ሰላማዊ የሥልጣን ፉክክር ሕጎች እና አሠራሮች እምብዛም ባልዳበሩበት ሁኔታ፣ በ2020 (እ.አ.አ.) ሊካሄድ የታቀደውም ሆነ ቀጣይ ምርጫዎች ላይ ችግር ሊፈጥሩ ይችላሉ።

የፖለቲካ ሽግግሩ ስኬታማ እንዲሆን ከተፈለገ፣ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የሚመራው መንግሥት በሀገሪቷ ውስጥ ካለው ጥልቅ እና ለረዥም ጊዜ ከዘለቀው የብሔር ክፍፍል መላቀቅ እና ለሁሉም የኢትዮጵያ ዜጎች ደኅንነት ዋስትና መስጠት ይጠበቅበታል። የሀገሪቷን ስፋት ውስብስብነት ግምት ውስጥ ካስገባን፣ ይህን ማድረጉ ቀላል እንደማይሆን ይታወቃል፤ ይሁንና፣ እነኝህን ነገሮች በኃላፊነት ስሜት ማከናወኑ ለሀገሪቷ የግዛት አንድነት እና ሀገሪቷ በተረጋጋ እና በብልጽግና

ወደ 21 ዞሯል



# “ዓላማችን ማህበራዊ ፍትህን ማስፈን ነው”

## አቶ የሺዋስ አሰፋ
## የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ - ፍትህ ፓርቲ ሊቀመንበር

**ባለፈው ሳምንት አርበኞች ግንቦት 7፣ ሰማያዊ ፓርቲና ሌሎች አምስት ፓርቲዎች እራሳቸውን በማክሰም፣ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ - ፍትህ ፓርቲን መስርተዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል የሰማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር የነበሩት አቶ የሺዋስ አሰፋ የአዲሱ ፓርቲ ሊቀመንበር፣ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የፓርቲው መሪ ሆነው ተመርጠዋል፡፡ ይህንና ሌሎች ጉዳዮችን አስመልክተን ከአቶ የሺዋስ ጋር ቆይታ አድርገናል፡-**

**ኢትዮጲስ፡- ኢዜማ፣ በአዲሱ አደረጃጀቱ መሪና ሊቀመንበር ሰይሟል፡፡ በመሪና በሊቀመንበር መካከል ያለውን ልዩነት ቢያብራሩልን?**

**አቶ የሺዋስ፡-** የኢዜማ ዋና ዓላማ፣ ከዚህ በፊት ከነበረው አደረጃጀት ተለይቶ፣ የፖርቲ ስልጣን ከመንግስት የተለየ እንዲሆን ታስቦ የተሰራ ነው፡፡ በአውሮፓና በአሜሪካ የ100 እና 200 ዓመት ዕድሜ ባላቸው ፓርቲዎች፣ በመሪና ሊቀመንበር (Leader and Chairmanship) መካከል ያሉ ልዩነቶች በግልፅ የተቀመጠ ነው፡፡ ይህ መሆኑ የሚያመላክተው፣ አንደኛ፣ መንግስት ለመሆን የተዘጋጀን መሆኑን፤ ሁለተኛ ደግሞ፣ ከዚህ በፊት የምንወቅሳቸው፣ በወያኔም ጊዜ ቢሆን፤ በግለሰብ፣ በድርጅቱና በመንግስት መካከል ግልፅ የሆነ ልዩነት የለም ላልነው መልስ የሚሰጥ ነው፡፡

በአዲሱ አደረጃጀት የፓርቲው መሪ ፖለቲካውን የበላይ ሆኖ ይመራል፤ የድርጅቱ የዕለት ተዕለት ሥራ ውስጥ ግን አይገባም፡፡ የድርጅቱን የዕለት ተዕለት ስራ ማከናወን የሊቀመንበሩ ድርሻ ነው፡፡ ሊቀመንበሩ የመንግስት መዋቅር ላይ ያለ ሰው መሆን አይችልም፡፡ ሁለቱ ግልፅ ልዩነቶች አሏቸው፡፡

በየወረዳውና በየዞኑ ባሉን መዋቅሮች፣ ለአባላትና ደጋፊዎች በደንብ ማብራራት ይጠበቅብን ይሆናል፤ የተባለው አዲስ ነው፤ አዲስ የሆነው ግን ለእኛ ሀገር ነው፡፡ ስለዚህ፣ ሁለቱ መስመሮች፣ ማለትም፣ የመንግስትና የፖለቲካ መስመሮች፣ በሌሎችም ፓርቲዎች መለመድ አለባቸው የሚል እምነት ነው ያለን፡፡

**ኢትዮጲስ፡- መንግስት ለመሆን የምታደርጉት እንቅስቃሴ ምን ይመስላል?**

**አቶ የሺዋስ፡-** የተወካዮች ምክር ቤቱ 547 መቀመጫዎች ናቸው ያሉት፡፡ አሁን ባለንበት ደረጃ፣ ከ547ቱ 312 ደርሰናል፡፡ ምርጫ ዛሬ ይደረግ ቢባል እንኳ፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ አማራጭ ሆነን የመቅረብ አቅም አለን ብለን እናስባለን፡፡ እንዳሰብነው ከሆነ፣ ራሱን የቻለ የእጩዎች ምክር ቤት ይኖራል፤ በትይዩ ጥላ ካቢኔት (Shadow cabinet) የሚባልም አደረጃጀት ይኖረናል፡፡

ይህ መሆኑ፣ “ኢህአዴግ ከፈረሰ ሀገር ትበተናለች” የሚለውን ስጋት ለመቅረፍ የሚረዳ ነው፡፡ ምክንያቱም፣ ህዝቡ ይህንን ስራ ከተመለከተ፣ እጩዎችን ካየ፣ ጥላ ካቢኔውን ካየ፣ “ይሄኛው ፓርቲ ቢሄድም፣ ይሄኛው አለ” ብሎ እንዲተማመን ያደርጋል፡፡ ዴሞክራሲ ባለባቸው ሀገራት የተለመደ አሠራር ነው፡፡ መንግስት ለመሆን ሀሳብ ያላቸው ፓርቲዎች፣ በዚህ ደረጃ ነው መዘጋጀት ያለባቸው፡፡

**ኢትዮጲስ፡- ምርጫው ይራዘም ያላችሁበት ምክንያት ምንድን ነው?**

**አቶ የሺዋስ፡-** ምርጫ፣ ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ፣ በህዝብ ተቀባይነት ያለው፣ የስልጣን ሽግግር የሚያደርግበት ነው፡፡ ከምርጫ በፊት የሚያስፈልጉ ነገሮች አሉ፤ ለምሳሌ፣ ሀገርና ህዝብ ሙሉ በሙሉ መረጋጋት አለበት፤ በመንግስት በኩል ደግሞ፣ ክትትልና ቁጥጥር (Check and control) ያስፈልገዋል፤ መንግስት የህዝብን ሰላምና ደህንነት የማስጠበቅ ግዴታውን መወጣት አለበት፡፡ ከዚህ በተረፈ፣ ተቋማት ላይ የምንነጋገራቸውና የምናስተካክላቸው ነገሮች ማለቅ አለባቸው፡፡ እነዚህ ነገሮች ሲያልቁ ነው ምርጫ መደረግ ያለበት፡፡

“ምርጫው ነገ ይደረግ ቢባል እንኳን፣ ዝግጁ ነን” ያልኩት፣ ዝግጁነታችንን ለመግለፅ ነው እንጂ፣ አሁን ሀገሪቱ ባለችበት ሁኔታ፣ ስልጣን ወይም ማሸነፍ የመጀመሪያ ዓላማችን አይደለም፡፡ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር እንድትቀጥል፣ ህዝብ በሀገሩ ላይ ሳይሸማቀቅና ሳይፈራ፣ በሰላም ወጥቶ መግባትና መኖር እንዲችል፤ የተጀመረው የለውጥ ሂደት ሳይቀለበስ፣ ሳይበላሽ፣ ህዝብ ሳይጎዳ በስርዓት መሄዱን ነው ቅድሚያ የምንሰጠው፡፡ ሀገር ላይ፣ ሀገራዊ እርቅ እንዲወርድ ማድረግ፣ ሠላምና መረጋጋት እንዲኖር በማድረግ፣ ሂደቱ ተቋማዊ እንዲሆን ማድረግ ዋና ዋና ነገሮቹ ናቸው፡፡ ከዚህ በኋላ ነው ምርጫው መምጣት አለበት ብለን የምናስበው፡፡

**ኢትዮጲስ፡- ምርጫ መደረግ አለበት የምትሉትን ጊዜ ቆርጣችኋል ? ወይስ ቀነ ገደብ አላስቀመጣችሁም? ሀገር የምትረጋጋው መቼ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? መንግስት እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ፣ “ሀገር እንዲረጋጋ መታገስ አለብን” እያለ ነው?**

**አቶ የሺዋስ፡-** ብዙ ጊዜ “የለውጥ ኃይል” ሲባል ለተወሰነ ወገን ይሰጣል እንጂ፣ ለዚህ ትግል አስዋጽኦ ያደረገ ሰው በሙሉ የለውጥ ኃይል ነው፡፡ ሰላምና መረጋጋት ይመለከተዋል፣ ዕርቀ ሰላም ይመለከተዋል፣ ምርጫ መቼ መደረግ አለበት? የሚለው ላይም፣ ሽግግሩ መቼ ማለቅ አለበት? በሚሉት ጥያቄዎች ዙሪያ በሙሉ የለውጥ ኃይሉ ስምምነት ላይ መድረስ አለበት ብለን እናምናለን፡፡ ስለዚህ፣ ይህን ለማድረግ ቁጭ ብለን እንነጋገር ነው የምንለው፡፡ ዝም ብሎ የምርጫው ቀን ተጠብቆ፣ ይዋጣልን ዓይነት ነገር ትክክል አይደለም፡፡ ከምርጫው በፊት ቁጭ ብለን መነጋገር አለብን፡፡

መንግስት ትዕግስተኛ መሆን አለበት፡፡ አንዳንዴ፣ “እርምጃ ለምን አይወስድም?” ሲባል ይገርመኛል፤ ከዚህ በፊት ስንታገል የነበረው፣ እርምጃ ሳይጣራ እንዳይወስድ ነው፡፡ ማንኛውም ሰው በህግ አግባብ ካልሆነ በስተቀር እንዳይያዝ፣ ቤቱ እንዳይፈተሽ፣ መጉላላት እንዳደርስበት ነው፡፡ በሌሎች ሀገሮች፣ አንድ ንፁህ ሰው ከሚያዝ ብዙ ወንጀለኞች ቢያመልጡ ይመረጣል ይላሉ፡፡ እኛጋ

ወደ ቀጣዩ ገጽ 13

ደግሞ፣ "አንድ ሰው ከሚያመልጥ፣ የማይመለከታቸው ብዙ ሰዎች ይጎዱ" የሚል አመለካከት አለ።

መንግስት እርምጃ እንዲወስድ የሚፈልጉ ሰዎች፣ በመረጡት ላይ ብቻ ይሆናል በሚል እሳቤ ነው፣ ብዙ ጊዜ ግን፣ እርምጃው ሲወሰድ እንደተባለው አይደለም። "ትዕግስት በዛ፣ እርምጃ ይወሰድ" የሚሉ ነገሮች የሚመከሩ አይደሉም። እንደውም፣ በተቃራኒው፣ ህዝብ በስርዓት መሄድ አለበት፤ መንግስት ደግሞ፣ በትእግስት ኃላፊነቱን መወጣት አለበት። ይህ ሲባል ግን፣ ጥፋቶችን የፈጸሙ ላይ በህግ አግባብ እርምጃ ተወስዶ መማሪያ አይሁኑ ማለት አይደለም።

**ኢትዮጲስ፡- የተራዘመው የህዝብና ቤት ቆጠራው መቼ መደረግ አለበት ትላላችሁ?**

**አቶ የሺዋስ፡-** ከምርጫው በፊት መደረግ ካለባቸው ነገሮች አንዱ ነው እንላለን። በመጀመሪያ፣ እንደ ሀገር ቅራኔ የገባንባቸው ነገሮች የሚፈቱበት ብሄራዊ ዕርቅ ወይም ሀገራዊ እርቀ ሰላም መደረግ አለበት ብለን እናምናለን። ከህዝብና ቤት ቆጠራ ቀድሞ መደረግ አለበት ብለን እናምናለን። የለውጡ ተቋማዊነት፣ እስከታች ድረስ በትክክል መረጋገጥ አለበት ብለን እናምናለን። ከሁሉም በላይ ግን፣ ሠላምና መረጋጋት ሀገሪቱ ላይ መኖር አለበት ብለን እናምናለን። እነዚህ ሳይኖሩ ስለምርጫ ማውራት፣ ባለ ችግር ላይ ሌላ ችግር እንደመጨመር ነው።

**ኢትዮጲስ፡- ሶስት ሚሊዮን ገደማ ኢትዮጲያውያን ተፈናቅለው ቆጠራው ከተካሄደ፣ እጣ ፋንታቸው ምን ይሆናል፣ እንዴት ነው የሚቆጠሩት?**

**አቶ የሺዋስ፡-** ይህ እንደ ሀገር የሚያሳፍረን፣ የሚያሸማቅቀን ነው። ሌላ ጠላት ሳይመጣ፣ የገዛ ወገኖቻችንን እራስ በራስ መጠቃቃት በጣም የሚያሸማቅቅ ነገር ነው። የተፈናቀለው ህዝብ ቁጥር በትክክል ተመዝግቦ መቀመጥ አለበት ብለን እናምናለን።

**ኢትዮጲስ፡- የጌዲዮ ተፈናቃዮችን ለምሳሌ ብንወስድ፣ "ግጭት ወደተፈጠረበት አካባቢ አንመለስም" እያሉ ነው፤ ከምርጫው ወረዳ ጋር በተያያዘ የእነሱ ቆጠራ የት ነው የሚሆነው?**

**አቶ የሺዋስ፡-** ይህ እያለ ስለምርጫ ማንሳት አይገባም። የተፈናቀሉትን ስለመመለስ ስናወራ፣ መጀመሪያ ሰው ሰላማዊ ኑሮ መኖር አለበት። ወደ ቦታቸው መመለሳቸው ከእነጭራሹ ለድርድር የሚቀርብ አይደለም። መጀመሪያ፣ ወደ ቀያቸው ሊያስመልሳቸው የሚያስችል ሰላምና መረጋጋት ኖሮ ነው ቆጠራው መደረግ ያለበት።

**ኢትዮጲስ፡- በኢትዮጵ 547 የምርጫ ወረዳዎች አሉ፡፡ እነዚህ የምርጫ ወረዳዎች፣ ኢህአዴግ ለራሱ በሚጠቅም መልኩ የሸነሸናቸው ናቸው ይባላሉ፡፡ ባሉበት እንዲቀጥሉ ነው የምትፈልጉት? ወይስ እንዲለወጡ ትሻላችሁ?**

**አቶ የሺዋስ፡-** የኢትዮጵያ ችግሮች የተወሳሰቡና ለዘመናት የቆዩ ናቸው። በተለይ ወያኔ ብዙዎቹን አወሳስቦ ነው ያለፈው። አንዳንድ የክልል አወቃቀሮችን ስናይ፣ ለክፋት የተሰሩ ሆነው መዘጋጀታቸው በተደጋጋሚ የተገለፀና የታወቀ ነው። ነገር ግን፣ እኛ አሁን ነገሮችን መቀየር የምንችለው፣ ተመርጠን፣ አሸንፈን ስልጣን ስንይዝ ነው።

ለምሳሌ፣ ፕሬዝዳንታዊ ስርዓት እንዲኖር እንፈልጋለን፤ ይህን ካሸነፍን በኋላ ነው የምናደርገው እንጂ፣ የምንወዳደረው አሁን ባለው ስርዓት ነው። የምርጫ ክፍሎችን በተመለከተ፣ የይስሙላም ቢሆን የ1987፣ የ1992፣ የ1997፣ የ2002ና የ2007 ምርጫዎች የተደረጉባቸው ናቸው። የተያያዝነው ማሻሻል (Re-form) ነው ካልን፣ የነበረውን ጠርገን ጥለን ሌላ ማምጣት ሳይሆን፣ ያሉትን የምርጫ ወረዳዎች ወስደን፣ የሚስተካከለውን እያስተካከልን ነው የምንሄደው ማለት ነው።

**ኢትዮጲስ፡- ካርታው ለተፎካካሪ ፓርቲዎች ቀርቦ ለውይይት ክፍት ሆኖ ያውቃል?**

**አቶ የሺዋስ፡-** ባለፈው ህዳር ወር ይመስለኛል፣ ወይይት ስናደርግ፣ ሁለት መሰረታዊ ጥያቄዎች ተነስተዋል። አንደኛው፣ ውይይቱ ሁሉን አቀፍ ይሁን የሚል ነበር። ያልተመዘገቡ፣ የተመዘገቡ፣ በሀገር ውስጥ ያሉ፣ ከውጭ የመጡ ድርጅቶች ሁሉ ተጋብዘዋል። ይህ የተመለሰ ይመስለኛል። ሁለተኛው፣ አጀንዳዎችን በሚመለከት ነው፤ የማይነሳ አጀንዳ የለም፣ ሁሉም ለውይይት ይቀርባል፣ የምርጫ ስርዓቱን ጨምሮ፣ ህገ መንግስቱም ለውይይት ይቀርባል። በዚህ ሂደት፣ በምርጫ ቦርድ አወያይነት እርማት የሚያስፈልጋቸው ነገሮች ላይ ውይይት ይደረግባቸዋል ማለት ነው። ስምምነታችን ይህ ነው።

**ኢትዮጲስ፡- ከዚህ ጋር በተያያዘ፣ ከዚህ በፊት፣ በድንበር አካባቢ የሚኖሩ 117 ሺህ ገደማ ኢትዮጵያውያን፣ ክልላቸው በግልፅ ስላልተለየ፣ መምረጥ አልቻሉም ነበር፡፡ የእነሱ ጉዳይ ከምርጫ በፊት በውይይቱ ይነሳል?**

**አቶ የሺዋስ፡-** አዎ ይነሳል። አቶ አንዷለም አራጌ እንዳሉት፣ የምርጫ ሂደቱ መራዘም ያለበት እነዚህ ሂደቶች እስከሚያልቁ ነው። አንድ ዓመትም ሆነ ስድስት ወር ይውሰድ፣ ትኩረት ሰጥተን ማስተካከል አለብን የተባለው ለእንደነዚህ ዓይነት ጉዳዮች ነው። ምክንያቱም፣ የአሰፋፈር ጥያቄ እያለ፣ እነዚህ ችግሮች ሳይፈቱ ወደ ምርጫ መግባት፣ ህዝቡን ወደ አልሆነ ነገር መምራት ነው የሚል እምነት አለን። በነገራችን ላይ፣ ውይይቱ ሁሉን አቀፍ ስለሚሆን፣ የማይነሳ አጀንዳ የለም፤ ለሀገር እስከጠቀመ ድረስ፣ ህገ መንግስቱም ቢሆን ለውይይት ይቀርባል፤ ህገ መንግስቱ አማራጭ ሃሳብም ቀርቦበት፣ ለህዝብ ውሳኔ እንዲቀርብ የሚያደርግ ውይይት ነው የሚሆነው ብዬ አምናለሁ።

**ኢትዮጲስ፡- ገለልተኛ መሆን የሚገባቸውን ተቋማት፣ ለምሳሌ፣ የምርጫ ቦርድና የህዝብ ቆጠራ ተቋማት ኃላፊዎችን መንግስት እየሾመ፣ ገለልተኛ ይሆናሉ ብላችሁ ትጠብቃላችሁ?**

**አቶ የሺዋስ፡-** ገና ነው። ለውጡ ተቋማዊ መሆን አለበት ስንል፣ ለምሳሌ፣ ምርጫ ቦርድን ገለልተኛ ማድረግ ማለት፣ ኃላፊውን መቀየር ወይም የቦርድ አባላቱን መቀየር ማለት አይደለም። ድሮም ቢሆን ኮሮጆ የሚገለብጡት እነሱ ብቻ አይደሉም፤ በየወረዳው ያለ ካድሬ ነው፤ ለዚህ ነው በስርዓት ደረጃ እንፍታው ብለን፣ ወደ ምርጫ አንቸኩል የምንለው። እስከ ወረዳ ደረስ ያለው መዋቅር፣ እንዴት ነው ገለልተኛ የሚሆነው? የትኛውን ሀገር ሞዴል ነው የምንወስደው? የሚሉት ጥያቄዎች መመለስ አለባቸው።

ገና ነው፣ የተጀመሩ መልካም ነገሮች አሉ፤ በቅርብ ጊዜ፣ በእነዚህ ተቋማት ተስፋ ሰጭ የሚባሉ ጅምሮች አሉ። ተቋማቱ "ገለልተኛ ናቸው" ብሎ ለመናገር ግን ገና ነው። በጣም ብዙ መሠራት አለበት፤ ይህ የአንድ ፓርቲ ጉዳይ ስላልሆነ፣ ለማሳካት አብረን እየሰራን ነው። የምርጫ ቦርድ አወቃቀርን በተመለከተ፣ በጋራ ሁሉም ፓርቲዎች እየመከሩበት ነው። ከምርጫው በፊት ይህ ሳይስተካከል፣ ስድስተኛ ምርጫ ብሎ ቆጠራ መግባት ተገቢ አይደለም። ስለዚህ ለውጥ አለ ካልንና፣ ተግባራዊ መደረግ አለበት ካልን፣ ቀድሞ መሰራት ያለባቸው ነገሮች ማለቅ አለባቸው። አለበለዚያ፣ ተመሳሳይ ነገር እየሰሩ የተለያየ ውጤት እንደመጠበቅ ነው የሚቆጠረው።


**ኢትዮጲስ፡- ምርጫውን በየት በየት እናሸንፋለን ትላላችሁ?**

**አቶ የሺዋስ፡-** እንደተናገርኩት፣ በ312ቱ ወረዳ ላይ ደርሰናል፣ ሌሎችን ለመሸፈንና በሁሉም በ547ቱ ለመወዳደር ነው ያቀድነው። በሁሉም የሀገራችን ክፍል፣ ዜግነትን የሚያስቀድም ሰው ይመርጠናል ብለን እናስባለን። እኛ፣ መንግስትን በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ለመቀየር ነው የምንታገለው። በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች እናሸንፋለን ብለን እናምናለን። አሁንም የኢትዮጵያዊነት ባህልና ጨዋነት አለ ብለን ነው የምናስበው።

**ኢትዮጲስ፡- ምዕራብ ወለጋን በመሳሰሉ አካባቢዎች እንዴት ለመንቀሳቀስ አስባችኋል?**

**አቶ የሺዋስ፡-** በመጀመሪያ፣ በእነዚህ ቦታዎች ያሉ እንቅስቃሴዎች ከእኛ ጋር የሚወዳደሩ አይደሉም። አንዳንድ ረብሻ የሚፈጥሩ ቡድኖችን፣ ፓርቲዎች ለማለት ያስቸግራል። ፓርቲ ማለት አማራጭ ሃሳብ አቅርቦ፣ ለውድድር የሚቀርብና፣ ድጋፍ ካገኘ የሚያሸንፍ ነው። ሃሳቡን ህዝብ ካልፈለገው አምኖ የሚቀበል እንጂ፣ ዝም ብሎ በየቦታው እየዘረፈ፣ እየተኮሰ የሚንቀሳቀስ ሁሉ ፓርቲ ነው ለማለት ያስቸግራል።

**ኢትዮጲስ፡- እናንተ በዜግነት ነው የምታምኑት፡፡ ህገ መንግስቱ ደግሞ ለብሄሮች ቅድሚያ ይሰጣል፡፡ ይህን እንዴት ትመለከቱታላችሁ?**



**በ312ቱ ወረዳ ላይ ደርሰናል፣ ሌሎችን ለመሸፈንና በሁሉም በ547ቱ ለመወዳደር ነው ያቀድነው፡፡ በሁሉም የሀገራችን ክፍል፣ ዜግነትን የሚያስቀድም ሰው ይመርጠናል ብለን እናስባለን፡፡ እኛ፣ መንግስትን በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ለመቀየር ነው የምንታገለው**

**አቶ የሺዋስ፡-** ህገ መንግስት የተፃፈ ወረቀትና ሰነድ ነው፤ ህዝብ ግን፣ የነበረና የሚኖር ነው። ህዝብ የጣለው ሃሳብ ይወድቃል። የለውጡ አመራሮች የሆኑት፣ እንደ እነ ለማ፣ ደመቀ፣ አዲሱና ንጉሱ ያሸነፉትና ለውጡ እዚህ ደረጃ የደረሰው፣ ኢትዮጵያዊነትን ከፍ አድርገው ስለተነሱ ነው።

ምንም እንኳን ለ27 ዓመታት፣ የመኪና ታርጋና መታወቂያ ላይ እየተለጠፈ የነበረው ሃሳብ፣ ገዢ ሃሳብ እንዲመስል ቢደረግም፣ አሁንም ኢትዮጵያዊነት እንዳለ እንደሚኖር እምነታችን ነው። እኛ ወረቀቱ ላይ ካለው በላይ፣ በስነልቦና ነው የምናምነው። ወረቀቱ ላይ የሰፈረው በሌላ ወረቀት ይቀየራል፣ ለዚህም ውይይት ያደረግበታል፤ መስተካከል ያለባቸው ነገሮች ይስተካከላሉ።

ስያሜው ብሄረሰብ ይባል ማህበረሰብ፣ ዘረኝነት መጥፎ ጉድጓድ ነው፤ ትውልድን ያጠፋል፣ ሌላው ከጉድጓዱ ውጭ ሆኖ ውስጡ ያሉትን መሳብ ነው እንጂ፣ ራሱ እየገባ ማለቅ ያለበት አይመስለኝም። ለምሳሌ፣ ገዢው ፓርቲን ያቋቋሙ አባል ድርጅቶች፤ አዴፓና አዴፓ እያሉ፣ አግላይ ከሆነ ፖለቲካ መራቅ አለባቸው። ከዚህ ሊያወጣቸው የሚችለው የዜግነት ፖለቲካ ነው፤ ህዝቡ ከብሄረሰብ ፖለቲካ ይልቅ፣ ትኩረቱን ወደ ሃሳብ ፖለቲካ ማዞር አለበት፤ ሰሞኑን እንዳሳየው ለዜግነት ፖለቲካ ድጋፍ በመስጠት ከዘር ፖለቲካ ይወጣል ብለን እናስባለን።

**ኢትዮጲስ፡- "በምርጫ ተወዳድረን ስናሸንፍ፣ ፕሬዝዳንታዊ ስርዓት እንመሰረታለን" ያላችሁት በህዝበ ውሳኔ ነው እንዲሆን ያቀዳችሁት?**

**አቶ የሺዋስ፡-** አዎ፣ ሁሉም ነገር በህዝብ ውሳኔ ነው። ይህ ብቻ አይደለም፣ አንድ ፕሬዝዳንት ከ2 ና 3 ክልል ድምፅ ማግኘት አለበት ብለን ስለምናስብ፣ አሁን ካለው አሰራር በተሻለ አሰባሳቢ ይሆናል ብለን እናምናለን። የተሰባጠረ ማህበረሰብ ባለበት ሀገር ይህ ቢሆን ጥሩ ነው። ከዘር ይልቅ ሃሳብ የበለጠ ኃይል እንዲኖረው ያደርጋል።


ከዚህ በተረፈ፣ መሬትም የግል መሆን አለበት ብለን እናምናለን፤ ይህንም ስናሸንፍ ወደ ተግባር የምናመጣው ነው። የገበያ ስርዓቱ፣ የትምህርት፣ የጤና፣ የአካባቢ ጥበቃና ፖሊሲዎቻችንን በሚመለከት ከገዥው ፓርቲ የምንለይባቸው ብዙ ነጥቦች አሉ። ለምርጫ ስንቀርብ እነዚህን ልዩነቶች ወደፊት እናመጣቸዋለን።

**ኢትዮጲስ፡- የምትከተሉት ርዕዮት ዓለም ምንድን ነው?**

አቶ የሺዋስ፡- እንግዲህ አሁን ባለው የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ፣ እንደ ከዚህ በፊቱ፣ ዝምብሎ ጥራዝ ነጠቅ የሆነ ሊዝም፣ ማለት ፌደራ-ሊዝም፣ ሶሻ-ሊዝም፣ ካፒታ-ሊዝም የተባለ ክርክር ውስጥ መግባት ተገቢ አይደለም። ተገቢ የሚሆነው ነገር፣ ተጨባጩን የህዝብ ችግር አጥንቶ፣ ያንን የሚፈታ አስተሳሰብ ይዞ መምጣት ነው።

በእኛ እምነት፣ ኢትዮጵያ፣ በተለያየ ሁኔታ ከመንግስት በመጠጋት በጣም ሀብታም የሆኑ፣ በተቃራኒው ደግሞ፣ ሙልጭ ብለው ድሃ የሆኑ፣ ጫፍና ጫና ላይ ያሉ ዜጎች የሚገኙባት ሀገር ናት። ይህ መስተካከል አለበት፤ ስለዚህ፣ እንደማህበረሰብ እንደ ግለሰብና ቡድን የህዝቦችን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል ተገቢ መሆኑን፣ እናምነበታለን።

ድሃው የሚደገፍበት፣ ሌሎቹ ደግሞ፣ ሀገርን በግብር የሚደግፉበት፣ መንግስት ከግለሰብ ጋር ውድድር ባይገባም፣ አረጋውያንንና አቅመድካሞችን፣ ሴቶችና ወጣቶችን የሚደግፍበት አሰራር እንዲኖር ነው የምንፈልገው፤ ይህንን ነው ማህበራዊ ፍትህ የምንለው።



ገበየሁ ዋለልኝ

ጋዜጠኛና ደራሲ

# ዕለተ ሰቆቀወ ግንቦት 20 ለምን ይከበራል?

ግንቦት 20 -1983 ዓ.ም ኢህአዴግ አዲስ አባን ተቆጣጠረ።እስከ አለፈው ዓመት ድረስም ዕለቱ "የድል በዓል" እየተባለ ሲከበር ቆይቷል። እውን በዓሉ የኢትዮጲያ ህዝብ በዓል ነውን? ህዝቡስ በግንቦት ሀያ የመንግስት ለውጥ ምን አገኘ? መልካም ውጤት ወይስ ውድቀት?



"የኢህአዴግ መንግስት አምባገነን ነው፣ መገለጫውም ምርጫ ማጭበርበር፣ የዲሞክራሲና የፍትህ ጥያቄዎችን ማፈን፣ ንፁሀንን መግደል፣ መግረፍና አካላቸውን ማጉደል መሆኑ በራሱ በድርጅቱ መሪዎች እየተነገረ እያለ፣ ግንቦት 20 ለምን ይከበራል?" ብለው የሚጠይቁ በርካቶች ናቸው። ባለፉት 28 ዓመታት በኢትዮጵያ ውስጥ ሰፍኖ በቆየው ፀረ ዴሞክራሲ ስርዓት፣ በህዝቡ ላይ በተፈፀመው አፈና፣ ጭፍጨፋ፣ አካል ማጉደል፣ እስራትና ግርፋት ምክንያት ዕለቱ እንደ የካቲት 12 የግራዚያኒ ጭፍጨፋ መታሰቢያ ዕለት ታስቦ ነው መዋል ያለበት የሚሉ አስተያየት ሰጪዎችም አሉ።

ግንቦት 20 ቀን አዲስ አበባን ተቆጣጥሮ ምኒልክ ቤተመንግስት ስለገባው ህወሓት ማንነት፣ የቀድሞው አባሉ አቶ ገብረመድህን አርአያ ዋና ዋና ዓላማዎቹን በሶስት ከፍለው አስቀምጠዋቸዋል፡-

1. ትግራይን ከኢትዮጵያ ገንጥሎ የትግራይን ሪፓብሊክ መመስረት
2. ኤርትራን "ከኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት" ነፃ ማውጣትና የራሷን ነፃ መንግስት እንድትመሰረት እስከ መጨረሻው መታገል
3. የኢትዮጲያ "ብሄር ብሄረሰቦችም" ልክ እንደ ትግራይና ኤርትራ እስመገንጠል ድረስ ያላቸው መብት ይከበርላቸዋል ብሎ እርስ በእርስ እንዲናከሱ ማድረግ።

ከእነዚህ ዋና ዋና ዓላማዎች መካከል፣ የመጀመሪያው (ትግራይን ከኢትዮጵያ ገንጥሎ የትግራይን ሪፓብሊክ መመስረት፣) ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ ወደ ስልጣን ከመጡ በኋላ በይፋ ባይታወጅም፣ በመሬት ላይ ግን ከሞላ ጎደል ተግባራዊ ሆኖ ይገኛል፤ ትግራይ አሁን በሀገር ውስጥ ሀገር ሆናለች፤ የማዕከላዊ መንግስቱ አያዛትም፤ ነፃነቷን በይፋ እንዳታውጅ በጉቦ መልክ ከማዕከላዊ መንግስት የበጀት ድጎማው ቀጥሎላታል፤ ህዝቡ ፈለገም አልፈለገም፣ የህወሓት ፍላጎት የክልሉ ፍላጎት ሆኖ ቀርቧል።

ሁለተኛውና ኤርትራን የሚመለከተው ዓላማ (ኤርትራን ማስገንጠሉ፣) ህወሓት ስልጣን እንደወጣ ተግባራዊ ያደረገው ነው። ሆኖም፣ እንዳሰበው፣ ኤርትራ ለትግራይ ደጀን ከመሆኑ ይልቅ በተቃራኒው በጠላትነት ቁመና ላይ ያለች አደገኛ ጎረቤት ሆናለች። እንዲሁም፣ ህወሓት ሁሌም የሚመኘው የትግራይ - ትግሪኝ ጥምረት፣ ከመቼውም ጊዜ በላይ የማይጨበጥ ህልም ሆኖ ይገኛል።

ሶስተኛው ዓላማ (ኢትዮጵያዊያንን መከፋፈሉ፣) የተፈለገውን ያህል ርቀት ባይሄድም፣ የተወጠነለትን ዓላማ በመጠኑም ቢሆን አሳክቷል፤ የህወሓት አገዛዝ ከተገረሰሰ በኋላ የብሄር ግጭቶች ተበራክተዋል። በጥቅሉ፣ የህወሓት ዓላማ ሙሉ ለሙሉ ተሳክቷል ባይባልም፣ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ በአፍራሽ መልኩ አሁንም ድረስ ጉልህ ስፍራ ይዞ ይገኛል።

ግንቦት 20ን አስመልክቶ አስተያየታቸውን ያካፈሉኝ ሰዎች እንዲህ ብለውኛል፡-

## "የሀገር ሀብት የተዘረፈበት ኦፕሬሽን"

### ስፋዬ አበባው፣ የባንክ ሙያተኛ

ህወሐት ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ በኋላ ኢትዮጵያ ለድህነት ተዳርጋለች። "ነፃ አወጣናቸው" ባሏቸው አካባቢዎች የኢኮኖሚ ተቋማትን ዘርፈዋል፣ ባንኮችን፣ የቴሌና የመብራት ኃይል መሣሪያዎችን፣ ጄኔሬተሮችን፣ የህክምና ቁሳቁሶችንና መድሀኒቶችን፣ የወፍጮ ቤት ዕቃወችን፣ የትምህርት ቢቶች ንብረቶችንና የጣራ ቆርቆሮዎችን ሳይቀር ነቅለው ወስደዋል።

እኔ በወቅቱ የመከላከያ ሠራዊት አባል ነበርኩ፣ የያዙትን ቦታ መልሰን አስለቅቀን ስንይዝ፣ አፈራርሰው ዘርፈው ባዶ ሆኖ ነበር የምናገኘው፤ የሆነ ቦታን ሲቆጣጠሩ፣ የሚነቃቀል፣ የሚዘርፍና በፍጥነት ተሸክሞ የሚያጓጉዝ የተደራጀ ክፍል ነበራቸው፣ የኤፈርት የኢኮኖሚ መሠረት የሆነው የዚህ ዓይነቱ ዘረፋ ነው። በግንቦት 20 አዲስ አበባን ከተቆጣጠሩም በኋላ ዘረፋውን ቀጥለውበት ነበር፣ ማታ ማታ መብራት እያጠፉ ሲጭኑ እንደነበር ማንም ያውቃል

የቀድሞው የኢፌዲሪ ፕሬዜዳንት የነበሩትና በቅርቡ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት ዶክተር ነጋሶ ጊዴዳ በበኩላቸው፣ በኦሮሚያ የተካሄደውን መሰል ዘረፋ እንደሚከተለው ገልፀውት ነበር።

"ኦሆዴድ ማዕከሉን ከነቀምት አንስቶ አዲስ አበባ ሲገባ፣ እኛም ወደ አዲስ አበባ ተጓዝን፣ አስታውሳለሁ ዘና ብለን በተለያዩ ከተሞች ያሉ የኦህዴድ ቢሮዎችን እየጎበኘን ነበር የተጓዝነው፣ በየአካባቢው በቆምን ቁጥር፣ ብር የተሞሉ ጆንያዎችን እንጭን ነበር። ያ ብር ከደርግ አባላትና ከተቋማት የተዘረፈ ነበር። ኦህዴድ ብቻ አልነበረም፣ ሻዕቢያና ህወሓትም "የጠላት ገንዘብ" እየተባለ ዘርፈዋል። በተለይ የጦር መሣሪያዎች ወደ ትግራይና ኤርትራ በገፍ ይጫኑ ነበር። በየመንገዱ በጆንያ የተጫነው ገንዘብ ለኦህዴድ እንቅስቃሴ ዋለ። በኋላ ደግሞ፣ ዲንሾ ሲቋቋም የካምፓኒው መመስረቻ ሆኗል። የህወሓት ኤፈርትም በዚህ ሁኔታ በተሰበሰበውና በውጪ እርዳታ ከተገኘ ገንዘብ ነው የተቋቋመው። ኢህዴን ደግሞ 'ጥረት 'የሚባል ነበረው። "በዳንዲ መፅሐፍ ላይ የቀረበ/ገፅ 141

## ግንቦት 20 ኢትዮጲያ የባህር በሮቿን ያጣችበት ዕለት

ስፋዬ አበባው አስተያየታቸውን ይቀጥላሉ፣ "የግንቦት ሀያው ባለ ድል ህወሓት፣ በከፍተኛ ደረጃ የታገለው ኤርትራ ከኢትዮጵያ እንድትገነጠል ነበር።እኛንም ተሃድሶ ብሎ ሲያስተምረን፣ "ኤርትራ የኢትዮጲያ ቅኝ ግዛት ሆና ቆይታለች" ይለን ነበር። እኛ ደግሞ ኤርትራ የኢትዮጲያ አካል፣ ህዝቡም አንድ ህዝብ መሆኑን የታሪክ ሰነዶችን እያጣቀስን እንከራከር ነበር።

ወደ ቀጣዩ ገጽ 15

የቅኝ ገዢን የዕድገት ደረጃ፣ ኢትዮጲያ ከነበረችበት ኋላ ቀር ኢኮኖሚ ጋር እያነፃፀርን እንሞግታቸዋለን። ህወሓቶች የኤርትራን ነፃ መውጣት የማይቀበል ወገን ዋንኛ ጠላታቸው ነበር።

ይህን የተቃወሙ፣ የራሳቸውን አባላት ሳይቀር ለእስር፣ ለሞትና ለስደት እንደዳረጉ ሰምተናል። እኔና ብዙ ጓደኞቼም፣ "ኤርትራ የኢትዮጲያ አካል ነች" ብለን የፀና አቋም በመያዛችን፣ ለእስርና እንግልት ተዳርገናል። ይህን ስናጤን፣ በግንቦት 20 ቀን አዲስ አበባን በጠብመንጃ የተቆጣጠረው ኃይል፣ ከኢትዮጲያዊነት ይልቅ የኤርትራን አጀንዳ ያነገበ፣ ሀገር ለማስገንጠል ፀንቶ የታገለ ኃይል መሆኑን እንረዳለን።

በመሆኑም፣ ኢህአዴግ አዲስ አበባ እንደገባ የአሰብና የምፅዋ ወደብ በሻዕቢያ ቁጥጥር ሥር እንዲሆን ተደረገ። ሀገራችንም የራሷን ወደብ በከፍተኛ ገንዘብ ለመከራየት ተገደደች። የኢትዮጵያ ንብረት የሆነውና በአሰብ ተተክሎ የቆየው ነዳጅ ማጣሪያ /refinery ለኢትዮጵያ በብዙ ገንዘብ ክፍያ ነበር ነዳጅ የሚያጣራው።

ህወሓት ኋላ ላይ አመጣሁት ብሎ ፕሮፓጋንዳ ሲነፋበት የነበረው የኢኮኖሚ ዕድገትም፣ ጥቂት የራሱን ሰዎችና የንግድ ተቋማቱን ብቻ ተጠቃሚ ያደረገ አድሎአዊ የኢኮኖሚ ፓሊሲ በመሆኑ፣ አብዛኞቹ የሀገሪቱ ዜጎች ለከፋ ድህነት ተዳርገዋል ።ሚሊየነር ባለስልጣናትና የጦር ጄኔራሎች የተፈጠሩት በኢህዴግ የስልጣን ዘመን ነው፤ እነዚህም አብዛኞቹ የህወሓት አባላት ናቸው፤ በቢሊዮን የሚቆጠር ሀብት ያካበቱ የፖለቲካ ድርጅት የቢዝነስ ተቋማት የተፈጠሩትና የፓርቲ ሞኖፓሊ የተጠናከረው በኢህአዴግ ዘመንና በኢህአዴግ የንግድ ድርጅቶች ነው።

የህወሓት ሰዎች አሳማኝ ፕሮጀክት ሳያቀርቡና በቂ ዋስትና/ማስያዣ ሳይኖራቸው፣ ከፍተኛ ገንዘብ በመበደር ባንኮችን አክስረዋል። ፍትሀዊ የሆነ የገበያ ውድድር አልነበረም፣ የሥራ ዕድል የሚያገኙት የህወሓት ሰዎችና የሊግ አባላት ነበሩ፣ ሌላው ተምሮ በሀገሩ ሥራ ማግኘት አልቻለም። ለሥራ ፍለጋ ሲሉ በአደገኛ ሁኔታ ከሀገር ለመውጣት ሲሞክሩ፣ በባህር ሰምጠው የሚሞቱና በአውሬ የሚበሉ ዜጎች በዝተው የዓለም መሳለቂያ የሆነው በህወሓት የስልጣን ዘመን ነው።

ሙስና (ሌብነት) ነውር መሆኑ ቀርቶ ሥራ የሆነበት፣ በብድርና በዕርዳታ የመጣው ገንዘብና ንብረት ሳይቀር የተመዘበረበት፣ የሀገርን ሃብት የዘረፉትን ለህግ ለማቅረብ ሲሞከር፣ "ጀግኖቻችን አይነኩም" የሚል አሳፋሪ ትውልድ የታየበት ወቅት፣ ህወሓት መራሹ ኃይል መንግስት በሆነበት ወቅት ነው። ጥቂት የህወሓት ሰዎችና የእነሱ የቢዝነስ ተቋማት ቢሊየነር ሆነው ሳሉ፣ ሀገሪቱ ዕዳዋን መክፈል ያቃታት ሁኔታ የተፈጠረው፣ በግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም ስልጣን በያዘው ቡድን ሳቢያ ነው፤ ይህ ነው የግንቦት 20 ውጤት።

## "ህወሓት፤ ከታሪክ ጋር የተጣላ"

### ለማየሁ ኢታና፣ የሁለተኛ ደረጃ የታሪክ መምህር

ህወሓት ኢህአዴግ በተዛባ የታሪክ አተያይ ኢትዮጲያን ያስገነጠለና የባህር በር ያሳጣ ኃይል ነው። ኤርትራ በታሪክም ሆነ በተፈጥሮ የኢትዮጲያ አካል ነች፣ ቀይ ባህር ላይም ኢትዮጲያ ሰፊ ይዞታ አላት። ይህ በአረቡ ዓለምም ሆነ በመላው ዓለም ይታወቃል ፣በርካታ የታሪክ ተመራማሪዎች ቀይ ባህርን ከኢትዮጵያ ጋር አያይዘው የፃፏቸው የታሪክ ድርሳናት አሉ። በአረቡ ዓለም ያሉ የኢትዮጲያ ታሪካዊ ጠላቶች፣ ሀገራችንን ከቀይ ባህር ይዞታዋ ለማስወጣትና ከከፍታዋ ለማውረድ ከ15ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ጥረት እያደርጉ ሳይሳካላቸው ቆይተዋል።

## “በህዝቦች መካከል የፀብ ግድግዳ (የአኖሌን ሐውልት) ያቆሙ ስልጣን የያዙበት ዕለት ስለሆነ በሃዘን ነው የማስታውሰው

የውጭ ኃይሎቹ በቀጥተኛ ወረራ ያላሳኩትን ኢትዮጲያን የባህር በር የማሳጣት ሴራ፣ ወያኔና ሻዕቢያ በቅጥረኝነት አሳኩላቸው። ግንቦት 20 ቀን ኢትዮጲያን የባህር በር ያሳጡ፣ አንድ ህዝብ የሆኑትን የኤርትራንና የኢትዮጲያ ህዝቦች የለያዩ፣ ከዚያም በኋላ የሌለ ታሪክ እየፈጠሩ ዜጎችን እርስ በእርስ በማባላት ኢትዮጲያን ለማፍረስ እየሰሩ ያሉ፣ ዓለም ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸውንና አፍሪካውያን የሚኮሩባቸውን መሪዎቻችንን ታሪክ ያጠለሹ፣ በህዝቦች መካከል የፀብ ግድግዳ (የአኖሌን ሐውልት) ያቆሙ ስልጣን የያዙበት ዕለት ስለሆነ በሃዘን ነው የማስታውሰው።

የታሪክ አስተማሪዎች የማስተመሪያ ፅሁፍ (ኖት) በካድሬዎች ይታያል።በደህንነት የተመደቡ ጆሮ ጠቢዎች ክፍል ውስጥ ይከታተሉናል። እኔ ትክክለኛውን የኢትዮጵያን ታሪክ በማስተማሬና ማስተማሪያ ኖቴንም አላሳይም በማለቴ ጥርስ ውስጥ ገባሁ። አዳማ የመንግስት ትምህርት ቤት ሳስተምር ተማሪዎች ስለ ምኒልክ ጡት መቁረጥና ስለ አኖሌ ሐውልት ጠየቁኝ፣ "እኔ በታሪክ ያልተፃፈ የፈጠራ ታሪክ አላስተምራችሁም፣የማስተምራችሁ የአውሮፓ ፀሐፊዎች ሳይቀር የፃፉትን የምኒልክን የአድዋ ጀግንነት ነው፣ የስልጣኔ ፈር ቀዳጅነታቸውን ታሪክ ነው "በማለቴ ከመምህርነት ሥራ ታግጃለሁ። ያገዱኝ ደግም የትምህርት ቤቱ ኃላፊዎች አይደሉም፤ አንድ የፌዴራል ደህንነት ሹም ነው። እና እነዚህ የኢትዮጲያ ህዝብ ጫንቃ ላይ የወጡበትን ቀን ነው የማከብርላቸው?

## "ዕለቱ አምባገነንና ዘረኛ መንግስት የቆመበት ነው"

### ዳኑ አበበ፣ ወልደያ

የ52 ዓመቱ ጎልማሳ ዳኑ አበበ በወልዲያ ከተማ ከቤተሰቦቹ ጋር ይኖር ነበር። አሁን በአዲስ አበባ ከተማ በንግድ ሥራ ተሰማርቶ ራሱንና ቤተሰቡን ያስተዳድራል። በህወሓት ተደጋጋሚ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተፈፅሞብኛል የሚለው አዳነ፣ ግንቦት 20 ለእሱ በኢትዮጵያ አምባገነንና ዘረኛ መንግስት ስልጣን የያዘበት ጊዜ ነው።

ከግንቦት 1983 በፊት ጭቆና የነበረ ቢሆንም፣ በብሔር አትመዘንም፣ ህወሓት ኢህአዴግ ስልጣን ላይ ከወጣ ወዲህ ግን፣ ዜጎች የሚለኩት በዘራቸው ሆነ ። ህወሓት ወደ መሃል ኢትዮጲያ ሳይዘልቅ፣ ወልዲያ በገባ ጊዜ፣ ህዝቡ ከፍተኛ ተቃውሞ አድርጎ ነበር። "ጠባቦች ናችሁ ፣አገር ገንጣዮች ናችሁ" ብሎ በተቃውሞ ወጥሯቸው ነበር ።ሲያስተምሩን (የፓለቲካ ቅስቀሳ ሲያደርጉልን) “ኤርትራ በኢትዮጲያ ቅኝ የተያዘች ሀገር ስለሆነች ነፃ መውጣት አለባት ይሉን ነበር፤ ምን አገባችሁ?እናንተ ኢትዮጲያዊያን ከሆናችሁ፣ ለምን ሀገራችሁን የሚጎዳ የመገንጠል ጥያቄን ትደግፋላችሁ? "እንላቸው ነበር። “አስገንጣዮች” በማለትም፣ ህዝቡ ተቃውሞውን በከፍተኛ ደረጃ አሰምቷል።

ውለው አድረው ግን ወያኔዎቹ የወልዲያን ህዝብ ተበቀሉት፣ ምንም መሠረተ ልማት አላገኘም። ህወሓት በቀለኛ ነው፣ ከምርጫ 97 በኋላ፣ “ቅንጅትን መርጠችኋል፣ የቅንጅት አባል ሆናችኋል” ብሎ ገበሬዎች ማዳበሪያ እንዳያገኙ አድርጓል። በቅርቡም የወልዲያን ህዝብ ህፃን ልጅ ሳይቀር ጨፍጭፏል። ጥምቀተ ባህር ላይ፣ ታቦት ፊት ለፊት፣ በስናይፐር ነዋሪውን ለሞትና ለአካል ጉዳት ዳርገዋል። እኔ ለሁለት የተለያዩ ጊዜያት ታስሬ ለመግለጽ የሚዘገንን ግፍ ተፈፅሞብኛል።ታዲያ ይህን ህዝብ፣ “ግንቦት ሀያን አክብር” ስትለው ቁስሉን በእንጨት መውጋት አይሆንም?

## የተገደሉ ሰዎችን አስከሬን እያወጡ ሌሎችን መግደል

### ወይዘሮ ጋቷ ሰብስቤ

ግንቦት 20 ቀን 1983 ህወሓት መላ ኢትዮጲያን እንደተቆጣጠረ በቀይ ሽብር ተገደሉ የተባሉ ዜጎችን አስከሬን እየቆፈረ ወደማውጣት ነበር የገባው። የህዝብ ድጋፍ ለማግኘትና ደርግን ለማስጠላት ሲል የሟች ዘመዶችን የተረሳ ሐዘናቸውን እያስለቀሰ ራሱ ግን ያለፍርድ ግድያ ይፈፅም ነበር።

በወቅቱ “ሌባ ሌባ” ተብሎ ሰው ሲሮጥ ከታየ፣ ተጋዳላዩ ተኩሶ ጠብ ያረገው ነበር። ባለፉት 27 ዓመታት ወያኔዎች ፍትህን በሰላማዊ መንገድ የጠየቁ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰላማዊ ዜጎችን ጨፍጭፈዋል፣ በምርጫ 97 ድምፃችን ይከበር ያሉ በርካታ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በአደባባይ ተረሽነዋል፣ ከቤታቸው ከወላጆቻቸው ስር በለሊት ታንቀው እየተወሰዱ ለሞትና ለአካል ጉዳት የተዳረጉ ብዙ ናቸው። እናትና ልጅ በአንድነት የተረሸኑ አውቃለሁ። እናት፣ “ልጄን አትግደል” ብላ ስትማፀን አብሮ ረሸኗቸው ሄደ፣ ይሄ ሁሉ የአዲስ አበባ ህዝብ በሰለጠነ መንገድ፣ በካርዱ “ኢህአዴግን አልፈልግህም” ስላለው ነው። እንደ አዲስ አበባ ህዝብ በወያኔ የግፍ በትር የተቀጠቀጠ የለም፣ ይህ ነው የግንቦት 20 ቱሩፋት።

## ሻለቃ ሙኤል ሎራቶ

ህወሓት የኢትዮጲያን መከላከያ ሠራዊት አፍርሶ የራሱን የፓርቲ ሠራዊት መሠረተ። ከደምወዛችን እየተቆረጠ የተሰበሰበውን የጡረታ መዋጮ ሳይቀር ነጥቆን በተነን። የወጣትነት አፍላ ጉልበታችንንና አካላችንን ለሀገራችን እንዳልገበርን፣ በአንድነት ጠላቶች የበቀል ዒላማ ተደረግን፤ የኢትዮጲያ ህዝብም የወያኔ መፈንጫ ሆነ። እኛ የሀገራችን ሰላም እንዳይናጋ በማሰብ ወደ ዘረፋ ከመግባት ይልቅ፣ በእጃችን የጦር መሣሪያ ይዘን ምፅዋት ጠይቀናል። ያን ጊዜ የመንግስት ለውጥ ሲደረግ ሀገሪቱ ሳትበጠበጥ ነበር ሰራዊቱ ትጥቅ የፈታው። አሁን በዚህ ጊዜ፣ ሀገሪቱን ሲግጡና ህዝቡን ሲያሰቃዩ የነበሩ ኃይሎች፣ “ስልጣንና ዘረፋ ለምን ቀረብን?” ብለው እርስ በርስ ያበጣብጡናል፤ ሀገሪቱም ልትረጋጋ አልቻለችም። የሆነ ሆኖ ግንቦት 20 ለኢትዮጲያ ህዝብ የሰቆቃው ምዕራፍ የተጀመረበት ዕለት ነው።


# የአቶ ግሩም ከፈኒ
## የ1ኛ ዓመት የሙት ዓመት መታሰቢያ



ከ1913 – 2010 ዓ ም

የአባታችን የአቶ ጉርም ከፈኒ የ1ኛ ዓመት መታሰቢያ

ግንቦት 16 ቀን 2011 ዓ ም ደብረ ኃይል ቅድስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን በጸሎተ ፍትሀትና ነዲያንን በመዘከር ታስቦ ይውላል ፡፡

ከልጆቻቸው

ለዚህ ማስታወቂያ ክፍያ አልተፈጸመም !



ዳንኤል አኬች ቲዮንግ
የደቡብ ሱዳን ፖለቲካ እና ኢኮኖሚ አማካሪ

# የደቡብ ሱዳን ተፋላሚ ወገኖች እና የዓለም ዓቀፍ ለጋሾች ግንኙነት



## እንደመግቢያ

የረድዔት ድርጅቶች በደቡብ ሱዳን ደም አፋሳሽ የእርስ በርስ ጦርነት ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል:: ታዲያ፣ ለጋሽ ድርጅቶቹ ከዚህ አስቸጋሪ እና አዳጋች አዙሪት መላቀቅ የሚችሉት እንዴት ነው?

የደቡብ ሱዳን የእርስ በርስ ጦርነት በ2013 (እ.አ.አ.) ከተቀጣጠለ ወዲህ፣ ሰብዓዊ ቀውሱ ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰ መጥቷል:: በዚህ ሂደትም፣ ዐማፂያን፣ የሀገሪቱ መንግሥት እና ዓለም ዓቀፉ ማኅበረሰብ የየበኩላቸውን ሚና ተጫውተዋል:: እነኝህ ሦስት ወገኖች ከአምስት ዓመታት ለበለጠ ጊዜ ይህንኑ ሚና በተደጋጋሚ ተጫውተዋል::

በደቡብ ሱዳን ባለው ሁኔታ ቅሬታ ወይም ብሶት የተሰማው አንድ የመሪዎች ቡድን የትጥቅ ትግል ሲጀምር፣ አንድ አዲስ የውጊያ ግንባር ይፈጠር ነበር:: እነኝህ ግለሰቦች አብዛኛውን ጊዜ የትጥቅ ትግል የሚጀምሩት በማኅበረሰቦቻቸው ዘንድ ያለውን ብሶት ወይም ቅሬታ ለመፍታት ወይም እውነተኛ ለውጥ ለማምጣት ሳይሆን፣ የግል ፍላጎታቸውን ለማሟላት የተነሡ የቀድሞ የመንግሥት ባለሥልጣናት ናቸው::

የጦር መሣሪያ ትንቅንቁ እየተስፋፋ እና በሁከቱ እና በብጥብጡ ብዙ ሕዝብ እያለቀ በሄደ ቁጥር፣ የረድዔት ድርጅቶች የለጋሾችን ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ እና የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ሲሉ፣ የእርስ በርስ ጦርነቱ እያስከተለ ባለው ሰብዓዊ ቀውስ ዙሪያ ሪፖርቶችን ያወጣሉ:: በስተመጨረሻ ላይም፣ ሽምጋዮች ደም መፋሰሱን ለማስቆም ተፋላሚ ወገኖቹ በሥልጣን መጋራት ዙሪያ ከስምምነት ላይ እንዲደርሱ በሂደቱ ጣልቃ ይገባሉ:: ስምምነቱ በሁለቱም ወገኖች ዘንድ ተቀባይነትን ካገኘ ደግሞ፣ ዐማፂያኑ ቀደም ሲል ከነበራቸው የበለጠ ሥልጣን ይዘው ለአንድ ተጨማሪ ጊዜ በመንግሥት ውስጥ ይታቀፋሉ:: አንዳንድ ጊዜ፣ ይኸው ዑደት ከተመሳሳይ ወይም ከተለያዩ መሪዎች ጋር ሊደጋገም ይችላል::

ዓለም ዓቀፉ ማኅበረሰብ በዚህ ተደጋጋሚ ሁነት ቁልፍ ሚና ይጫወታል:: የዓለም ዓቀፉ ማኅበረሰብ ጥረት ከልብ የመነጨ እና የተራውን ሕዝብ ሰቆቃ ለማስወገድ ያለመ ሊሆን ይችላል:: ይሁን እንጂ፣ ተፋላሚ ወገኖቹ ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ከዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ጋር የሚያደርጉት ግንኙነት አላስፈላጊ ውጤቶችን ሊያስከትል ይችላል::

## የተፋላሚ ወገኖች ሚና

ደቡብ ሱዳን ውስጥ ሰብዓዊ ቀውስ በተፈጠረ ቁጥር፣ የእርዳታ ድርጅቶች ምግብ፣ መድኃኒት እና መጠለያ በማቅረብ፣ ችግሩን ለመፍታት ይጥራሉ:: ይህ አሠራር ወሳኝ ነው፤ ይሁንና፣ የእርዳታ ድርጅቶቹ ተነሣሽነት ተገቢው ጥበቃ እስከሌለው እና በዕቅድ እስካልተመራ ድረስ፣ የጦር አበጋዞችን፣ በተለይም የዐማፂያንን፣ ጥቅም የሚያስከብር መሆኑ አይቀርም::

በመጀመሪያ ደረጃ፣ ታጣቂ ቡድኖቹ ለራሳቸው የጦርነት ዓላማ ማራመጃ የሚያውሉትን ሰብዓዊ እርዳታ እጃቸው ውስጥ ለማስገባት የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ:: ከዚህም በላይ፣ ተፋላሚ ወገኖቹ አብዛኛውን ጊዜ የሰብዓዊ እርዳታው በቦታው መገኘት የራሳቸውን ሕጋዊነት ከፍ ለማድረግ እና 'እወክልሃለሁ' በሚሉት ማኅበረሰብ ስም እየተንቀሳቀሱ እንደሆነ ለማሳየት፣ እንዲሁም የድጋፍ መሠረታቸውን ለማጠናከር ይጠቀሙበታል:: ለምሳሌ ያህል፣ ፕሬዚዳንት ሳልቫ ኪር በአንድ ወቅት ከቻይና መንግሥት በእርዳታ የተገኘውን 10,000 ከረጢት ሩዝ፣ ለሕዝባቸው ያቀረቡት የራሳቸው ስጦታ እንደሆነ ገልጸው ነበር::

ከዚህ በተጨማሪም፣ የደቡብ ሱዳን መንግሥት ለጋሽ ድርጅቶች በየጊዜው የተፈጠሩ ሰብዓዊ ቀውሶችን በተመለከተ የሚያወጣቸውን ሪፖርቶች፣ የራሱን ጥቅም እና ፍላጎት ለማሟላት ተጠቅሞባቸዋል:: የመንግሥት ባለሥልጣናት አስደንጋጭ የሆኑ የሰብዓዊ ቀውስ ሪፖርቶችን አንዳንድ ጊዜ ሀገሪቷ ከመፈራረስ አደጋ ጋር እንደተፋጠጠች በመግለጽ፣ በሕዝቡ ዘንድ ፍርሃት ለማስፈን ሲጠቀሙባቸው ይስተዋላል፤ ዓለም ዓቀፍ አጋሮች ደግሞ፣ ይህን አሳሳቢ አደጋ ለማስቀረት እየተረባረቡ እንደሆኑ የመንግሥት ባለሥልጣናቱ ለሕዝባቸው ይፋ ያደርጋሉ:: የደቡብ ሱዳን መንግሥት የውጭ ለጋሾችን እንዳሻው ለማሳመን እና ዓለም ዓቀፍ የፋይናንስ ተቋማትን ገንዘብ ለመጠየቅ ይህ ዓይነቱን አሠራር መጠቀሙ የዕለት ተዕለት ክስተት ነው ማለት ይቻላል:: ለምሳሌ ያህል፣ የደቡብ ሱዳን መንግሥት ይህንኑ ዘዴ በመጠቀም፣ የአውሮጳ ኅብረት ከሚያዝያ 2017 (እ.አ.አ.) ወዲህ ለ30,000 የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን በየወሩ 40 የአሜሪካ ዶላር በደመወዝ መልኩ እንዲከፍላቸው ማሳመን ችሏል::

ተፋላሚ ወገኖች የሰብዓዊ እርዳታ ለጋሽ ድርጅቶችን በሀገራቸው ውስጥ መገኘት ከተለያዩ አካላት ገንዘብ አስገድዶ ለመቀበል ሊጠቀሙበት ይችላሉ:: የደቡብ ሱዳን ታጣቂዎች በለጋሽ ድርጅቶች ላይ "የመቀመጫ ክፍያ" እና "የአውሮፕላን ማረፊያ ክፍያ" የመሰሉ አሠራሮችን በመዘርጋት፣ ፍርደ-ገምድል የክፍያ ሥርዓትን ለማቋቋም ተጠቅመዋል:: የደቡብ ሱዳን መንግሥት በበኩሉ፣ በመጋቢት 2017 (እ.አ.አ.) ለውጭ ሀገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ ለመስጠት የሚጠይቀውን ክፍያ ከ100 የአሜሪካ ዶላር ወደ 10,000 የአሜሪካ ዶላር አሳድጎታል:: ዓለም ዓቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የመመዝገቢያ ክፍያ ደግሞ፣ ከ2,000 የአሜሪካ ዶላር 3,500 የአሜሪካ ዶላር ደርሷል::

በስተመጨረሻ ደግሞ፣ በደቡብ ሱዳን በርካታ የረድዔት ድርጅቶች መገኘት በተዘዋዋሪ መልኩ ለተፋላሚ ወገኖቹ የተለያዩ ጥቅሞችን ያስገኛል:: የምግብ እርዳታ የመሠረታዊ ሸቀጦች ዋጋ እንዳይጨምር ያግዛል:: ከዚህ በተጨማሪም፣ የውጭ የእርዳታ ድርጅቶች ሠራተኞች ለተለያዩ ዓላማዎች የሚያወጡት ገንዘብ፣ የተወሰኑ የንግድ ተቋማት ትርፋማ እንዲሆኑ ያግዛል::

ዑደቱን ማስቆም

ዓለም ዓቀፉ ማኅበረሰብ በደቡብ ሱዳን ለተቀጣጠለው የእርስ በርስ ጦርነት የሰጠው ምላሽ፣ በተለያዩ መስኮች የተሟላ ነበር ብሎ መናገር አይቻልም:: ተፋላሚ ወገኖቹ የሥልጣን መጋራት ስምምነትን እንዲፈራረሙ የሚደረገው ዲፕሎማሲያዊ ጥረት፣ ስኬታማ የመሆን ዕድሉ በጣም ጠባብ ነው:: ይህ ዓይነቱ አካሄድ ለሁከቱ እና ለብጥብጡ ዕውቅና የሚሰጥ፣ የግጭቱን ሥረ-መሠረት ከግምት ውስጥ ያላስገባ፣ እንዲሁም በስምምነቱ ያልተደሰቱ ልሂቃንን ከመንግሥታዊ ሥልጣን እና ከሀገሪቱ ሀብት የአንበሳውን ድርሻ ማንሣት በፈለጉ ቁጥር፣ የትጥቅ ትግል እንዲጀምሩ የሚያበረታታ ነው:: የመስከረም 2018 (እ.አ.አ.) የሰላም ስምምነት ላይ ፊርማቸውን ለማኖር ፈቃደኛ ያልሆኑት የጄነራል ቶማስ ቺሪሎ የቅርብ ጊዜ እርምጃዎች ደግሞ፣ ይህን የስምምነቱን ጉድለት አጉልቶ የሚያሳይ አብነት ነው::

ሽምጋዮች ለዚህ የስምምነቱ ጉድለት ዕውቅና በመስጠት፣ በአሁኑ ወቅት ሀገሪቷን እያመሳት ላለው ሁከት ያለውን አስተዋጽኦ ለማስወገድ መጣር ይኖርባቸዋል:: ይሁን እንጂ፣ ዓለም ዓቀፍ ለጋሾችም ቢሆኑ

ወደ 21 ዞሯል



*ማቲያ ካቻቶሪ*
ባዝ ዩኒቨርሲቲ
እንግሊዝ

# የአል-በሽር እና የዓለም አቀፍ ወንጀለኞች ፍርድ ቤት ፍጥጫ

## እንደመግቢያ

ለ30 ዓመታት የዘለቀው የፕሬዚዳንት ኦማር ሐሰን አል-በሽር አምባገነናዊ አገዛዝ በቅርቡ በተካሄደ ወታደራዊ መፈንቅለ-መንግሥት አብቅቷል። የሱዳን የመከላከያ ሚኒስትር፣ አዋድ ኢብን ኡፍ፣ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ አገዛዙ ማክተሙን እና የሀገሪቷ ርዕሰ-ብሔር ለደኅንነታቸው አስተማማኝ በሆነ ቦታ እንዲቀመጡ መደረጉን አስታውቀዋል። አል-በሽር በአሁኑ ወቅት ያሉበት ቦታ በግልጽ መታወቁን እጅግ አስፈላጊ የሚያደርገው ደግሞ፣ ዳርፉር ውስጥ በሰብዓዊነት ላይ ፈጽመዋቸዋል ለተባሉ ወንጀሎች፣ የጦር ወንጀሎች እና የዘር ማጥፋት በዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት የእስር ማዘዣ ስለወጣባቸው ነው። ይህ በእንዲህ እያለ፣ ዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት የሱዳኑን ፕሬዚዳንት፣ አል-በሽር፣ በተደጋጋሚ ችሎት ፊት ለማቅረብ ሞክሮ አልተሳካለትም።

ዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ከዚህ ጋር በተያያዘ መንቀሳቀስ የጀመረው የተባበሩት መንግሥታት በ2005 (እ.አ.አ.) የሱዳን መንግሥት ዳርፉር ግዛት ውስጥ በሰብዓዊነት ላይ ያነጣጠሩ ወንጀሎችን ስለመፈጸሙ የሚያትት ሪፖርት ማውጣቱን ተከትሎ ነው። ሪፖርቱ ከወጣ በኋላ፣ የተባበሩት መንግሥታት በጉዳዩ የተጠረጠሩትን ሰዎች ስም ዝርዝር ኔዘርላንድ፣ ዘ ሄግ ለሚገኘው ዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት አሳልፎ ሰጥቷል።

ዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት በቀጣዮቹ ዓመታት በዘር ማጥፋት፣ በጦር ወንጀሎች እና በሰብዓዊነት ላይ ለተፈጸሙ የተለያዩ ወንጀሎች በ2009 እና በ2010 (እ.አ.አ.) በአል-በሽር ላይ ሁለት የእስር ማዘዣዎችን አውጥቷል። በ2014 (እ.አ.አ.) የዓለም ዓቀፍ ወንጀለኞች ፍርድ ቤት ዋና ዐቃቤ ሕግ፣ ፋቱ ቤንሱዳ፣ አል-በሽርን በቁጥጥር ሥር በማዋሉ ሂደት ከተለያዩ አካላት በቂ ትብብር ባለመገኘቱ፣ ክሱን ወደጐን ገፍተውት ነበር። በርካታ የፖለቲካ ተንታኞች ይህን ውሳኔ ዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ኃያል ባለሥልጣናትን፣ በተለይም በሥልጣን ላይ የሚገኙ ርዕሰ-ብሔሮችን እና መራሄ-መንግሥታትን፣ ችሎት ፊት የማቅረብ ዓቅሙ ውስን እንደሆነ አመላካች ነው ባዮች ናቸው።

## ውስብስብ ችግር

የአል-በሽር ከሥልጣናቸው መወገድ የቀድሞው የሱዳን ፕሬዚዳንት በዓለም ዓቀፉ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ችሎት ፊት ይቀርቡ እንደሆነ ዳግም ጥያቄዎችን እያስነሣ ነው። የፖለቲካ ተንታኞች ገና ከወዲሁ አል-በሽር ዘ ሄግ ከሚገኘው ዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ፊት በመቅረባቸው ጉዳይ ዙሪያ የተለያዩ አስተያየቶችን እየሰነዘሩ ነው። ከእነኝህ አስተያየቶች መካከል፣ አል-በሽር ቀደም ሲል የነበራቸውን ሥልጣን በማጣታቸው፣ ሕግ ፊት መቅረባቸው አይቀርም የሚለው አንዱ ነው። ሌላኛው አስተያየት ደግሞ፣ አል-በሽር ከሥልጣናቸው ቢወገዱም፣ አሁንም ቢሆን በአዲሱ መንግሥት ዘንድ ተሰሚነት ስላላቸው ዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ችሎት ፊት የሚቀርቡበት አጋጣሚ በጣም ውስብስብ ይሆናል የሚለው ነው።

እንደእኔ እምነት፣ እዚህ ላይ አስቸጋሪ የሆነው ጉዳይ 'ዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት የቀድሞውን የሱዳን ፕሬዚዳንት ሕግ ፊት ማቅረብ ይኖርበታል ወይ?' የሚለው ነው። ይህ አስተያየት በተደጋጋሚ የቀረበ አላስፈላጊ ጥያቄ፣ አሊያም ኃላፊነት የጐደለው ጥያቄ ይመስል ይሆናል። አልፎ ተርፎም፣ 'አል-በሽር ከዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ችሎት ፊት ካልቀረቡ፣ ታዲያ ማን ሊቀርብ ነው?' የሚል ጥያቄ እዚህ ላይ ይነሣ ይሆናል። ይሁን እንጂ፣ ጉዳዩ ከዚህ ባለፈ ይበልጥ ውስብስብ ነው።

እዚህ ላይ አንድ ነገር ግልጽ ማድረግ እፈልጋለሁ፤ እኔ በበኩሌ፣ ለአል-በሽር ምንም ዓይነት ኀዘኔታ የለኝም። አልፎ ተርፎም፣ እንደአል-በሽር ሲቪሎችን የሚጐዱ ወይም ለመጉዳት ያለሙ ፖሊሲዎችን ለሚቀርጹ አምባገነን መሪዎች ምንም ዓይነት ኀዘኔታ የለኝም።

ያም ሆነ ይህ፣ አል-በሽር በአሁኑ ወቅት ያሉበት ልዩ ሁኔታ ዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤትን አጣብቂኝ ውስጥ እንደሚከትተው መዘንጋት የለብንም። ይህም የሚሆንበት ምክንያት፣ አሁን ካለው ሁኔታ ጋር ሁለት በጣም አስቸጋሪ ጉዳዮች በተያያዥነት ስለሚነሡ ነው። ሁለቱም ጉዳዮች በፍርድ ቤቱ እና በሥራው ላይ አሳሳቢ አንድምታዎች ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ፣ በሥልጣን ላይ የሚገኙ መሪዎች ከተጠያቂነት አመልጣለሁ በሚል መንፈስ ሕዝባቸውን እንዳሻቸው መምራት ይችሉ እንደሆነ ጥያቄዎችን የሚያስከትሉ ናቸው።



## እንቆቅልሹ

ማንም ሆነ ማንም፣ በሥልጣን ላይ ያሉ የሀገራት መሪዎች ዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ችሎት ፊት መቅረብ አለባቸው ከሚለው ሐሳብ በስተጀርባ፣ በሰብዓዊነት ላይ ያነጣጠሩ ወንጀሎች በጅምላ እስኪተፈጸሙ ድረስ ፍትሕ የሚሹት ወገኖች ድምፅ መሰማት አለበት የሚለው እሳቤን እናገኛለን። በመሠረቱ፣ የዚህ እሳቤ መነሻ ሐሳብ በርዕሳነ-ብሔር እና በመራሄ-መንግሥታት ላይ ገደብ በማስቀመጥ፣ የሉዓላዊ ሀገራት መሪዎች በሕዝባቸው ላይ አሰቃቂ ወንጀሎችን እንዳይፈጽሙ ማሳመን እና መገፋፋት ነው። በሌላ አነጋገር፣ የሐሳቡ መነሻ እና መድረሻ፣ መሪዎች የያዙት ሥልጣን ዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ችሎት ፊት ከመቅረብ እንደማይከላከልላቸው እንዲያውቁ እና ግንዛቤው እንዲኖራቸው ማድረግ ነው።

ያለመታደል ሆኖ፣ ዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ይህን እሳቤ ተግባራዊ ለማድረግ በተነሣበት ወቅት ከባድ ተቃውሞ ገጥሞታል። ለምሳሌ፣ ኬንያን በተመለከተ፣ የዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ዋና ዐቃቤ ሕግ፣ ፋቱ ቤንሱዳ፣ በ2014 (እ.አ.አ.) በሀገሪቷ ውስጥ ተፈጽመዋል የተባሉትን ወንጀሎች ከዚህ ባለፈ ለመመርመር አልቻልኩም በሚል ምክንያት ቀደም ሲል በሀገሪቱ ርዕሰ-ብሔር፣ ኡሁሩ ኬንያታ፣ ላይ የመሠረተውን ክስ ለመሰረዝ ተገድዷል። ይህም የሆነበት ምክንያት፣ ምሥክሮች የምሥክርነት ቃላቸውን ለመስጠት በመፍራታቸው፣ እንዲሁም የኬንያ መንግሥት ለመተባበር ፈቃደኛ ባለመሆኑ ነው።

የአፍሪቃ ኅብረት በበኩሉ፣ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ትኩረቱን ማድረግ ያለበት በመካከለኛ እርከን በሚገኙ የመንግሥት ባለሥልጣናት ላይ ነው የሚል አቋም እስከመያዝ ደርሷል። ይሁን እንጂ፣ ዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት አል-በሽርን ችሎት ፊት ማቅረብ ካልቻለ፣ ፍርድ ቤቱ የአንዲት ሀገርን ከፍተኛ ባለሥልጣናትን በተመለከተ ዓቅመ-ቢስ ነው ብለው የሚያስቡ ተቺዎቹን የሚያበረታታ ይሆናል። በሌላ በኩል፣ ዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት አል-በሽርን ችሎት ፊት ማቅረብ ከቻለ፣ በእሳቸው እርከን የሚገኙ ባለሥልጣናት ችሎት ፊት የሚቀርቡት ከሥልጣናቸው ሲወርዱ ብቻ ነው የሚል መልዕክት ያስተላልፋል።

እኔን የሚያሳስበኝ ነገር የሚመጣው ደግሞ፣ እዚህ ላይ ነው። ዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት አል-በሽርን ችሎት ፊት ማቅረብ ከቻለ፣ ለሌሎች አምባገነን መሪዎች አስጨናቂ መልዕክት የሚያስተላልፍ ይሆናል፤ ይህም መልዕክት በሥልጣን ላይ እስካላችሁ ድረስ ያሻችሁን አድርጉ የሚል ነው። እንዲውም፣ መልዕክቱ አልፎ ተርፎ የሥልጣን ዕድሜያችሁን ለማራዘም ያሻችሁን ፈጽሙ የሚል ሊሆን ይችላል። ታዲያ፣ ይህን ዓይነቱ መልዕክት በሁለት ምክንያቶች አደገኛ ሆኖ እናገኘዋለን።

## አደገኛ መልዕክት

ከአል-በሽር ከዓለም ዓቀፉ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ችሎት ፊት መቅረብ ጋር ግንኙነት ያለው የመጀመሪያው መልዕክት፣ በጦርነት እየታመሱ ከሚገኙ ሀገራት ጋር የተያያዘ ነው። ዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ከመሠረታቸው ክሶች መካከል፣ አብዛኞቹ ወንጀሎች የተፈጸሙት በጦርነት እየታመሱ በሚገኙ ክልሎች እና

ወደ 21 ዞሯል

*አዘጋጅ፡- ማውሮ*

# ጥቂት ነጥቦች ስለእርግዝና

- በማንኛውም ጊዜ ከአሜሪካውያን ሴቶች መካከል 4% ያህሉ ነፍሰ-ጡር ናቸው፡፡
- ለመጀመሪያ ጊዜ በቀዶ ማዋለድ ስኬታማ በሆነ መልኩ የወለደች በ16ኛው ምዕተ-ዓመት በስዊዘርላንድ ኗሪ የሆነች አንዲት ሴት ናት፤ ሕክምናውን ያደረገውም መተዳደሪያው የአሳማ ሙክት አድላቢው ባለቤቷ ነበር፡፡
- በየዓመቱ በዩ.ኤስ. አሜሪካ ከሚከሰቱ 6.7 ሚሊዮን እርግዝናዎች መካከል፣ ግማሽ ያህሉ የታቀዱ አይደሉም፤ ከእነኚህም መካከል፣ 43% መጨረሻቸው ውርጃ ነው፡፡
- በሁለተኛው የእርግዝና አጋማሽ ሽሉ በቀን አንድ ሊትር ያህል ሽንት መሽናት ይጀምራል፤ ከዚህ ሽንት ላይም አብዛኛውን የሚውጠው ሽሉ ራሱ ነው፡፡
- ብዙ ሴቶች በእርግዝናቸው ወቅት በሚያጋጥም የሆርሞን ለውጥ እና ሰውነታቸው ከወትሮው ተጨማሪ ቪታሚን ስለሚመገብ ጸጉራቸው ይወፍራል፣ ያብረቀርቃል፡፡
- ነፍሰ-ጡር ሴቶች የተለያዩ ነገሮችን መመገብ የሚያምራቸው ሰውነታቸው ተጨማሪ የማዕድናት እና የምቾት ሰጪ ሴሮቶኒን ሆርሞን ፍላጎት ስለሚኖረው ነው፡፡
- ከዐሥር ሴቶች መካከል ዘጠኙ ልጅ በሚወልዱበት ወቅት ብልታቸው በተወሰነ መልኩ ይሸረከታል፤ ከዚህ ዓይነቱ እክል የተወሰነው ምንም ዓይነት ሕክምና ሳያስፈልገው በራሱ ጊዜ የሚድን ቢሆንም፣ ሽርክቱ አንዳንድ ጊዜ እስከፊንጣጣ ሊደርስ ይችላል፡፡
- ነፍሰ-ጡር ሴቶች ካረገዙ በኋላ ባሉት ጥቂት ሳምንታት ውስጥ የማሽተት ስሜታቸው ይጨምራል፤ አንዳንድ የዘርፉ ባለሙያዎች እንደሚሉት፣ ሁኔታው የሴቷ ሰውነት ለሽሉ አላስፈላጊ የሆኑ የምግብ ዓይነቶችን ለመከላከል የሚያደርገው ጥረት አካል ነው፡፡
- የአንዲት ነፍሰ-ጡር ሴት ጡት ወተት ማምረት የሚጀምረው ካረገዘች ከሦስት ወራት በኋላ ነው፡፡
- ከሁሉም ነፍሰ-ጡር ሴቶች መካከል መንታ የሚወልዱት 3% ያህሉ ብቻ ናቸው፡፡

# የንዴት ጉዳት

በጣልያን፣ ፓዱዋ ዩኒቨርሲቲ የሥነ-ልቦና መምህርት፣ ቫሌንቲና ዱርሶ፣ እንደሚሉት፣ "ንዴት በኅብረተሰባችን ውስጥ በጣም እየተስፋፋ የመጣ ክስተት ይሁን እንጂ፣ በሰውነታችን ለሰይ ጉዳት ያስከትላል።" ስንናደድ ቱንቻዎች ይኮማተራሉ፣ የልብ ምት ይጨምራል፣ ትንፋሽ ቁርጥ ቁርጥ ይላል፣ እንዲሁም መላው ሰውነት ከባድ ውጥረት ውስጥ ይገባል። ከዚህ በተጨማሪም፣ ንዴት የአንድን ሰው የማሰብ እና የማመዛዘን ችሎታ ያዛባል፣ እንዲሁም የሚያደርጋቸውን ነገሮች እንዳይቆጣጠር ተጽዕኖ ያሳድርበታል። ዱርሶ፣ " ሊያናድዱ ለሚችሉ ሁኔታዎች ራሳችንን አስቀድመን የማዘጋጀት ልምድ ይኑረን... በረጋ መንፈስ ፊት ለፊት 'በዚህ ነገር አልስማማም' ማለት ብንችል የተሻለ ኑሮ እንኖራለን። በማለት ይመክራሉ።

# የኢንሱሊን ሕክምና

የስኳር ሕመም ያለባቸው ብዙ ሰዎች የአመጋገብ ጥንቃቄ እና የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ከማድረግ በተጨማሪ፣ በየቀኑ በደማቸው ውስጥ ያለውን የስኳር መጠን መመርመር እና በተለያዩ ሰዓታት ኢንሱሊን መወጋት ያስፈልጋቸዋል። ዓይነት 2 የስኳር ሕመም ከያዛቸው ሰዎች አንዳንዶቹ ጥሩ የአመጋገብ እና የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ልማድ በማዳበራቸው ጤንነታቸው ከመሻሻሉም በላይ፣ ለጊዜውም ቢሆን ኢንሱሊን መወጋት አቁመዋል። በዓይነት 2 የስኳር ሕመም ተጠቂ የሆኑ ሰዎች የአካል ብቃት እንቅስቃሴ መሥራታቸው፣ በመርፌ የሚወስዱት ኢንሱሊን በሰውነታቸው ውስጥ በተሻለ ሁኔታ እንዲሠራ እንደሚረዳቸው ተገንዝበዋል። በዚህም ምክንያት፣ በየቀኑ የሚወጉትን የኢንሱሊን መጠን እስከ 20 በመቶ ድረስ መቀነስ ችለዋል። ይሁን እንጂ፣ ኢንሱሊን መውሰድ አስፈላጊ ሆኖ ቢገኝ፣ ሕመምተኛው ተስፋ የሚቆርጥበት ምክንያት የለም። ለበርካታ የስኳር ሕሙማን የሕክምና ክትትል የሚያደርጉት የጤና ባለሙያዋ፣ ሜሪ አን፣ "ኡንሱሊን መውሰዱ ድክመት እንዳለብን አያሳይም። ምንም ዓይነት የስኳር ሕመም ይኑረን፣ የደማችንን የስኳር መጠን በጥንቃቄ ከተቆጣጠርን፣ ወደኋላ የሚመጡ የጤና ችግሮችን በአብዛኛው መቀነስ ይቻላል" ብለዋል። እንዲያውም፣ በቅርቡ የተደረገ አንድ ጥናት የደማቸውን የስኳር መጠን በጥንቃቄ የተቆጣጠሩ ዓይነት 1 የስኳር ሕመም ያለባቸው ሰዎች በስኳር ሕመም ምክንያት የሚመጡ የዓይን፣ የኩላሊት እና የነርቭ በሽታዎችን በእጅጉ መከላከል እንደቻሉ አረጋግጧል። ለምሳሌ፣ በዓይን ሕመም (ሬቲኖፓቲ) የመጠቃት ዕድላቸው 76 በመቶ ቀንሷል። ዓይነት 2 የስኳር ሕመም ያለባቸውም ቢሆኑ፣ የደማቸውን ስኳር መጠን በጥንቃቄ በመቆጣጠር፣ ተመሳሳይ ጥቅም አግኝተዋል። የኢንሱሊንን ሕክምና ይበልጥ ቀላል እና የማያሳምም ለማድረግ በጣም የተለመዱት የኢንሱሊን መውጊያ መሣሪያዎች፣ ማለትም ሲሪንጆች እና የኢንሱሊን ብዕሮች፣ በጣም ቀጭን መርፌ እንዲኖራቸው ተደርጓል። አብዛኛውን ጊዜ በጣም የሚያሳምመው "የመጀመሪያው መርፌ ነው። ከዚያ በኋላ ግን፣ ምንም እንደማይሰማቸው አብዛኞቹ በሽተኞች ይናገራሉ" ይላሉ ሜሪ አን። ሌሎች የኢንሱሊን መውጊያ መሣሪያዎችም አሉ። በማያሳምም መርፌ ቆዳ ላይ ጠቅ ካደረጉ በኋላ ኢንሱሊን የሚፈጩ እና ሆድ ላይ ወይም ሌላ ቦታ ላይ ተሰክተው ለሁለት ወይም ለሦስት ቀናት የተመጠነ ኢንሱሊን ወደሰውነት የሚያስገቡ መሣሪያዎች ይገኛሉ። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ይህ የትንሽ ተንቀሳቃሽ ስልክ መጠን ያለው የኢንሱሊን መርጫ መሣሪያ የበለጠ ተወዳጅነትን አትርፏል። ይህ ራሱን በራሱ እየተቆጣጠረ ሰውነታችን በሚያስፈልገው መጠን ኢንሱሊን የሚያስተላልፍ መሣሪያ የኢንሱሊንን አወሳሰድ ይበልጥ ትክክለኛ እና አመቺ አድርጎታል።

# ይህን ያውቁ ኖሯል?

- እንጆሪ መመገብ ዕይታን ከማሻሻል ባለፈ፣ የካንሰር ተጋላጭነትን ይቀንሳል።
- ናርባ፣ ሐብሐብ፣ ቃሪያ፣ ሰለሪ፣ እርጎ፣ እንቁላል፣ ዓሣ፣ አረንጓዴ ሻይ፣ ውኃ እና አጃ በሰውነታችን ውስጥ ያለውን ስብ ለማቃጠል የሚያግዙ የምግብ ዓይነቶች ናቸው።
- ሰውነታችን አንዴ ስምንት ሰዓታትን በመተኛት ፈንታ በቀን ሁለቴ አራት ሰዓታትን እንዲተኛ ሆኖ የተፈጠረ ነው።
- እንቅልፍ የተከለከሉ ሰዎች ከአዎንታዊ ይልቅ አሉታዊ ተሞክሮዎችን ይበልጥ የማስታወስ አዝማሚያ አላቸው።
- ከባዮኬሚስትሪ አንጻር ወሲብ መፈጸም ቸኮላት ከመብላት የተለየ አይደለም።
- ስንሞት አካላችን መበስበስ ይጀምር እና የተሠራንባቸው አቶሞች እንደገና ጥቅም ላይ ለመዋል መሬት ውስጥ በሚካሄደው ዑደት በኩል ያልፋሉ።
- ሳይንቲስቶች እንደሚሉት፣ ሕፃት ብልኀነትን የሚወርሱት ከእናታቸው ነው።
- አእምሯችን 70% ጊዜውን የሚያሳልፈው ትዝታዎችን በመምዘዝ እና የተለያዩ ምስሎችን በመፍጠር ነው።
- ወንዶች ከሴቶች ያነሰ የሚያለቅሱበት አንዱ ምክንያት የእንባ ከረጢቶቻቸው ተለቅ ስለሚሉ ነው፤ በዚህም ምክንያት፣ እንባቸው በቀላሉ አይመጣም።
- አልኮል መጠጥ ጠጥተን ከልክ በላይ ስንሰክር አንጎላችን አዳዲስ ትዝታዎችን የመፍጠር ዓቅሙን ያጣል።

# አንጎልን ማጨናነቅ

በአንድ ጊዜ ብዙ ነገሮችን ለመሥራት መሞከር በአእምሮ ላይ ጫና ይፈጥራል፡፡ በአንድ ጊዜ በርከት ያሉ ሥራዎችን መሥራት ቅልጥፍናን እንደሚቀንስ፣ ለስሕተት እንደሚዳርግ፣ ብሎም በሽጻን እንደሚያስከትል አናዳንድ ጥናቶች አመልክተዋል፡ ፡ ለምሳሌ ያህል፣ የማስታወስ ችሎታን ሊያዳክም እና የወፈ,ገብ ሕመም ሊያስከትል የሚችል ከመሆኑም በላይ፣ አንድ ሰው በጉንፋን እና በምግብ አለመፈጨት ችግር በቀላሉ ሊጐዳ ይችላል፡፡
የዩ.ኤስ. አሜሪካ ብሔራዊ የጤና ተቋማት ባካሄዱት አንድ ጥናት መሠረት፣ ሰዎች አንዳንድ ሥራዎችን በሚያከናውኑበት ወቅት በአንጎል ውስጥ ያሉ የተለያዩ ክፍሎች መሥራት ይጀምራሉ፡፡ መኮና እያሽከረከሩ በተንቀሳቃሽ እንደመነጋገር ያሉ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ነገሮችን በአንድ ጊዜ ለመሥራት በሚሞክሩበት ጊዜ ግን፣ "አንጎላቸው መቆለፍ ይጀምራል፡፡ አንጎላች ሥራውን አለመሥራት ብቻ ሳይሆን፣ ለመሥራትም ፈቃደኛ አይሆንም" ሲሉ በኤመሩ ዩኒቨርሲቲ የነርቭ እስፔሽያሊስት የሆኑት ዶክተር ጆን ስላኬ ተናግረዋል፡፡ የዘርፉ ተመራማሪዎች እንደሚሉት፣ ሰዎች ረጋ ብለው መሥራት እና አንጎላቸው የጠየቁት ነገር ሁሉ ሊሠራላቸው እንደማይችል አምነው መቀበል አለባቸው፡፡

# መሳሳም እና ጀርም

መሳሳም የጊዜያዊም ሆነ የዘላቂ ፍቅር ዓለም ዓቀፋዊ ምልክት ነው ማለት ይቻላል። ይሁን እንጂ፣ መሳሳም ከዚህኛው በጎ እሳቤ ያፈነገጠ ጐጂ ጐን እንዳለውም የእንግሊዝ ሳይንቲስቶች እየተናገሩ ነው። እንደሳይንቲስቶቹ ከሆነ፣ በሽታ አማጪ ተሕዋስያን "ሳይቶሜጋል ቫይረስ"፣ በተለይም ጀርሙ የተላለፈው በእርግዝና ወቅት ከወንዱ ወደሴቷ ከሆነ፣ ለፅንሱ በጣም አደገኛ ነው። "ሳይቶሜጋል ቫይረስ" የተሰኘው እና በምራቅ ውስጥ የሚኖረው ተሕዋስ አብዛኛውን ጊዜ ምንም ችግር የማይፈጥር ቢሆንም፣ በእርግዝና ወቅት እጅግ አደገኛ ሊሆን ይችላል። ከዚህ በተጨማሪም፣ በማሕፀን ውስጥ ያለን ሽል ሊገድል ወይም በውልደት ወቅት ችግርን ሊያመጣ እንደሚችል ሳይንቲስቶች ይናገራሉ።
ሜዲካል ሃይፖቴሲስ በተሰኘው ጆርናል ላይ ጽሑፋቸውን ያሰፈሩት የሊድስ ዩኒቨርሲቲው ተመራማሪ ዶክተር ኮሊን ሄንድሪ፣ "የአንዲት ሴት በተለየ የወንድ ሳይቶሜጋል ቫይረስ መከተብ ይበልጥ እውን የሚሆነው በአፍ ለአፍ ግንኙነት እና በምራቅ ልውውጥ፣ በተለይም ምራቅ ከወንዱ ጋር ያላት ግንኙነት የአጭር ጊዜ ወደሆናት ሴት ሲፈስ ነው" ብለዋል።
እንዲህ ሆኖ ግን፣ ተመራማሪው ከአንድ ሰው ጋር ከስድስት ወራት በላይ መሳሳም የሴቷ የቅስመ-ተፈጥሮ መከላከያ ሥርዓት እንዲገነባ ጊዜ ስለሚሰጠው የበሽታውን አደገኛነት እንደሚያስወግደው አልሸሸጉም። በአንጻራዊነት ሲታይ፣ በመጀመሪያው የመሳሳም ወቅት አነስተኛ መጠን ያለው ቫይረስ በሴቷ ላይ ሕመም የሚያስከትል ሲሆን፣ ግንኙነቱ በዘለቀ ቁጥር እና መሳሳሙም ይበልጥ ጥልቅ እየሆነ በሄደ መጠን ሰውቷ የቅስመ-ተፈጥሮ መከላከያ ሥርዓቱን እየገነባ ስለሚሄድ፣ እየለመደው ይመጣል። ስለዚህም፣ በረዥም ጊዜ ግንኙነቱ መኻል ብታረግዝ ፅንሱ በሽታውን የመከላከል ዓቅሙ ዝቅተኛ እንደሚሆን አረጋግጠዋል።
ከዚህ በፊት ሳይንቲስቶች መሳሳም ያለውን ጠቀሜታ ብቻ ሲገልጹ የቆዩ ቢሆንም፣ የሊድስ ዩኒቨርሲቲው ተመራማሪ ጐጂ ጐንም አለው እያሉ ነው። በመሳሳም ዙሪያ የወጣው ይኸው አዲስ መረጃ፣ በመሳሳም ዙሪያ የሚኖረው ጫና ወይም ግፊት እጅግም ነው የሚሉ ወገኖችም አሉ።

# የቀዶ ሕክምና ባለሙያዎች ብዛት (ለ100,000 ሕዝብ)

- ግሪክ - 166
- ጣልያን - 114
- ስዊድን - 113
- ጀርመን - 112
- ስፔይን - 109
- ዩናይትድ ኪንግደም - 90
- ሩሲያ - 88
- አውስትራሊያ - 72
- ቤልጂየም - 65
- ፈረንሳይ - 58
- ዩ.ኤስ. አሜሪካ - 54
- ግብጽ - 50
- ቱርክ - 50
- ቻይና - 40
- ጃፓን - 37
- ካናዳ - 35
- ብራዚል - 34
- አርጀንቲና - 10
- ሕንድ - 6
- ኢራን - 5
- ናይጄሪያ - 1

(ምንጭ፡- ላንሴት መጽሔት)

አዘጋጅ፡- ማውሮ

## "አላስታውሰውም"

ከአልበርት ኧንስታይን የሥራ ባልደረቦች መካከል አንዱ ስልክ ቁጥሩን ይጠይቀዋል፡፡ ኧንስታይንም የስልክ ቁጥር ማውጫውን ወደእሱ ጠጋ አድርጎ ካገላበጠው በኋላ ስልክ ቁጥሩን ይሰጠዋል፡፡ በዚህ የተገረመው የኧንስታይን የሥራ ባልደረባ፣ "የራስህን ስልክ ቁጥር እንዴት ማስታወስ አትችልም?" ሲል ይጠይቀዋል፡፡ ይህን ጊዜ ኧንስታይን፣ "አላስታውሰውም፡፡ ከመጽሐፍ ላይ በቀላሉ ማግኘት የምችለውን ነገር ለምንድን ነው በቃሌ የማጠናው?" ሲል ጥያቄውን በጥያቄ መለሰለት፡፡ ኧንስታይን ከሁለት ደቂቃዎች ባነሰ ጊዜ ውስጥ አንብቦ ማወቅ የሚችለውን ነገር ፈጽሞ በቃሉ የማጥናት ፍላጎት አልነበረውም፡፡

## ጥቂት ነጥቦች ስለዝኆን

- ዝኆን ውኃ ከመሬት ሥር ቆፍሮ ከማውጣቱ በፊት የከርሰ-ምድሩ ውኃ በስንት ሜትር ጥልቀት እንደሚገኝ የሚያሰላው ከፍተኛ የማሽተት ኃይል ባለው ኩምቢው አማካኝነት ነው።
- ትላልቅ ዛፎችን ከሥራቸው መንግሎ ለመንቀል የሚያገለግለው የዝኆን ኩምቢ፣ እንደመጥረቢያ፣ መከትከቻ እና መኮትኮቻ ጭምር ያገለግላል።
- ዝኆን አዳኝ አንበሳን እና ነብርን ታግሎ የሚያሸንፈው እና መንጋውን ከጠላት የሚታደገው ኩምቢውን እንደጦር መሣሪያ በመጠቀም ነው።
- ብዛቱ እየተመናመነ የመጣውን የዝኆን ዝርያን ለመታደግ የዝኆን ጥርስ ዝውውር እና ሽያጭ በ1989 (እ.አ.አ.) በዓለም ዓቀፍ ሕግ ታግዷል።
- ከ1979-89 (እ.አ.አ.) ባሉት ዐሥር ዓመታት ውስጥ ብቻ 600,000 የአፍሪካ ዝኆኖች በአዳኞች ተገድለዋል።
- ቀደም ባሉት ዓመታት በደቡብ አፍሪቃ እና በሕንድ የነበሩ የመንገድ ቀያሽ መሃንዲሶች አቋራጭ፣ ምርጥ እና ውጤታማ የሚሉትን የመንገድ ቅያስ የሚያወጡት የዝኆንን ዱካ  እና ኮቴ በመከተል ነበር።
- ዝኆን ከፍተኛ የማስተዋል ችሎታ ያለው የዱር እንስሳ ነው።
- ዝኆኖች የሚነጋገሩት በሹክሹክታ ቢሆንም፣ ሰላምታ የሚለዋወጡት በከፍተኛ ድምፅ ነው።
- ትላልቆቹ የዝኆን ጆሮዎች ከብዙ ኪሎ ሜትሮች ርቀት ያለን ሹክሹክታ ማዳመጥ ይችላሉ፤ በዚህ ርቀት ላይ ሆነውም እርስ በርስ መነጋገር ይችላሉ።
- የዝኆን ዓይኖች ሚጢጢ ናቸው፤ በዓይኖቹ አናሣነት የተነሣ ከርቀት አጥርቶ መመልከት ይቸግረዋል፡፡

## አስገራሚ አሟሟት

ኤሚ ሮዝ ኮክስላ የተባለች አንዲት እንግሊዛዊት የ16 ዓመት ኮረዳ ትምህርቷን ለመከታተል ወደሆንግ ኮንግ ታመራለች፡፡ ታዲያ፣ አንዱን ቀን የዘመኑ ፋሽን የነበረ ቁንጠኛ ሻርፕ በአንገቷ ዙሪያ አስራ ብስክሌት ስትጋልብ የአንገት ፎጣው አንድ ጫፍ በጎማው ራጅ ውስጥ ይጠላለፋል፡፡ በዚሁ ሳቢያም ሻርፑ አንገቷን አንቆ ለሞት ሊዳርጋት ችሏል፡፡

## ወንጀል የሚያስከትለው ኪሳራ

በዩ.ኤስ. አሜሪካ ውስጥ በየቀኑ 94,000 የወንጀል ድርጊቶች እንደሚፈጸሙ የፍትሕ ዘርፉ ይገምታል። ኤድ ሩበንስታይን የተባሉ ኢኮኖሚስት እንደተናገሩት፣ መኪና፣ ገንዘብ እና ጌጣጌጦች የመሳሰሉ ነገሮችን በመዝረፍ፣ በቀጥታ የሚደርሰው ኪሳራ በዓመት 20 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ይደርሳል። በዚህ ላይ ፍርድ ቤት፣ ወኅኒ እና ጥበቃ ለመሳሰሉ ሕግ አስከባሪ አካላት የሚመደበው ወጪ ሲጨመር ጠቅላላው ኪሳራ ወደ 100 ቢሊዮን ይደርሳል። ከዚህም ሌላ፣ የወንጀል ሰለባ የሆኑ ብዙ ሰዎች ድንጋጤ፣ ፍርሃት እና ጭንቀት ስለሚሰማቸው እነዚህን አፍራሽ ስሜቶችን ለመቋቋም ከሥራ ቀርተው እቤት ይውላሉ። ስለዚህም፣ በወንጀሉ ሂደት ምርታማነት እንደሚቀንስ ሲገመት፣ ወንጀል የሚያስከትለው ጠቅላላ ኪሳራ በየዓመቱ "ከ250 እስከ 500 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ይደርሳል" በማለት ሩበንስታይን ይገምታሉ።

## ይህን ያውቁ ኖሯል?

- አፍንጫችንን ማየት ብንችልም፣ አንጎላችን ይህን ችሎታችንን ዘወትር ችላ እንዳለው ነው፡፡
- በአንድ ጥናት መሠረት፣ ዕድሜያቸው አራት ዓመት የሆናቸው ሕፃናት ይበልጥ ጓደኝነት መመሥረት የሚፈልጉት እነሱ የሚያውቁትን ዘፈን ከሚያውቁ ልጆች ጋር ነው፡፡
- በምድር ላይ ካሉት የአሸዋ ቅንጣቶች ይልቅ በሰማይ ያሉት ከዋክብት ብዛት ይበልጣል፡፡
- ጐርምጥ (ኦክቶፐስ) የተባለው የባሕር እንስሳ ሦስት ልቦች አሉት፡፡
- ሴቶች የሥጋት ምንጭ አድርገው ስለሚመለከቷቸው የሌሎች ቆንጆ ሴቶችን መልክ በማስታወሱ ረገድ ከወንዶች የተሻሉ ናቸው፡፡
- ተመራማሪዎች እንደሚገምቱት፣ ከሰው ልጅ መካከል ሁለት-ሦስተኛው የሚሆኑት በምን ዘርፍ ጐበዝ እንደሆኑ ወይም ጥንካሬያቸው እምን ላይ እንደሆነ አያውቁም፡፡
- ያለንበት ጋላክሲ ቢያንስ 2 ቢሊዮን ምድርን መሰል ፕላኔቶችን በውስጡ ይዟል፡፡
- በዛሬው ምሽት 1 ቢሊዮን ያህል የዓለማችን ሕዝብ ተርቦ ያድራል፡፡
- ኖርዌይ ውስጥ "ገሃነም" የሚል ትርጉም ባለው እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ "Hell" በሚለው ስያሜ የምትጠራ አንዲት ከተማ አለች፡፡
- እንግሊዝ ውስጥ በተካሄደ አንድ ጥናት መሠረት፣ እርቃናቸውን የሚተኙ ጥንዶች ልባሳቸውን ለብሰው ከሚተኙት ጋር ሲነፃፀሩ፣ በፍቅር ግንኙነታቸው ይበልጥ ደስተኞች ናቸው፡፡

## ለፈገግታ ያህል

ጆን፡- ወንድም፣ አጠጣጥህ ፍጹም አላማረኝም። አልኮል መጠጥ የጤናህ ጠላት አይደል፣ እንዴ?
አንድርው፡- በእርግጥ፣ ጠላት ነው።
ጆን፡- ታዲያ፣ ለምንድን ነው ይህን ያህል አብዝተህ የምትጠጣው?
አንድርው፡ ምን ታደርገዋለህ? ታላቁ መጽሐፍ "ጠላትህን እንደራስህ አድርገህ ውደድ" ማለቱን ዘነጋኸው፣ እንዴ?

***

መኖሪያ ቤት ለመግዛት የሚፈልግ አንድ ሰው ጋዜጣ ሲያገላብጥ አንድ የሽያጭ ማስታወቂያ ይመለከታል። ማስታወቂያው ስለቤቱ ውበት ካተተ በኋላ ቤቱ ከከተማው መኻል የድንጋይ ውርወራ ያህል እንደሚርቅ ይገልጻል። ቤት ፈላጊውም በተባለው አድራሻ ቤቱን ፈልጎ ካገኘ በኋላ ርቀቱ እንደተባለው ሳይሆን፣ ከከተማው ሊወጣ ምንም አልቀረውም። ጉብኝቱን ጨርሶ ሊሄድ ሲልም ሻጩን፣ "እንዲያው ለመሆኑ፣ ከከተማው መኻል እዚህ ድረስ ድንጋይ የወረወረውን ግዙፍ ሰው ያሳዩኛል?" ሲል በብሽቀት ጠየቀው።

***

ቄሱ ስብከታቸውን ሲጀምሩ፣ "ፍቅር ምንድን ነው?" ብለው ከምዕመናኑ መካከል አንዷን ይጠይቃሉ። ካህኑ የጠበቁት ምላሽ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተ ትርጉም እንዲኖረው ፍላጎታቸው ነበር። ሆኖም፣ ተጠያቂዋ ምእመን፣ "አባቴ፣ እንዲህ ዓይነቱን የማይረባ ጥያቄ ባያቀርቡልኝ ደስ ባለኝ ነበር። ጥያቄዎን ለመመለስ ያህል ግን፣ ፍቅር ጊዜያዊ የአእምሮ መናጋት መሆኑን እርስዎም የእኔን ያህል ሳያውቁት አይቀሩም ብዬ እገምታለሁ" አለች።

## ጥንታዊት ስፓርታ

በጥንት ስፓርታ የከተማ መንግሥት ሕግ መሠረት፣ እያንዳንዱ የከተማዋ ዜጋ ከተወለደበት ጊዜ አንሥቶ እስከ ዕለተ-ሞቱ ድረስ የመንግሥት ንብረት ነው፡፡ አንድ ሕፃን ተወልዶ ሰባት ዓመት እስኪሞላው ድረስ ወታደራዊ ማሠልጠኛ ካምፕ በመግባት፣ ጥብቅ የአካል ብቃት እና የዲሲፕሊን ትምህርት ይሰጠዋል፡፡ ዜጋው ከ20 እስከ 60 ዓመት ዕድሜው መንግሥት ላዘዘው ወታደራዊም ሆነ ሌላ ማንኛውም ዓይነት ሕዝባዊ ግዴታ ራሱን በሙሉ ታማኝነት አዘጋጅቶ ጊዜውን፣ ሕይወቱን እና ጉልበቱን ለዚሁ ዓላማ ይሠዋል፡፡ በዚያን ዘመን አንድ ሕፃን ልጅ እንደተወለደ ልፍስፍስ ወይም ሕመምተኛ ሆኖ ከተገኘ፣ በመንግሥት ትእዛዝ ይገደላል፡፡ ይህ ዓይነቱ እርምጃ የሚወሰደውም የስፓርታ መንግሥት ጠንካራ ዜጋ ብቻ ለማፍራት ያለውን ዓላማ ለመተግበር ነው፡፡

## አስገራሚ የፍቺ ምክንያት

በግብረ-ሥጋ ግንኙነት ወቅት የብልት ቅጥያው በመውለቁ፣ ሚስቱ የፈታችው አንድ ሩሲያዊ በሁኔታው ቅስሙ መሰበሩን ተናግሯል፡፡ በደቡብ ሩሲያ፣ ቮሮኔዥ ከተማ የሚገኙ ሐኪሞች ለ47 ዓመቱ ግሪጎሪ ቲፖሬቭ የብልት ቅጥያውን የገጠሙለት የሚስቱን "አልጋ ውስጥ አታረካኝም" የሚለውን ተደጋጋሚ ቅሬታ ለማስቀረት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ ባል እና ሚስት በአንድ ምሽት አንሶላ በሚጋፈፉበት ወቅት የብልት ቅጥያው ሲወልቅ ባለቤቱ ክፉኛ መደንገጧ እና መበሳጨቷ አልቀረም፡፡ ግሪጎሪ አዲስ የብልት ቅጥያ እንደሚያስገጥም ለሚስቱ ቢገልጽላትም፣ በአልጋ ውስጥ ድክመቱ በመማረሯ ልትፈታው ወስናለች፡፡

## ከዊንስተን ቸርችል አንደበት

የቀድሞው የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ዊንስተን ቸርችል፣ በአንድ ወቅት በዩ.ኤስ. አሜሪካ ተገኝተው ንግግር በሚያደርጉበት አጋጣሚ ብዙ ሕዝብ ተሰብስቦ ነበር፡፡ የቸርችልን ንግግር ለማዳመጥ በተሰበሰበው ሕዝብ ብዛት የተገረመች አንዲት ሴት፣ "ብዙ ጊዜ እርስዎ ንግግር ሲደርጉ ብዙ ጊዜ የስብሰባ አዳራሾች በሕዝብ ይጨናነቃሉ፡፡ ለመሆኑ ንግግር በሚያደርጉበት ጊዜ ስለሰዎቹ ብዛት ምን ይሰማዎታል?" የሚል ጥያቄ ታቀርብላቸዋለች፡፡ ቸርችልም፣ "የእኔ እመቤት፣ የሆነ ጥፋት አጥፍቼ ብሰቀል ኖሮ፣ ከዚህ የበለጠ ብዙ ሕዝብ እንደሚሰበሰብ ይሰማኛል" የሚል ምላሽ ሰጧት፡፡

## የዓለም ሀገራት

አጠቃላይ የዓለም ሀገራት ቁጥር 195 ደርሷል። 195ኛዋ አዲሷ ሉዓላዊት ሀገር ደግሞ፣ ደቡብ ሱዳን ናት። ከ195ቱ የዓለማችን ሀገራት መካከልም የተባበሩት መንግሥታት አባላት 192 ናቸው። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን በቅርቡ የተቀላቀሉት ሀገራት ደግሞ፣ ስዊዘርላንድ (2002 እ.አ.አ.) እና ሞንቴኔግሮ (2006 እ.አ.አ.) ናቸው። ከ1990 (እ.አ.አ.) ወዲህ ብቻ 29 አዳዲስ ሀገራት ተፈጥረዋል። ከእነኝህ አዳዲስ ሀገራት መካከልም 14ቱ ከቀድሞዋ ሶቪዬት ኅብረት፣ እንዲሁም ሰባቱ ከቀድሞዋ ዩጎዝላቪያ መበታተን የተፈጠሩ ናቸው። ደቡብ ሱዳን 54ኛዋ የአፍሪቃ ሀገር ሆናለች። በዚህም መሠረት፣ የዓለማችን አዲሷ ርዕሰ-ከተማ ጁባ መሆኗ ነው።

### የዋጋ ግሽበት (2018 እ.አ.አ.)

- ቬኔዙዌላ - 12615%
- ቱርክ - 12%
- ፓኪስታን - 5%
- ሕንድ - 4.7%
- ሜክሲኮ - 4.4%
- ሳውዲ ዐረቢያ - 4.4%
- ኢንዶኔዢያ - 3.5%
- ብራዚል - 3.5%
- ሩሲያ - 2.9%
- ዩ.ኤስ. አሜሪካ - 2.5%
- ዩናይትድ ኪንግደም - 2.4%
- ካናዳ - 2.2%
- ቻይና - 2.2%
- ማሌዢያ - 1.9%
- ፈረንሳይ - 1.9%
- ጀርመን - 1.8%
- እስራኤል - 1.7%
- ደቡብ ኮሪያ - 1.7%
- ጣልያን - 1.2%
- ጃፓን - 1%

(ምንጭ፡- ስቴኪታተር ኢንዴክስ)

## እርስዎም ይሞክሩት ጥያቄ

1. ከፈረንሳዩ ንጉሠ-ነገሥት፣ ናፖሊዮን፣ ውድቀት በኋላ አውሮጳ ውስጥ ሰላም ያሰፈነው ጉባዔ ምን ተብሎ ይጠራል?
2. የባስክ ሕዝብ የት ይገኛል?
3. በሕንድ የምትገኘው ቼናይ ከተማ የቀድሞ መጠሪያ ማን ነው?
4. የታላቁ እስክንድር አያት ማን ነው?
5. ማሪነር 10 ወደየትኛዋ ፕላኔት የተጓዘ የጠፈር መንኮራኩር ነበር?

መልሱን በገጽ 20 ይመልከቱ

# የነፃነት ጮራ

ከገጽ 5 የዞረ

መስጠት በውስጡ ያሉትን ብዙዎች ጎሳዎች ሰብአዊ መብት መጣስ ነው። ባሁኑ ዘመን ሰብአዊ መብት የሚጥስ ሥርዓትን የሚቀበል ሰው ኋላ-ቀር ብቻ ሳይሆን፥ ደረጃው ከሰው ደረጃ በታች ነው። መጽሐፉ፥ "አሆ በልዎ ለእግዚአብሔር ወእንብየ በልዎ ለጋኔን" እንዳለ፥ ሰብአዊ መብት ለሚያከብር ህግ እንታዘዛለን፤ ሰብአዊ መብት የሚጥስ ህግን እንቃወማለን።

በመሠረቱ፥ መንግሥትን መቀበል በገዛ ፈቃድ የግል ነፃነትን ቀንሶ ራስን መንፈግ ነው። መንግሥት የሚያወጣቸው የህግ አናቅጽ ማድረግ የማይገባንን ነገሮች የሚዘረዝሩ ናቸው። ከሌሎች ጋር ስለምንኖር፥እነዚህ ነገሮች እንዳይደረጉ መከልከላቸውን ብንወድም ባንወድም እንቀበላቸዋለን። የተከለከሉት የሰው ሰብአዊ መብት እንዳይጣስ፥ የኅብረተሰቡ ደኅንነት እንዲጠበቅ ነው።

## ትልቁ ደኻ ትንሹን ደኻ

እንደተረዳሁት፥ መንግሥቱ ፌዴራል እንዲሆን የሚፈልጉ ሰዎች በባህላቸው ላይ የተመሠረተ አሐዳዊ መንግሥት ለማቋቋም ስላልቻሉ ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት በባህላቸው ላይ የተመሠረተ ቢሆን አሐዳዊነቱን ሳያቅማሙ ይቀበሉት ነበር። ይህ ሊሆንላቸው ካልተቻላቸው፥ ከኢትዮጵያ ወጥተው (ተገንጥለው) ከሌሎች መንግሥታት ጋራ በጕርብትና የሚኖሩበት የራሳቸው አሐዳዊ መንግሥት ማቋቋም ይፈልጋሉ። ይህም ካልተቻላቸው፥ አማራጫቸው በፌዴራሉ መንግሥት ሥር ሆነው በባህላቸው ላይ የተመሠረተ የራሳቸው አሐዳዊ መንግሥት ማቋቋም ነው።

የሚጠሉትን አሐዳዊ መንግሥት መቸ እንደሚወዱት፥ መቸ እንደሚጠሉት ልብ እንበል። የሚጠሉት በባህላቸው ባልተቋቋመ መንግሥት ሥር መኖርን ሆኖ ሳለ፥ እነሱ በባህላቸው በሚያቋቁሙት አሐዳዊ መንግሥት ሥር ስፍር ቍጥር የሌላቸው ሌሎች ቢኖሩ ደንታ የላቸውም። ሥነ ምግባር ያለው ሰው ራሱ የሚጠላውን በሌሎች ላይ አያደርስውም። ሰብአዊ መብት የሚጥስ ሥርዓትን ለመዘርጋት የሚጥር ሰው ደረጃው ከሰው ደረጃ በታች ነው። ትልቁ ደኻ ትንሹን ደኻ አይወደውም ይባላል።

እነዚህ ሰዎች የጥንቱ የኢትዮጵያ መንግሥት የተቋቋመው በነሱ ባህል ላይ ስላልሆነ፥ ያ አሐዳዊ መንግሥት እንዲቀጥል አይፈልጉም ብለናል። ባህሉን ለውጦ የሚመኙትን መንግሥት ለማቋቋም ደግሞ፥ አጥጋቢ ምክንያት ያስፈልጋል። ከሌለ፥ በህዝብ ሁሉ ዘንድ ቅቡልነት አይኖረውም። ምክንያቱም፥ ብንቀበለው፥ ብዙዎቻችንን መበደል ይሆናል። እስከ ዛሬ የመንግሥት ታሪክ የሌላቸው ጀማሪ ህዝብ ያደርገናል።

## ልዩ ትኵረት የሚሰጠው ጉዳይ

ከላይ "የሀገር መበታተን (የመገንጠል) መብት ልዩ ትኵረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው" ብያለሁ። የኢህአዴግ ህገ መንግሥት የፈለገ ጎሳ ልገንጠል ቢል መብቱ ይከበርለታል የሚለው ውይይት እንደሚያስፈልገው ለማስታወስ ነው። ታሪካቸው የመገንጠል መብትን የሚያሰጣቸው ህዝቦች በሌላ ሀገር ሊኖሩ ይችላሉ። በኛ ዘንድ ግን የሉም። ያለው የህዝብ መገንጠል መብት እንጂ፥ የሀገር መገንጠል መብት የለም። ሀገር ጥሎ መሄድ የማንም መብት ነው። ማንም ህዝብ ተገንጥሎ የግል ንብረቱን ይዞ ከፈለገው ሀገር ይሄዶ ለመኖር ቢፈልግ፥ የትውልድ ሀገሩ መንግሥት መብቱን ሊነሣው አይችልም። መሬት ግን ዜጎች ለመንግሥት ኪራይ (= ግብር) እየከፈሉ የሚኖሩበት የመንግሥት ሀብት ስለሆነ፥ ማንም ሰው የኖርኩበትን ምድር ይዤው ልሂድ ቢል፥ መንግሥት ሊፈቅድለት አይገባውም። የሀገርን ሉዓላዊነት መዳፈር ነው።የመንግሥት ባለሥልጣናት ግዴታ ሀገርን መንከባከብ፥ ከተቻለም ማስፋፋት እንጂ፥ መበታተንስ የጠላት ሥራ ነው። አይታሰብም።

በመጨረሻም፥ ምርጫው ርቱዕ እንዲሆን የጠቅላይ ሚኒስትሩ ፍላጎት እንደሆነ የሰማሁትን አምናለሁ። ግን በብዙ ወንጀል፥ በተለየም በህዝብ ማፈናቀል፥ የመንግሥት ሠራተኞች እጅ እንዳለበት ስለተረጋገጠ፥ የምርጫው ሂደት ርቱዕ የሚሆነው እነዚህ ስውር እጆች ሲቈረጡ ነው። ለምሳሌ፥ አሁን ባለንበት ሁኔታ አንድነትን ዓላማቸው ያደረጉ ፓርቲዎች አሮሞዎች በሰፈሩበት አካባቢ በነፃ ሊንቀሳቀሱ አይችሉም። ስለዚህ ምርጫው ተአማኒነት እንዲኖረው፥ መንግሥት ይኸንን አስቀድሞ ማስተካከል አለበት። ማፈናቀሉ ላይ የመንግሥት ሠራተኞች እጅ አለበት በተባለው አካባቢ መንግሥት ህጋዊ እርምጃ መውሰዱን ሰምተናል። እውነት ከሆነ ትልቅ ብሥራት ነው። ምርጫውንም ርቱዕ ያደርገዋል።

የለውጡ ግሥጋሤ አብዛኛው ህዝብ የሚፈልገው እንዲሆንና እንዲሠምር፥ ህዝባችን የእኩልነት መብቱ ተጠብቆ በሰላም እንዲኖር ድምፃችንን ለኢትዮጵያ መንግሥት፥ ጸሎታችንን ለኢትዮጵያ አምላክ ማሰማታችንን አናቋርጥም።

# የዶላር እጥረት፣ የዋጋ ...

ከገጽ 7 የዞረ

የእዳ መክፈል ችግር ብቻ ሳይሆን፣ በዕዳ ላይ ዕዳ ይቆልላል:: የተበደርነውን በትክክል የመጠቀም አቅም እንዳይኖረን ያደርጋል፤ ጥገኝነት እንዲቀጥል ያደርጋል::

በዚያ ላይ፣ መንግስት የተበደረውን ሁሉ ለትክክለኛ ዓላማ አያውልም:: ብዙ ገንዘብ ባክኖ ይቀራል፤ ብዙ ገንዘብ "ነጭ ዝሆን" በመባል ለሚታወቁ ትልልቅ የታይታ ፕሮጀክቶች ውሏል፤ ሲያዮዋቸው ለሀገር ክብር ተብለው የተሰሩ፣ ዕዳቸውን ለመክፈል ግን አስቸጋሪ ስለሆኑ ዕዳ አከማችተዋል::

ብድር ማግኘት ብቻ ሳይሆን፣ "መክፈል ይቻላል ወይ?" የሚለውን አመዛዝኖ ብድሩን ማጽደቅ የፓርላማ ስራ ነበር፤ ብድሩን ሲያፀድቁ የመክፈል አቅምን መመልከት ይገባቸዋል:: ለፖለቲካ ፍጆታ፣ ለገፅታ፣ ወይም ለምርጫ ተብሎ ሳይሆን፣ ሀገርን ለመለወጥ ካለው አቅም አኳያ ተመዝኖ፣ ከዚያም የመክፈል አቅማችን ተለክቶ፣ የሚያወጣ ከሆነ ብቻ ነው ብድር መፅደቅ ያለበት::

ጫናው ለትውልድ እንዳይተላለፍ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል:: ከገንዘብ ሚኒስተር፣ ብሄራዊ ባንክና ፖርላማ በተጨማሪ፣ የሀገር ውስጥ ንግድ ግምት ውስጥ እንዲገባ የንግድ ሚኒስተር፣ እንዲሁም፣ አብዛኛው ህዝብ የሚተዳደርበትን ግብርናን የሚቆጣጠረው ሚኒስትር መስሪያ ቤት ኃላፊነት አለባቸው::

ከዚህ በፊት ተሰርዞልናል፣ አሁንም ይሰረዝልናል፣ ብሎ መጠበቅ አደገኛ ነው:: በተደጋጋሚ ተሰረዘልን ማለት ሁሌ ይሰረዝልናል ማለት አይደለም:: ባልጠበቅነው ሰዓት "ክፈሉ" ብለው ሊያፋጥጡን ይችላሉ:: ያኔ ከሚከሰተው ቀውስ ባሻገር፣ እንደ ሀገር የሚጠለሸው ስማችን የበለጠ ጉዳት ያስከትላል፤ አንዴ የጠፋን ስም መልሶ ለማደስ እጅግ አዳጋች መሆኑን የብዙ ሀገራት ተሞክሮ ያስተምራል:: የእዳ ወጥመድ ውስጥ በመግባት የአገሪቱን ሉአላዊነት የሚፈታተን ችግር ውስጥ እንዳንገባ ያሰጋል::

### ቻይና ችግር

የዓለም ባንክን የመሳሰሉት የፋይናንስ ተቋማት የየሀገራቱን የብድር የመክፈል አቅም በዝርዝር ያጠናሉ:: ብድር ሲሰጡ ዝም ብለው አይሰጡም:: የቻይና ችግር ግን፣ መክፈል መቻሉን በቅድሚያ የሚያጤኑ አይመስሉም :: ብድሩ የተበዳሪውን ሀገር ህጋዊ መንገድ ተከትሏል ወይ? የሚለውንም ለማወቅ የሚሄዱበት መንገድ ደካማ ይመስለኛል:: ለማበደር እጃቸው ላላ ያለ ነው፣ በእጅ አዙር የሚጠብቁት ነገር ቢኖርም፣ ብድሩን ከረዥም ጊዜ ዕቅዳቸው አኳያ ነው የሚመዝኑት::ቻይናዊያን 40 እና 50 ዓመታት ወደፊት አርቀው የማየት አቅም አላቸው፤ ምዕራባዊያን ተቃራኒ ናቸው::

የቻይና ልል እጅ ብዙ ውዝግብ ቀስቅሷል:: ለምሳሌ፣ በዛምቢያና በሌሎች ሀገራት ቅሬታ እየቀረበባቸው ይገኛል::"ቻይና የብድር ወጥመድ ውስጥ እያስገባችን ነው"ይላሉ:: ይህ እውነት መሆኑንና አለመሆኑን ለመለየት ጥናት ይጠይቃል፤ ጥናቱም ቢኖር ቀላል መልስ አይኖረውም:: የሀገራችንን ብድር ከዚህም አኳያ መገምገም እንዳለብን ይሰማኛል::

# የአሜሪካ ልውካንና የዐቢይ...

ከገጽ 10 የዞረ

ከአፍሪቃ ሀገራት፣ በተለይም ከኢትዮጵያ፣ ጋር ያላቸው ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ነው:: ፕሬዚዳንት ኢሳይያስ መጋቢት 3/2019 (እ.አ.አ.) ከኬንያው ፕሬዚዳንት፣ ኡሁሩ ኬንያታ፣ እና ከኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ዐቢይ አሕመድ፣ ጋር በአስመራ ተገናኝተዋል፤ የኤርትራ መንግሥታዊ ሚዲያ የሦስቱን ሀገራት መሪዎች ግንኙነት "የሦስትዮሽ ጉባዔ" ሲል ገልጾታል:: በወቅቱ፣ ፕሬዚዳንት ኬንያታ ብዙም ሳይቆዩ ወደሀገራቸው ሲመለሱ፣ ፕሬዚዳንት ኢሳይያስ ግንባታቸውን በቅርበት የተከታተሏቸውን የግድብ ሥራዎች ለጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አስጐብኝተዋል:: (በነገራችን ላይ፣ አስመራን ጨምሮ፣ በርካታ የኤርትራ ከተሞች የንጹሕ ውኃ እጥረት ችግር አለባቸው፤ ባለፈው ነሐሴ ወር 300 የውኃ ቦቴዎች የውኃ እጥረት ላለባቸው ከተሞች ውኃ እንዲያከፋፍሉ በዘመቻ መልኩ እንዲሰባሰቡ ተደርጎ ነበር::)

በቀጣይነትም፣ ፕሬዚዳንት ኢሳይያስ እና ጠቅላይ ሚኒስትር ወደደቡብ ሱዳን በመብረር ከፕሬዚዳንት ሳልቫ ኪር ጋር ተገናኝተዋል:: በየሀገሮቻቸው ከከባድ እና አሳሳቢ ችግሮች ጋር የተፋጠጡት የሦስቱ ሀገራት መሪዎች፣ ለሀገር ውስጥ ጉዳዮች ትኩረት ከመስጠት ይልቅ፣ በክልላዊ የኢኮኖሚ ውሕደት ዙሪያ ተወያይተዋል::

## "መሪያችን ነህ"

ኤርትራ እና ኢትዮጵያ ለሁለት ዐሥርት-ዓመታት ከገቡበት ፍጥጫ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከተላቀቁ ወዲህ በሀገራቱ መሪዎች መካከል እየታየ ያለው ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት፣ በርካታ ኤርትራውያንን እያስጨነቃቸው ነው:: ኤርትራውያን ፕሬዚዳንት ኢሳይያስ በሐምሌ 2018 (እ.አ.አ.) ኢትዮጵያን ከጐበኙ በኋላ የሚያደርጓውን ንግግሮች በጥሞና እየተከታተሉ ነው:: የኤርትራውያንን ፍርሃት እና ጭንቀት ትክክለኛ የሚያደርገውም የፕሬዚዳንት ኢሳይያስ ተለዋዋጭ ፀባይ ነው:: ፕሬዚዳንቱ በሐዋሳ ተገኝተው ባደረጉት ንግግር፣ "ከአሁን በኋላ፣ ኤርትራ እና ኢትዮጵያ ሁለት ሕዝቦች ናቸው የሚል ሰው ከእውነታው የራቀ ነው" ብለው ነበር:: በቀጣይነትም፣ ዐቢይ "መሪያችን ነህ" ያሉት ፕሬዚዳንት ኢሳይያስ፣ "የኤርትራን አመራር እና ሥልጣን ሙሉ ኃላፊነት ሰጥቼዋለሁ" ብለዋል::

## አሳሳቢ ጉዳዮች

ፕሬዚዳንት ኢሳይያስ ከሐምሌ 2018 (እ.አ.አ.) ወዲህ ከካቢኔ ሚኒስትሮቻቸው ጋር አንድ ጊዜ ብቻ ሲሰበሰቡ፣ ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ጋር ግን ዘጠኝ ጊዜ ተገናኝተዋል:: ኤርትራውያኑን ሊያሳስባቸው የሚገባው ግን፣ ዩ.ኤስ አሜሪካ እና ኢትዮጵያ በኤርትራ ላይ እያሳደሩት ያለው ተጽዕኖ ብቻ አይደለም:: የሬውተርስ የዜና ወኪል በነሐሴ 2018 (እ.አ.አ.) እንደዘገበው፣ የተባበሩት ዐረብ ኤሚሬቶች ከኤርትራ የወደብ ከተማ፣ አሰብ፣ እስከ አዲስ አበባ የሚደርስ የነዳጅ ዘይት ማስተላለፊያ ቧንቧ የመዘርጋት ዕቅድ አላት:: የኤርትራ መንግሥት እስካሁን ድረስ ይህን አስመልክቶ ምንም ዓይነት መግለጫ አልሰጠም:: በቀጣይነት ደግሞ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በጥር 2019 (እ.አ.አ.) በስዊዘርላንድ፣ ዳቮስ-ክሎስተርስ በተካሄደው የዓለም ኢኮኖሚ ፎረም ኢትዮጵያ፣ ኤርትራ እና ጂቡቲ የተለያዩ ጦር ኃይሎች እና ኤምባሲዎች እንደማያስፈልጓቸው ተናግረዋል:: ከጥቂት ቀናት በኋም፣ ዐቢይ ከጣልያን ጠቅላይ ሚኒስትር ጋር ተገናኝተው መወያየታቸውን እና አዲስ አበባን ከምጽዋ ጋር የሚያገናኝ የባቡር መሥመር ለመዘርጋት መስማማታቸውን የጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ በትዊተር ገጹ አስታውቋል፤ ኤርትራውያን ዲያስፖራዎች በበኩላቸው፣ ስምምነቱን አጥብቀው አውግዘዋል:: የኤርትራ ማስታወቂያ ሚኒስትር፣ የማነ ገብረ መስቀል፣ ተቃውሞውን ለማብረድ በማሰብ፣ በዕቅድ ደረጃ የተያዘው የባቡር መሥመር "ሦስቱ ሀገራት ቀደም ሲል ባካሄዷቸ ውይይቶች የተዳሰሰ የትብብር መስክ" ነው ሲሉ በትዊተር ገጻቸው ገልጸዋል:: ይሁን እንጂ፣ ጉዳዩ በዚህ የሚያበቃ አልሆነም:: የቀድሞው የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ-መስተዳድር፣ ለማ መገርሳ፣ ኢትዮጵያ ባሕር ኃይል መገንባት ለምን እንዳስፈለጋት ሲያብራሩ፣ "አይታወቅም፤ ምናልባት፣ ወደፊት የባሕር በር ይኖረን ይሆናል" የሚል ምላሽ ሰጥተጠው ነበር::

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ባለፈው ወር በተካሄደው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች ስብሰባ ላይ ለኢትዮጵያ አንድነት አጽንኦት ከመስጠታቸውም ሌላ፣ "ኢትዮጵያ አትፈርስም፤ እንዲያውም፣ ቀደም ሲል ከኢትዮጵያ የተነጠሉት ሀገራት መመለሳቸው የጊዜ ጉዳይ ነው" ሲሉ ተናግረዋል:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ በስም ባይገልጹትም፣ በንግግራቸው ላይ በተዘዋዋሪ መጠቆም የፈለጉት ኤርትራን እንደሆነ ግልጽ ነው::

## እንደድምዳሜ

በባሕር ማዶ የሚገኙ የኤርትራ ብዙኃን መገናኛዎች እነኝህን ሁኔታዎች በቅርበት እየተከታተሏቸው ነው:: በአሁኑ ወቅት በስደት ላይ የሚገኙ የቀድሞ የኤርትራ የነጻነት ታጋዮች፣ ፕሬዚዳንት ኢሳይያስ በኤርትራ ሉዓላዊነት ላይ ያላቸውን አሻሚ አቋም ለመግለጽ በትግሉ ወቅት የነበሩ የተለያዩ ገጠመኞችን እንደአብነት እያቀረቡ ነው::

የኤርትራ ሕገ-መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን ሊቀ-መንበር የነበሩት በረከት ሀብተ ሥላሴ፣ የኤርትራን ጉዳይ በቅርበት ከሚከታተለው ማርቲን ፕላውት ጋር በቅርቡ ባደረጉት ቃለ-ምልልስ፣ "የፕሬዚዳንት ኢሳይያስ ውሳኔ ኤርትራን ለኢትዮጵያ አሳልፎ የሚሰጥ" እንደሆነ ተናግረዋል::

## መልስ

1. የቪዬና ኮንፈረንስ
2. ስፔይን
3. ማድራስ
4. ካልሳዊ አምይንታስ
5. ሜርኩሪ

# ኢትዮጵያ ወደቀድሞው አፋኝ...

ከገጽ 11 የዞረ

ጉዳና እንድትጓዝ ከተፈለገ፣ ወሳኝነት አለው::

ከዚህ በተጨማሪም፣ በኢኮኖሚው ዘርፍ ጠንካራ ሥራ መሠራት ይኖርበታል:: የሀብት አለመመጣጠን እና በወጣቱ ዘንድ የሚታየው ተስፋ መቁረጥ መቀረፍ አለበት። ወጣቶች በ2016 (እ.አ.አ.) የተጀመረው ሕዝባዊ ንቅናቄ ዋነኛ አንቀሳቃሽ ሞተሮች ነበሩ፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የሥልጣን እርካቡን የጨበጡት እነሱ ባነሱት የለውጥ ማዕበል ታግዘው ነው:: ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ካለው በየዓመቱ ሁለት ሚሊዮን አዳዲስ የሥራ ዕድሎችን መፍጠር ይጠበቅባታል::

ቨርጂ፡- እኔ በበኩሌ፣ ለሁለት ተግዳሮቶች አጽንኦት መስጠት እፈልጋለሁ:: በመጀመሪያ ደረጃ፣ ከርዕሰ-ከተማዋ፣ አዲስ አበባ፣ ውጭ ያለው ሁኔታ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል:: በተለያዩ ክልሎች መካከል ያለው ውጥረት የማዕከሉን የፖለቲካ አመራር አቅም ሊያናጋው ይችላል:: ለምሳሌ፣ በአማራ እና በኦሮሚያ ክልሎች፣ በኦሮሚያ እና በሶማሌ ክልሎች፣ እንዲሁም በትግራይ እና በአማራ ክልሎች መካከል ውጥረቶች አሉ፤ ዝርዝሩ በዚህ ብቻ የሚያቆም አይደለም:: ሕዝቡ ጋብቻን ጨምሮ፣ በተለያዩ መንገዶች እርስ በርሱ የተሳሰረ ቢሆንም፣ የብሔር ማንነት ለበርካታ ኢትዮጵያውያን ትልቅ ትርጉም አለው:: ይህ በእንዲህ እያለም፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በብሔር ማንነታቸው ሳይሆን፣ እንደግለሰብ በሕዝባቸው ዘንድ ከፍተኛ ተወዳጅነት አላቸው፤ ይህም በተራው፣ በተለያዩ ክልሎች መካከል ያሉትን አለመግባባቶች ለመፍታት ታሪካዊ ዕድል ሊፈጥርላቸው ይችላል።

በሁለተኛ ደረጃ፣ ምርጫን በተመለከተ፣ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ተወዳጅነት ራሱ አላስፈላጊ ውጤት ሊፈጥር ይችላል:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዘወትር በሚያደርጓቸው ንግግሮች ለመድብለ-ፓርቲ ሥርዓት መመሥረት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ለማበርከት ዝግጁ እንደሆኑ ገልጸዋል:: በእርግጥ፣ ቀጣዩ የኢትዮጵያ ፓርላማ በአሁኑ ወቅት ሙሉ በሙሉ በገዢው ፓርቲ አባላት ከተሞላው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተለየ እንደሚሆን ገና ከወዲሁ የታወቀ ነው:: በአሁኑ ወቅት አንድም የተቃዋሚ ፓርቲ አባል በሕግ አውጪው አካል ውስጥ የለም:: ዳሩ ግን፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቀጣዩን ምርጫ ለማሸነፍ በሕዝቡ ዘንድ ያላቸውን ተወዳጅነት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ከተጠቀሙበት፣ ኢትዮጵያ በቀጣዮቹ ዓመታትም የአንድ ፓርቲ አገዛዝ የሰፈነባት ሀገር ሆና መቀጠሏ አይቀርም::

ጥያቄ፡- በቀጣዮቹ ዓመታት ኢትዮጵያ ውስጥ ምን ዓይነት ሁኔታ ይፈጠራል ብላችሁ ታስባላችሁ?

ቨርጂ፡- ወሳኙ ነገር የሀገሪቷ ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የሚፈቱበት መንገድ ይሆናል:: ኢኮኖሚው ሁሉንም ዜጎች ባማከለ መልኩ ካደገ፣ ለጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ መንግሥት የተወሰነ ድጋፍ ይሆነዋል፤ ይህ ዓይነቱ አካሄድ፣ ለ ኢትዮጵያውያን ትርጉም ያለው ለውጥ የሚያስገኝ ይሆናል:: በአንጻሩ፣ ኢኮኖሚው እምብዛም ዕድገት ካላስመዘገበ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚኖሯቸው አማራጮች በዚያው መጠን መቀነሳቸው አይቀርም::

ሀገሪቷ ወደቀድሞው አፋኝ ሥርዓት አትመለስም ከሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ጊዜው አሁን አይደለም:: በአሁኑ ወቅት ያለው መንግሥት ከበፊቱ ጋር ሲነፃፀር፣ እምብዛም ፈላጭ ቆራጭ አይደለም ቢባልም እንኳን፣ አምባገነንናዊው ሥርዓት ሙሉ በሙሉ ተወግዷል ከማለት ይልቅ፣ ቀስ በቀስ እየተለወጠ ነው ማለቱ የተሻለ ነው::

መንግሥት በርካት ሕዝብ ከቤት ንብረቱ እንዲፈናቀል ያደረጉት የብሔር ግጭቶችን የሚፈታበት መንገድ፣ የ2020 (እ.አ.አ.) ምርጫ እየተቃረበ ሲመጣ ትኩረት ከሚሰጣቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ መሆኑ አይቀርም:: በርካቶች ቀጣዩ ምርጫ ለሀገሪቷ ወሳኝ እንደሆነ ቢገልጹም፣ ስኬታማ ምርጫ ማካሄድ በራሱ የፖለቲካ ሽግግሩ የተሟላ እንደሆነ አይጠቁምም::

# የአዲስ አበባ ህዝብ ራሱን...

ከገጽ 6 የዞረ

## ስለ ልዩ ጥቅም

ሲጀመር፣ ልዩ ጥቅም ተብሎ በህገ መንግስቱ መገለጹ ችግር ያለበት ይመስለኛል:: በአንድ ሀገር ውስጥ ልዩ ጥቅም ተቀባይና ሰጪ መኖሩ በራሱ ችግር አለበት:: በሌላ በኩል፣ በህገ መንግስት ደረጃ ልዩ ጥቅም ሲባል፣ በልዩ ጥቅም የሚጠቀምና የማይጠቀም ዜጋ አለ ማለት ነው፤ ሁለት ዓይነት ዜጋ አለ ማለት ነው፤ ሁለት ዓይነት ዜጋ አለ ማለት ደግሞ፣ የተለያየ ደረጃ ያላቸው ዜጎች አሉ ማለት ነው፤ ደረጃ ካለ ደግሞ መበላለጥ አለ፤ መበላለጥ ካለ እኩል መብት የለም ወደሚለው ይሄዳል ማለት ነው:: ባለንበት ዘመን፣ የዜግነት መሰረታዊ መርህ፣ ዜጎችን ሁሉ በእኩል ደረጃ ማስቀመጡ ነው፤ ልዩ ጥቅም ይህን የዘመናችንን መሰረታዊ መርህ የሚጥስ ነው:: የህግ የበላይነት ማለት አለማዳላት ማለት ነው:: ህግ "ልዩ ጥቅም" ብሎ ካበላለጠ፣ የህግ የበላይነት ይናዳል ማለት ነው::

ይህ ማለት ግን፣ አዲስ አበባና ኦሮሚያ ጎረቤት እንደመሆናቸው መጠን፣ የሚያስተሳስራቸው ጉዳይ የለም ማለት አይደለም:: በተላይ፣ አዲስ አበባ በኦሮሚያ መሀል የምትገኝ በመሆኗ ብዙ የሚያስተሳስራቸው ነገሮች አሏቸው:: አስተዳድራዊ ጉዳዮች ያገናኟቸዋል፣ ተፈጥሯዊ ሀብትን ከመጋራት አኳያ ይገናኛሉ:: አዲስ አበባ ከኦሮሚያ ውሃ ታገኛለች ማለት ግን፣ በህገ መንግስት ደረጃ አንዱ በአንዱ ላይ ልዩ ጥቅም አለው ተብሎ እስከ መደንገግ የሚያደርስ አይደለም:: ተፈጥሮ ሀብት የሚጋሩት አዲስ አበባና ኦሮሚያ ብቻ አይደሉም፤ ሁሉም አጎራባች ክልሎች ናቸው፤ በሐረሪና በኦሮሚያ መካከል ተመሳሳይ ነገር አለ፤ አንዱ በአንዱ ላይ ልዩ ጥቅም አለው የሚል ነገር ግን አልተነሳም:: ተመጋጋቢነቱም ቢሆን፣ በአንድ በኩል ብቻ አይደለም:: ከአዲስ አበባ የሚወጣ ይኖራል ከኦሮሚያ የሚገባ ነገር ይኖራል፤ በተቃራኒውም ከአዲስ አበባ የሚገባ ነገር ይኖራል፣ ከኦሮሚያ የሚወጣ ነገር ይኖራል፤ መደጋገፍ ነው ያለው:: በእነዚህ ጉዳዮች ይደራደራሉ እንጂ፣ አንዱ በሌላው ላይ ልዩ ጥቅም አለው መባል የለበትም::

ልዩ ጥቅም የሚለው ወደ ባለቤትነት ጥያቄ እያደገ ችግር እያስነሳ ነው:: እንደ እኔ፣ ሌሎች ክልሎች እንደሚደራደሩት ኦሮሚያም ከአዲስ አበባ ጋር መደራደር አለባት እንጂ፣ ልዩ ጥቅም ልታገኝ የምትጠይቅበት ወይም የምታገኝበት ምንም ምክንያት የለም::

# የደቡብ ሱዳን ተፋላሚ...

ከገጽ 16 የዞረ

በዚህ ውስብስብ ሥርዓት ውስጥ እየተጫወቱ ያለውን ሚና መጋፈጥ ይኖርባቸዋል:: ከዚህ በተጨማሪም፣ በደቡብ ሱዳን ውስጥ ያላቸው እንቅስቃሴ ለተፋላሚ ወገኖቹ የድጋፍ መሠረት የሆነባቸውን አሠራሮች፣ እንዲሁም ግጭቱን ለማራዘም የተጫወተውን ሚና ማጤን ይኖርባቸዋል:: ታጣቂዎቹ የሥርዓቱን ድክመት ለራሳቸው ጥቅም እና ፍላጎት ማስፈጸሚያ እየተጠቀሙበት እንደሆነ ልብ ልንል ይገባል::

### እንደድምዳሜ

ይህን ዓይነቱን ደካማ ሥርዓት ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ማስወገዱ፣ አዲስ እና ግልጽ የሰብዓዊ እርዳታ ስርጭት አሠራርን መዘርጋት ይጠይቃል:: ይኸው አዲስ የአሠራር ሥርዓት ሌሎች ነገሮችን ጨምሮ፣ የተባበሩት መንግታት ሰላም አስከባሪ ኃይሎች የሰብዓዊ እርዳታ ፍሰቱን እንዲቆጣጠሩ መፍቀድን ሊያካትት ይገባል:: ከዚህ በተጨማሪም፣ የእርዳታ ጥረቱን ለራሳቸው ጥቅም የሚያውሉ ወገኖችን ለመቅጣት የሚያስችል ጠንካራ ሥርዓት መዘርጋት ይኖርበታል::

ከዚህ በተጨማሪም፣ አዲሱ የእርዳታ አሰጣጥ ሥርዓት መንግሥት የሀገር ውስጥ ሀብትን በተመለከተ ቸልተኝነትን እያሳየ፣ ከባሕር ማዶ የሚመጣውን እርዳታ የማከፋፋሉ ሥራ ለዓለም ዓቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች የተወበት የአሠራር ዘዴ መወገድ ይኖርበታል:: በዚህም መሠረት፣ ዓለም ዓቀፍ ለጋሾች ቃል የገቡትን እርዳታ የሚያቀርቡበት ቀነ-ገደብ በትክክል እና በጥብቅ ተግባራዊ መሆን አለበት:: ይህን ተከትሎም፣ የደቡብ ሱዳን መንግሥት በአሁኑ ወቅት በዩ.ኤስ. አሜሪካ፣ በእንግሊዝ እና በካናዳ መንግሥታት እየተደገፉ ያሉትን የትምህርት እና የጤና ዘርፎች በራሱ ዓቅም ማጠናከር መጀመር አለበት::

በስተመጨረሻም፣ የሰብዓዊ እርዳታው አካሄድ በራሱ ጥያቄ ውስጥ መግባት ይኖርበታል:: ለደቡብ ሱዳን እየተሰጠ ያለው ሰብዓዊ እርዳታ የተለያዩ ወገኖች ለየግል ጥቅማቸው በቀላሉ በሚያውሉበት ሥርዓት በኩል የሚያልፍ ነው:: ከዚህ በተጨማሪም፣ ዕርዳታ ተቀባዩ ሕዝብ በጊዜ ሂደት ራሱን የሚችልበትን እና ጽናት የሚያገኝበትን ዕድል የሚፈጥር አይደለም::

በእርግጥ፣ በደቡብ ሱዳን ያለውን የእርዳታ አሰጣጥ ሥርዓት ለማሻሻል የሚያግዙ ቀላል መፍትሔዎች የሉም:: ይሁን እንጂ፣ ዓለም ዓቀፉ ማኅበረሰብ እና ለጋሽ ድርጅቶች አሠራራቸው በተፋላሚ ወገኖች ዘንድ ለግል ጥቅም እየዋለ እንደሆነ እስካልተገነዘበ ድረስ፣ ደቡብ ሱዳን ውስጥ እየታየ ላለው የደም መፋሰስ ዑደት አስተዋጽኦ ማድረጋቸውን ይቀጥላሉ::

# የአል-በሽር እና የዓለም...

ከገጽ 17 የዞረ

ሀገራት እንደመሆናቸው መጠን፣ መልዕክቱ በሥልጣን ላይ ያሉ መሪዎች ሥልጣናቸውን ይበልጥ የሙጢኝ ብለው እንዲይዙ አንድ ተጨማሪ ገፋፊ ምክንያት ይሰጣቸዋል::

ለዚህ ሁኔታ ዓይነተኛ ምሳሌ የምትሆነን ሶሪያ ናት:: ሶሪያ ውስጥ እየተካሄደ ባለው የእርስ በርስ ጦርነት አገባብ መሠረት፣ የአል-በሽር በአሁኑ ወቅት ከዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ችሎት ፊት መቅረባቸው የሶሪያው መሪ፣ በሽር ሃፌዝ አል-አሳድ፣ ከሥልጣናቸው ከወረዱ፣ በቀጣይነት ምን ሊጠብቃቸው እንደሚችል የማስጠንቀቂያ ደወል መሆኑ አይቀርም:: የሶሪያን የእርስ በርስ ጦርነት ለማስቆም እየተደረገ ያለው ዲፕሎማሲያዊ ጥረት፣ በዋነኝነት አል-አሳድ ሥልጣናቸውን በሚለቁበት ሁኔታ ዙሪያ ያጠነጠነ እንደመሆኑ መጠን፣ የአል-በሽር ከዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ችሎት ፊት መቅረብ አል-አሳድ በአሁኑ ወቅት በያዙት አቋም እንዲጸኑ ተጨማሪ ምክንያት ይሆናቸዋል::


ሁለተኛው ችግር፣ ከአተያይ ጋር የተያያዘ ነው:: አል-በሽር ችሎት ፊት እንዲቀርቡ፣ ዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት በአሁኑ ወቅት በሥልጣን ላይ የሚገኘው የሱዳን ወታደራዊ የሽግግር ምክር ቤት ፈቃደኝነት እና ትብብር ያስፈልገዋል:: የአፍሪቃ ቀንድ ሀገራት ፖለቲካ ተመራማሪው እና ተንታኙ፣ አሌክስ ደ ቫአል እንደሚሉት፤ አል-በሽር ውስብስብ በሆነ ድር መኻል የሚገኙ ሸረሪት ነበሩ:: ከዚህ በተጨማሪም፣ በአሁኑ ወቅት በአዲሱ የሀገሪቷ መንግሥት ከታቀፉ ከፍተኛ ባለሥልጣናት መካከል፣ አንዳንዶቹ አል-በሽር በሚፈለጉባቸው ወንጀሎች እጃቸው እንዳለበት ብዙም አያጠራጥርም:: ዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት አል-በሽርን ችሎት ፊት ማቅረብ ፈልጎ የአዲሱን መንግሥት ትብብር ከጠየቀ፣ የሀገሪቷ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ላይ ተመሳሳይ ክሶችን እንዳይመሠርት መጠየቁ አይቀርም::

ዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤትን አጣብቂኝ ውስጥ የከተተ ሁኔታ ሲከሰት የአሁኑ ለመጀመሪያ ጊዜ አይደለም:: የዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት የቀድሞው ዋና ዐቃቤ ሕግ፣ ሉዊስ ሞሬኖ አካምፖ፣ ከኡጋንዳው መሪ፣ ዮዌሪ ሙሴቬኒ፣ ጎን ቆመው የተነሷቸው ፎቶግራፎች ከብዙዎቻችን የትውስታ ማኅደር አልጠፉም:: በወቅቱ፣ ከዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ጋር በተያያዘ ይነሣ የነበረው አንገብጋቢ ጉዳይ አድሎአዊነትን በተመለከተ ነበር:: የዓለም ዓቀፍ ሕግ ምሁሩ፣ ማርክ ከርስተን፣ ለመጠቆም እንደሞከረው፣ ዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት በወቅቱ ኡጋንዳን በተመለከተ የተከተለው አቋም በከፍተኛ የመንግሥት የሥልጣን እርከን ላይ የሚገኙ ሰዎች የፈጸሟቸውን ወንጀሎች ችላ ብሏል:: አሁንም ቢሆን፣ ዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ይህን መሰሉን ስሕተት ዳግም ከመፈጸም መቆጠብ ይኖርበታል::

### እንደድምዳሜ

ታዲያ፣ ይህ ሁኔታ ዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤትን ምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ይከትተው ይሆን? በእርግጥ፣ ዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት በአሁኑ ወቅት የገባበትን ችግር መፍታቱ ቀላል አይሆንም:: የተለያዩ የዓለማችን ሀገረ-መንግሥታት በዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ላይ ያላቸው የበላይነት፣ በሥልጣን ላይ ያሉ መሪዎችን ችሎት ፊት ለማቅረብ ለሚደረገው ጥረት አንድ ከባድ መሰናክል ነው:: ችግሩን ይበልጥ የሚያወሳስቡት ደግሞ፣ በቀጣይነት ሥልጣን ላይ የወጡት ባለሥልጣናት የቀድሞውን የሀገር መሪ ለፍርድ ቤቱ አሳልፈው ለመስጠት ያላቸው ፈቃደኝነት፣ እንዲሁም የሚሰጡት ትብብር ናቸው::

ስለዚህም፣ በርዕሱ ላይ እንደተገለጸው፣ አል-በሽርን በተመለከተ ዓለም ዓቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት አጣብቂኝ ውስጥ ገብቷል ያልኩት በዚሁ ምክንያት ነው:: ያለመታደል ሆኖ፣ በአል-በሽር ዙሪያ ያለው ሁኔታ ለእነኝህ ችግሮች መፍትሔ አይሆንም:: እንዲያውም፣ ችግሮቹን ይበልጥ ሊያወሳስበው ይችላል::



ኒቆዲሞስ ኢያሌው (የብዕር ስም)

# ከ "ያ ትውልድ" አባል ለዶክተር ዐቢይ የተፃፈ ግልፅ ደብዳቤ

# እነ "አሸነፈ እና አቸነፈ" ባዮች

## እንደ መግብያ

የ1966 ዓ.ም አብዮት፣ መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከ ዳር ያንቀሳቀሰ እና ያሳተፈ ነበር። ሥልጣን የያዘውና አብዮቱን የመራው ቡድን፣ ከሻለቃ ማእረግ በታች ከሆኑ መኮንኖችና ባለሌላ ማዕረጎች ከነበሩ የተወጣጣ እና ራሱን ወታደረዊ ደርግ ብሎ የሰየመ ቡድን ነበር:: በወቅቱ፣ ጥቂት የተደራጁ የፖለቲካ ድርጅቶችም ለአብዮቱ አስተዋፅኦ አድርገዋል። ከእነዚህ የፖለቲካ ቡድኖች መካከል ፣ የመላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) እና የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ሚና ፣ በተለይ በአብዮቱ የመጀመርያ ዓመታት በጣም የጎላ ነበር። መኢሶን እና ኢሕአፓ፣ በማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮት ላይ በመመስረት (የየራሳቸውን አረዳድ እና አካሄድ ጨምረው፣) ኢትዮጵያን የተሻለ የዕድገት ደረጃ ላይ ለማድረስ ከፍተኛ ትግል አድርገዋል። መኢሶን፣ ሕዝቡን በማንቃት እና በማደራጀት ላይ ሲያተኩር፣ ኢሕአፓ ደግሞ የገጠር እና የከተማ የትጥቅ ትግል ላይ አተኩሯል::

## ሶሻሊዝም ለምን ?

ዶ/ር ዐቢይ አህመድ፣ "እርካብና መንበር" በሚለው መጻሐፋቸው ገጽ 65 ላይ፣ "ሶሻሊዝም አይሠራም ተብሎ ተሞክሮ መውደቁ በተረጋገጠበት ዘመን ፣... ሶሻሊዝምን መረጡ፣... እርስ በእርስም ተላለቁ" እንዳሉት ሳይሆን፤ በወቅቱ፣ በአብዛኛው የዓለም ክፍል፣ ሶሻሊዝም የገነነበት፣ ካፒታሊዝም እና ኢምፔሪያሊዝም የተወገዙበት ዘመን ነበር::

ከዚህም ሌላ፣ የሶሻሊስት አስተምህሮ፣ ለደሀው እና ለጭቁን ሕዝቦች ነፃ መውጣት የቆመ በመሆኑ፣ በመላው ዓለም የመስፋፋት እና በቀላሉ ድጋፍ የማሰባሰብ ኃይል ነበረው። ከዚህም የተነሳ ፣ በስልሳዎቹ አካባቢ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ሶሻሊስት ሆኖ አለመገኘት (በተለይ በተማረው ትውልድ አካባቢ፣) እንደ ሕዝብ ጠላትና የለውጥ እንቅፋት ያስቆጥር ነበር።

በአለም ዙሪያም ቢሆን፣ በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ በርካታ በሶሻሊዝም የተቃኙ እንቅስቃሴዎች ተካሂደዋል። ለምሳሌ፣ በአፍሪካ ፣ ጊኒ ቢሳዎ፣ ኬፕ ቨርዴ ፣ አንጎላ ፣ ጋምቢያ ...ወዘተ ውስጥ የተደረጉ፣ የፀረ-ቅኝ አገዛዝ እና የፀረ-ዘረኝነት ትግሎች ይጠቀሳሉ:: በእስያ፣ የቻይና የባህል አብዮት፣ እንዲሁም በቬትናም ፣ በላኦስ እና በካምፑቺያ የተደረጉት የፀረ-ኢምፔሪያሊስት ጦርነቶች፤ በአሜሪካ የተካሔደው፣ ፀረ-የቬትናም ጦርነት ንቅናቄ ፣ የጥቁሮች እና የሴቶች መብት ለማስከበር የተደረጉ እንቅስቃሴዎች፤ በደቡብ አሜሪካ ፣ የኩባ አብዮት እና የትራይ ኮንትኔንታል ንቅናቄ፤ በምዕራብ አውሮፓ ፣ በእንግሊዝ ፣ በፈረንሳይ፣ በጀርመን ፣ በስፔይን ፣ በጣሊያን ... ወዘተ፣ ወጣቱና ሕዝቡ ያካሄዱት የእኩልነት እና ፀረ-ጦርነት ትግል፣ ከዳር እስከ ዳር የተስፋፋበት ወቅት ነበረ። በዚህም የተነሳ ፣ አብዛኛው የኢትዮጵያ ወጣት እና ምሁር፣ የዚህ ዓለም አቀፍ እንቅስቃሴ አካል




ከመሆን አላመለጠም። በተቃራኒው ዛሬ የዓለም-አቀፍ ሁኔታ ተቀይሮ ፣ ወቃሹ ተወቃሽ ፣ አውጋዡ ተወጋዥ ፣ ጨቋኙ ነፃ-አውጭ የሆነበት ዘመን ላይ እንገኛለን፤ እድሜ ከሰጠን ገና ብዙ እናያለን።

## የታሪክ ዘጋቢዎች ሚና

ከላይ በአጭሩ የተጠቀሰው፣ የአብዮት እና የትግል ታሪክ፣ ለዛሬ ወጣት ፖለቲከኞች፣ የታሪክ ተመራማሪዎች፣ ደራሲያን እና የሚዲያ ሰዎች የሚያስተላልፈው ታላቅ ትምህርትና አደራ አለው። እርሱም፣ ስለአንድ የቅርብም ሆነ የሩቅ ሁኔታ ስትዘግቡ፣ መቼቱን (ኮንቴክስቱን) አትርሱ የሚለው ነው። የትላንትን ድርጊት በዛሬ መነጽር እያዩ፣ ታሪኩንም ሆነ የታሪኩን ተዋንያን ማብጠልጠል፣ የስህተት ሁሉ ስህተት ከመሆኑም በላይ፣ የተዛባ እና የተንሸዋረረ ታሪክ፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ ይሆናል። በአብዮት ወቅት፣ ብዙ ተለዋዋጭ ነገሮች ስለሚፈጠሩ፣ ተጨባጭ ሁኔታውን የሚዘግቡ ሁሉ፣ ታሪክን ላለማዛባት ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

## አብዮት ማለት

ጠቅለል ባለ መንገድ ሲገለጽ፣ አብዮት ማለት፣ የመደቦች ሹምሽር ሲሆን፣ በሲቪሎች መካከል የሚካሄድ የመብት እና የነጻነት ጦርነትም ነው ይባላል። ከዚህ የተነሳ፣ በሃገራችን ገጠርም ሆነ ከተማ፣ በአብዮተኞችም ሆነ በጸረ- አብዮተኛው ወገን ብዙ ሕይወት ጠፍቷል፤ ይህ ደግሞ በኢትዮጵያ አልተጀመረም። በቅርብ ዘመን እንኳን፣ በአንግሊዝ፣ በፈረንሳይ፣ በጀርመን፣ በአሜሪካ፣ በራሽያ፣ በቻይና.......ወዘተ፣ በአብዮቶቹ ወቅት የተፈጠረውን የሕዝብ እልቂት ማስታወስ ይቻላል።

አብዮት ደግሞ፣ የሌላውን ብቻ ሳይሆን የራሷንም ልጆች ትበላለች። አያምጣው እንጂ፣ አንዴ ከመጣ፣ "አብዮት የራት ግብዣ አይደለም" የሚባለው ለዚህ ይመስለኛል። ግብዣ ደግሶ፣ ተጋባዥ ጠርቶ፣ "ለምን በላና ጠጣ" እንደማይባል ሁሉ፣ አብዮት ለኩሶ፣ ለምን ሰው ሞተ ማለት አይቻልም። ባይሆን ታሪኩን ለትውልድ መማሪያነት ለማቆየት፣ የአብዮቱን መነሻና ጠቅላላ ሂደቱን፣ ተአማኒ እና ሚዛናዊ በሆነ መልኩ መዘገቡ የዜጎች ሁሉ ሃላፊነት ይመስለኛል።

## የእኛ ጉዳይ፥

የ1966 ዓ.ም. አብዮት ትርክት፣ በጽሁፍም ሆነ በልዩ ልዩ ሚዲያዎች፣ ባለፉት 28 ዓመታት፣ አብዛኛውን ጊዜ አየተዛባ ሲቀርብ ተመልክተናል። በወቅቱ የነበሩ ተዋንያን ገንቢም ሆነ አፍራሽ አስተዋጽኦዋቸው፣ ፈር በለቀቀ ወገንተኝነት ተመዝግቦ አንብበናል። በዛ ያሉ ቃለ መጠይቆች ማን? የት? መቼ? የሚሉትን ጥያቄዎች ሳያስተናግዱ፣ በጅምላ ሲጻፉና በቴሌቪዥን ሲተላለፉ ተመልክተናል። ትርክቱ፣ ሚዛኑን አና መቼቱን ጠብቆ ቢቀርብ፣ ሕሊናን ከጸጸት፣ ሙያን ከውግዘት ያድናል። ለምሳሌ፣ ደርግ ከ1966 አ/ም አስከ 1983 አ/ም ለአስራ ሰባት አመታት፣ አካሄዱን እየቀየረ ኢትዮጵያን አስተዳድሯል። በአነዚህ አመታት ውስጥ፣ በሰራቸው መልካም ሆነ እኩይ ተግባራት፣ ለፈጸማቸው ገንቢም ሆነ አፍራሽ ድርጊቶች፣ በአግባቡ እና ሚዛናዊ በሆነ መንገድ መወቀስም ሆነ መወደስ ይኖርበታል።

መኢሶንም ቢሆን፣ በየካቲት 25 ቀን 1967 ዓ.ም. ከታወጀው፣ ከገጠር መሬት አዋጅ በኋላ፣ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስቱን፣ በአላማው ግፋ በርታ እያለው፤ ባጠፋው ደግሞ፣ ከጥፋቱ አንዲታረም ጫና በማድረግ ሲታገል ቆይቷል:: ከሚያዝያ 13 ቀን 1968 ዓ.ም. ጀምሮ፣ ማለትም፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ከታወጀና የህዝብ ድርጅት ጊዜያዊ ጽ/ቤት ከተቋቋመ በኋላ ደግሞ፣ ከሌሎች ተራማጅ ድርጅቶችና ግለሰቦች ጋር ተባብሮ በተሻለ ቅርበት፣ እስከ ነሃሴ 14 ቀን 1969 ዓ.ም. ድረስ ታግሏል። ይኸውም ለአንድ አመት ከስድስት ወር መሆኑ ነው። መኢሶን፣ በእነዚህ ግዜያት ውስጥ ባበረከተው አዎንታዊ አስተዋጾ መሞገስ፣ ባከናወናቸው አሉታዊ ተግባራት ደግሞ መኮነን ይገባዋል። በተረፈ፣ መኢሶን ከግዜያዊ ወታደራዊ መንግስት ጋር ከተለያየ በኋላ፣ በጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስትም ሆነ በሌሎች ፓርቲዎች ለተሰሩ፣ ጥሩም ሆኑ መጥፎ ተግባራት ባለድርሻ መሆን የለበትም።

ወደ ቀጣዩ ገጽ 23

ሌሎች ድርጅቶችም ሆኑ ግለሰቦች እንዲሁ፣ ወቀሳውም ሆነ ውዳሴው ሲነገር፣ በመረጃ እና በማስረጃ ቢደገፍ ይመረጣል። ለዚህ ነው፣ ደግሜ እና ደጋግሜ "ወቅቱን ስትተርኩ መቼቱን ጠብቁ" የምለው፣ በተለይ ለሚዲያ ሰዎች።

### የዚህ ጽሁፍ አላማ ያልሆነው

የዚህ ጽሁፍ አላማ፣ በመኢሶን እና በኢሕአፓ መካከል የነበረውን የአቋም ልዩነት ለመዘገብ አይደለም። ይህን ለማድረግ የፈለገ ጋዜጠኛ፣ የፖለቲካ ሰው ወይም የታሪክ ተመራማሪ፣ በወቅቱ ይነሱ በነበሩ ዋና ዋና ጥያቄዎች፣ ለምሳሌ፡-

- የብሔር ጥያቄ - በተለይ ኤርትራን በሚመለከት፣
- የከተማ እና የገጠር ትጥቅ ትግል - ቀይ እና ነጭ ሽብርን ጨምሮ፣
- የስልጣን ጥያቄ - የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስትን ጨምሮ፣
- የእድገት በሕብረት፣ የእውቀት እና የስራ ዘመቻን በሚመለከት፣
- የአብዮቱ ወዳጆች እና ጠላቶችን ፍርጃ - ከመሬት አዋጁ በፊት እና በኋላ፣
- የዲሞክራሲ ጥያቄን- ለምን? ለማን? በገደብ ወይስ ያለገደብ? የሚለውን በሚመለከት፣
- ሂሳዊ ድጋፍ ወይስ ፋሽዝም በኢትዮጵያ...... ወዘተ ላይ ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል።

ሁለቱ ድርጅቶች አቋማቸውን ለሕዝብ ለማስተዋወቅ

1ኛ ፣ በህቡዕ ያሰራጯቸው ከነበሩት፣ "የሰፊው ሕዝብ ድምጽ" እና "ዲሞክራሲያ" ልሳኖቻቸው (በአብዛኛው በአ.አ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ማእከል ይገኛሉ

2ኛ ፣ "በአዲስ ዘመን" እና "በዛሬይቱ ኢትዮጵያ" ጋዜጦች፣ በወቅቱ ከተመዘገቡ አብዮት ነክ ዜና መዋእሎች

3ኛ ፣ በተለያዩ ጊዜያት የሁለቱ ድርጅቶች አባላት ፣ በመጽሄት እና በመጻህፍት ካወጧቸው ጽሁፎች

4ኛ ፣ ገለልተኛ ደራሲያን እና የደርግ አባሎች የጻፏቸውን፣ ልዩ ልዩ መጽሀፍት በትኩረት በማንበብ እና በማመሳከር፣ በወቅቱ ትርክት ላይ የተፈጠረውን ብዥታ በመጠኑም ቢሆን ለማጥራት ይቻላል። ፍላጎቱ ካለ ማለቴ ነው።

### የዚህ ጽሁፍ አላማ ፡-

ለዚህ ጽሁፍ መነሻ የሆነኝ፣ አንድ ፕሮፌሰር፣ ቀደም ሲል ለሕዝብ ያስጨበጡት ፣ "የስልሳዎቹ ትውልድ አሸነፈ እና አቸነፈ በሚል ትግል እርስ በእርሱ ተጠፋፋ" የሚለው ትርክታቸው ነው። ይህ ያለፈውን ትውልድ በጅምላ የሚያንኳስስ ፍረጃ ፣ በአብዮቱ ጥቅማቸው የተነካባቸውን ፊውዳሎች፣ በለውጡ ያኮረፉ ቢሮክራቶችንና ለሹመት አሰፍስፈው የነበሩ ምሁራኖችን ጭምር፣ በአንድ ያሰባሰበ ከመሆኑም በላይ፣ ወሬው በወቅቱ በየመሸታ ቤቱ ለጸረ- አብዮተኞች አረቄ ማጫለጫ እና ወግ ማድመቂያ ሆኖ በግብአትነት አገልግሏል።

ይህንን ጉዳይ፣ ለዓመታት በትዝብት ብቻ አልፌው ነበር። ታዲያ አመታት አልፈው፣ መንግስታትም ተቀያይረው፣ "አሸነፈ እና አቸነፈ" ባዮች በአዲስ መልክ ብቅ ማለታቸው አልቀረም። በጣም የሚገርመው ደግሞ፣ በአሁን ጊዜ ይህን "መፈክር" ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ፣ በተዋቡ ንግግራቸው መሃል ጣል የሚያደርጉት ዶ/ር ዐቢይ አህመድ መሆናቸው ነው። መጀመሪያ ላይ፣ "የአፍ ወለምታ" ይሆናል ብዬ አለፍኩት፤ ሲደጋግሙት ግን አሳሰበኝ። ከዚያም ዝምታዬን ሰብሬ ይህችን መልእክት ለማስተላለፍ ወሰንኩ።

ዶ/ር ዐቢይ፣ በአብዮቱ ጊዜ ገና ሕጻን እንደነበሩ ይገመታል። መጽሀፋቸውን (እርካብና መንበርን) ያነበበና በአለፈው አንድ አመት ያደረጓቸውን ንግግሮች የሰማ፣ የተማሩ፣ ብዙ ያነበቡ እና የቀድሞዋንም ሆነ የዛሬዋን ኢትዮጵያ ታሪክ ከበቂ በላይ የሚያውቁ መሆናቸውን በቀላሉ ለመረዳት ይችላል። የአካባቢያችንን እና ዓለም-አቀፍ ሁኔታዎችን ሲተነትኑና ግንዛቤ ሲያስጨብጡ ደግሞ፣ በዘርፉ አንቱ ከተባሉ ምሁራን አያንሱም ለማለት ያስደፍራል። ከዚህ ሁሉ ተነስተን፣ ዶ/ር ዐቢይ "አሸነፈ እና አቸነፈ" የሚለውን ትርክት፣ ባለማወቅ እየደጋገሙ ተጠቅመውበታል ብሎ ለማሰብ፣ በጣም እጅግ በጣም ይከብዳል።

### እንደ ምክንያት፡-

ታዲያ ዶ/ር ዐቢይንና "አሸነፈ እና አቸነፈን" ምን አገናኛቸው ? እኔ ያገኘሁት መልስ የሚከተለው ነው፤ ከተሳሳትኩም ለመታረም ዝግጁ ነኝ። ዶ/ር ዐቢይ

> **"ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር፣ በጣም ከበዛ ጨዋነት ጋር የኢትዮጵያ ህዝብ በንግግርዎ ብቻ እጁን ዘርግቶ በደስታ ተቀብልዎታል : : አሁን፣ ንግግረዎን በተግባር የማሳያ ጊዜዎ እያለፈ ነው**

አምነውበት የተሳተፉበት ድርጅትም ሆነ ንቅናቄ የለም፣ (ቢያንስ መጀመሪያ ላይ) ለአቅመ አዳም ከደረሱ በኋላ፣ በታሪክ አጋጣሚ ዘው ብለው የገቡትና ራሳቸውን ያገኙት፣ ሌሎች (ህወሓቶች፣)"ደማችንን አፍሰን፣ አጥንታችንን ከስክሰን አመጣነው" በሚሉት ድርጅት ውስጥ ነው።

ከሃያ ሰባት አመታት በላይ፣ ድርጅታቸውን ኢሕአዴግን እና እርሳቸውን ሲታገል የነበረው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቀጣጠለውን ሀገር-አቀፍ ትግል ተከትሎ፣ ዶ/ር ዐቢይ እና ጓደኞቻቸው (ቲም ለማ) የሀገሪቱን አመራር ተረክበዋል። ይህን ተከትሎ፣ ዶ/ር ዐቢይ አህመድ እርካቡን እረግጠው፣ መንበሩ ላይ በመውጣት የሾፌሩን ቦታ ተረክበዋል።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እርሳቸው ይሸከረከራሉ፣ እኛንም ያሽከረክራሉ። ወዴት እንደሚሄዱና ወዴት እንደሚወስዱን ገና አልታወቀም፤ ዝም ብለው ይነዳሉ፤ እየነዱም ያወራሉ፤ አሻግራችኋለሁ ይሉናል፤ ከየት ወዴት እና እንዴት እንደሆነ ግን የታወቀ ነገር የለም። በሚያማልለው ንግግራቸው መሀል፣ "አሸነፈ እና አቸነፈ ተባብለው ተጨራረሱ" ይላሉ። የስልሳዎቹን ትውልድ ትግል እና መስዋእትነት፣ አንድ አረፍተ ነገር በማይሞላ "ትንታኔ" ድምጥማጡን ያጠፉታል።

ለምን ? መልሱ ግልጽ ነው። ቀደም ሲል ፕሮፌሰሩ የግል ስብዕናቸውን ከፍ ለማድረግ እንደተጠቀሙት ሁሉ፣ ዶ/ር ዐቢይ ደግሞ ፣ የፖለቲካ ክህሎታቸው ከዚያ ትውልድ የላቀ እና የመጠቀ ነው ለማለት እየተጠቀሙበት ይገኛሉ። ይህን ግምት ይበልጥ የሚያጎላው ደግሞ ፣ በመጽሀፋቸው፣ "እርካብና መንበር" ገጽ 53 ላይ፣ ኢሕአፓ እና መኢሶን ፣ "በቀራጥ እና ባንዳ ፣ በወዝአደር እና ላብአደር ተለያይተው፣ በቀይና ነጭ ሽብር ተላለቁ" ማለታቸው ነው። ትንሽ ወረድ ብለው፣ ገጽ 65 ላይ ደግሞ፣ ".... ኃይሌ ፊዳም፣ ዶ/ር ተስፋዬ ደበሳይም፣ ብርሃነ-መስቀልም ሆነ ሡናይ ልኬ፣ በታሪካቸው መስከረውልን ያለፉት እውነታ፣ የቴዎድሮስን የኃይለስላሴን እና የመንግስቱ ኃይለማርያምን ግብርን ነበር..." በማለት ሁሉንም በአንድ ከረጢት አጭቀው ይጨፈልቋቸዋል። ማን ቀረ ? ዶ/ር ዐቢይ ብቻ። ታዲያ ሌሎችን በማንኳሰስ እራስን ለማግዘፍ መሞከር፣ ከዚህ የበለጠ ምን ማስረጃ ያስፈልገዋል ?

### እንደ መውጫ፡ -

ዶ/ር ዐቢይም ሆኑ ሌሎች "አሸነፈ እና አቸነፈ" ባዮች፣ በመኢሶን እና በኢሕአፓ አቋሞች ላይ ችግር ካላቸው፣ ከላይ በተዘረዘሩት እና ሌላም ጨምረው ፣ በመረጃ የተደገፈ ሂስ እና ትንተና ማቅረብ ይችላሉ። ከዚህ በተረፈ፣ የደብዳቤውን (የጽሁፉን) ይዘት ትቶ፣ በፊርማው (በመፈክሩ) ላይ ማተኮር ግን፣ ድብቅ ፍላጎትን ለማሳካትና የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት የሚደረግ ሩጫ ይመስለኛል።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር፣ በጣም ከበዛ ጨዋነት ጋር የኢትዮጵያ ህዝብ በንግግርዎ ብቻ እጁን ዘርግቶ በደስታ ተቀብልዎታል። አሁን፣ ንግግረዎን በተግባር የማሳያ ጊዜዎ እያለፈ ነው። በግልም ሆነ በድርጅቱ፣ ተደጋጋሚ ስህተት እየሰሩ ይቅርታ ማለት ብዙ አያስኬድም፤ ሕዝብ መጠራጠር ጀምሯል። በተለይ፣ የሀገርን ጉዳይ በሚመለከት የሚነገረው እና የሚሰራው ከተለያየ፣ ፍቅር ወደ ጥላቻ ይቀየራል፤ ጠንቀቅ ማለት አይከፋም፤ በሀገር ጉዳይ ግልጽ እንሁን። ያለችን አንድ ሀገር ብቻ ነች። ኢትዮጲያ ኬኛ ብለን እሩቅ እናልም። ዛሬም የኢትዮጵያ ህዝብ ያቸንፋል ! ነገም የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሸንፋል ! ችግሩ ያለው ከእናንተ ዘንድ እንጂ፣ መፈክሩ ላይ አይደለም።

ቸር እንሰንብት!!!

## የህክምና ባለሙያዎች በአዲስ አበባ...

ከገጽ 2 የዞረ

"ኢትዮጵያ፣ አንቱ የተባሉ፣ ሙያቸውን ያስጠሩና ያስከበሩ ትልልቅ ሀኪሞች አሏት። እነዚህ ሀኪሞች በሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃም ስማቸው የሚጠራ ነው። ለምሳሌ ያህል፣ ፕሮፌሰር በእደማርያም ፀጋ፣ ፕሮፌሰር ጀማል አብዱል ቃድር፣ ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ፣ ዶክተር ተክለ ፂዮንን የመሰሉ ብዙ ባለሙያዎችን ያፈሩና ለብዙ የህክምና ትምህርቶች ፈር የቀደዱ አባቶቻችን ናቸው፤ እነዚህ አሁን ላለነው ሁሉ አርአያ ናቸው። ይህ እንኳን ቢቀር፣ በሰኔ 16ቱ የቦንብ ጥቃት ሰለባ የሆነውና ዓይኑ የጠፋው ሀኪም ጓደኞችን፣ በጥይት ናዳ ውስጥ ሆነው በአሶሳና በጅጅጋ የተጎዳውን ህብረተሰብ ለማገልገል ሳይፈሩ የህክምና አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ ጓዶቻችን (ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ዓለሙ ነው፤) የጌዲኦ ችግርን መንግስት ከመናገሩ በፊትና እርዳታ ከማሰባሰቡ በፊት፣ በግላቸው ተነሳሽነት እርዳታ አሰባስበው የሄዱት ወጣት የሙያ ልጆቻችን ሊጠቀሱ ይገባ ነበር ብለን እናምናለን፤ ይህ ባለመሆኑ እኛ ሀኪሞች አዝነናል። ግን፣ ፍቅር ከሁሉም በላይ ነው፤ ስለምንወዳቸው (ጠ/ሚ/ሩን) በሙሉ ልብ ይቅርታ እናደርግላቸዋለን።"

ዶክተር ገመቺስ የማህበሩን ራዕይ ሲያብራሩም፣ ከግል ጥቅም ባሻገር፣ ህብረተሰቡ የሚገባውን ጥራት ያለው ህክምና እንዲያገኝ፣ ተማሪዎች ጥራት ያለው የህክምና ትምህርት እንዲያገኙ፣ በሞትና በሽረት መካከል ያሉ ህሙማን መድኃኒት ያለምንም ችግር እንዲያገኙ (መንግስትን) መማፀን ነው ብለዋል። "የእኛ ጥቅም የታካሚዎች መዳን ነው" ብለዋል ዶክተር ገመቺስ።

በቀጣይነት፣ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ዓለሙ ማህበሩ ለመንግስት ያቀረበውን ጥያቄ በዝርዝር አቅርበዋል። ከቀረቡት ጥያቄዎች መካከል፣ የጤና ፖሊሲውን ለማሻሻል ያለው መነሳሳት የሚበረታታ ቢሆንም፣ የጤናው ዘርፍ ክፍተቶች ጋር የማይመጣጠን ስለሆነ ማስተካከያ እንዲደረግበት፣ የሀገራችን በጀት የዓለም የጤና ድርጅት ያስቀመጠውን ዝቅተኛውን የበጀት መጠን እንኳን የማያሟላ በመሆኑ ማስተካከያ እንዲደረግ፤ አብዛኞቹ አመራር ላይ ያሉ ሰዎች (በተለይ ዋና አስተዳዳሪወች) ኃላፊነት የሚሰጡት (የሚሾሙት) በችሎታቸውና በእውቀታቸው መሰረት ሳይሆን በፖለቲካዊ አመለካከታቸው የሚመደቡ በመሆኑ እንዲስተካከል፤ የጥቅማጥቅም ክፍያን በተመለከት፣ የሚከፈለው ክፍያ ወጥነት ያለው፣ ነባራዊ ሁኔታንና የስራ ጫናውን ያገነዘበ እንዲሆንና ጭማሪም እንዲደረግበት፤ ኢትዮጵያ ለሀኪሞች የምትከፍለው ደምወዝ በዓለም ካሉት የመጨረሻ በመሆኑ ማስተካከያ እንዲደረግበት፤ የህክምናውን ዘርፍ የትምህርት ጥራት በተመለከተ ከብዛት ይልቅ ለጥራት ቅድሚያ እንዲሰጥ፤ የሚሉት ተካትተዋል።

የማህበሩ አመራር አባላት በቀጣይነት በሰጡት አስተያየት፣ በመገናኛ ብዙሃን በኩል(በስም ባይጠቅሷቸውም፣ የመንግስት መገናኛ ብዙሃንን ማለታቸው እንደሆነ ይታመናል) በጤና ባለሙያዎች ላይ ሰፊ የማጥላላት ዘመቻ መደረጉ አግባብ አለመሆኑን ተናግረዋል። "እነዚህ የሚዲያ ተቋማት፣ የጤናው ስርዓት ስላለበት ችግር ግን ሲተቹ ሰምተን አናውቅም" በማለት ትዝብታቸውን አስመዝግበዋል።

ከዚህ በኋላ የጥያቄና የመልስ ፕሮግራም የነበረ ሲሆን፣ ከጠ/ሚ/ሩ ጋር የነበረውን ስብሰባ አስመልክተው ሲናገሩ፣ " ከሚኒስትሩ ጋር በነበረን ቆይታ፣ የማህበሩ አመራሮች ጥያቄ ለመጠየቅ እድል እንደሚሰጠን ቃል ተገብቶልን ነበር፤ በኋላ ግን ሳይሆን ቀርቷል። የስብሰባው ዓላማ እውን የጤና ችግሩን ለመቅረፍ የታሰበ ነበር ወይ? የሚል ጥያቄ አለን። በእኛ እይታ፣ የጤናው ጉዳይ በፖለቲካው ተጠልፏል የሚል ነው" ብለዋል። ብዙ ጋዜጠኞች ያነሱትን የስራ ማቆም አድማ አስመልክተው በሰጡት ምላሽም፣ "እኛ እንደማህበር ሀኪም ስራ ማቆም አለበት ብለን አናምንም። የማንደግፈው ህጉ ስለሚያግደን አይደለም። ህግ ሰውን እንደማያግድ ያለፉት ሁለት ዓመታት የቄሮና የፋኖ ትግል ያስታውሰናል። የስራ ማቆም አድማን የማንደግፈው፣ እኛ ስራ አቁመን ታካሚዎች ችግር ላይ እንዳይወድቁ ነው። የምንገዛው ሉዓላዊ ለሆነው የሞራል ህግ ስለሆነ ነው። እኛ ይህን የስራ ማቆም አድማ አልጠራንም። አድማውን ማን እንደጠራውም አናውቅም። ግን፣ ደረጃውን ባልጠበቀ ሁኔታ የምሰጠው የህክምና አገልግሎት ትክክል አለመሆኑን ማሳየት የምችለው በስራ ማቆም አድማ ነው የሚል ግለሰብ፣ ያ የግለሰብ ውሳኔ ነው" ብለዋል ዶክተር ገመቺስ ማሞ። ከዚህ በኋላ በሚኖረውም ሂደት፣ የህክምና ባለሙያዎች የሚያስተሳስራቸው የጋራ ጥያቄዎች ቢኖራቸውም፣ የአካሄድ ልዩነት ሊኖር እንደሚችል፣ በማህበሩ በኩል ግን እስከ ሰላማዊ ሰልፍ ድረስ ሊሄድ የሚችል ትግል እንደሚያደርጉ ገልፀዋል። ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ዓለሙ በሰጡት ምላሽ፣ "ያላከበሩትን ባለሙያ፣ ህብረተሰቡን ተንከባክብ ማለት አይቻልም" ብለዋል።

አዘጋጅ:- ማውሮ

# ማንቸስተር ሲቲ በቀጣዩ የቻምፒየንስ ሊግ ውድድር በቅጣት ላይሳተፍ ይችላል



የአውሮጳ እግር ኳስ ማኀበር መርማሪዎች ማንቸስተር ዩናትድ የማኅበሩን የፋይናንስ ሕግ ጥሶ ከተገኘ፣ በቀጣዩ የውድድር ዘመን በቻምፒየንስ ሊጉ ውድድር እንዳይሳተፍ እገዳ እንዲጣልበት ፍላጎታቸውን ገልጸዋል:: አንድ የውስጥ ዐዋቂ ምንጭ እንደገለጹት ግን፣ የመጨረሻውን ውሳኔ የሚያስተላልፉት የእግር ኳስ ማኅበሩ ዋና መርማሪ፣ ኢቭ ለተርም፣ ናቸው:: በአሁኑ ወቅት የአውሮጳ እግር ኳስ ማኅበር የፋይናንስ ቁጥጥር ቦርድ ሊቀ-መንበር የሆኑት የቀድሞው የቤልጂየም ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ለተርምመ በአንድ ሳምንት ውስጥ ከውሳኔ ላይ ይደርሳሉ ተብሎ ይጠበቃል::

በእንዲህ ዓይነቱ ጉዳይ ውሳኔ የሚሰጠው በድምፅ ብልጫ ባለመሆኑ፣ የመጨረሻው ውሳኔ የለተርም ነው:: ይሁን እንጂ፣ ጥቂት የማይባሉ የሥራ ባልደረቦቻቸው ማንቸስተር በተጠረጠረበት ድርጊት ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ፣ ለአንድ የውድድር ዘመን በቻምፒየንስ ሊጉ ከመሳተፍ መታገድ እንዳለበት በቅርቡ ባካሄዱት ስብሰባ ላይ ተናግረዋል::

ለተርም እና የመርማሪ ቡድናቸው ባለፈው የፈረንጀች ዓመት የጀርመኑ ደር ስፒገል መጽሔት ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ያቀረባቸውን ዘገባዎች እየመረመሩ ነበር:: በመጽሔቱ ዘገባዎች መሠረት፣ ማንቸስተር ሲቲ የስፖንሰርሺፕ ስምምነትን ዋጋ በማጋነን፣ የአውሮጳ እግር ኳሽ ማኅበርን የፋይናንስ ሕግን ጥሷል:: ማነርቸስተር ሲቲ ቀደም ሲል በተመሳሳይ ድርጊት ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘቱ፣ በ2014 (እ.አ.አ.) 49 ሚሊዮን የእንግሊዝ ፓውንድ ተቀጥቶ ነበር::

የፕሪሚየር ሊጉ ሻምፒዮን በበኩሉ፣ ምንም ዓይነት ጥፋት አለመፈጸሙን አስተባብሏል:: የአውሮጳ እግር ኳሽ ማኅበር በምርመራው ዙሪያ አስተያየት ከመስጠት ቢቆጠብም፣ የኒው ዮርክ ታይምስ ጋዜጣ እንደሚለው፣ መርማሪዎቹ ክለቡ እንዲቀጣ እና የማኅበሩ የፋይናንስ ሕግ እንዲከበር ፈልገዋል::

የአውሮጳ እግር ኳስ ማኅበር ፍርድ ሸንጎ ለተርም ከሚያቀርቡት የውሳኔ ሐሳብ ጋር መስማማቱን ማሳወቅ ይኖርበታል:: ዳሩ ግን፣ ማንቸስተር ሲቲ ውሳኔውን ይግባኝ ማለት እና ጉዳዩን ወደስፖርት አሸማጋይ ፍርድ ቤት መውሰድ ስለሚችል እገዳው በቀጣዩ የውድድር ዘመን ተግባራዊ የመሆን ዕድሉ በጣም ጠባብ ነው::

ይሁን እንጂ፣ ውሳኔው የአውሮጳ ቻምፒየንስ ሊግ ዋንጫን ለመጀመሪያ ጊዜ ለማሸነፍ ብርቱ ፍላጎት ላለው ክለብ ተልቅ ራስ ምታት መሆኑ አይቀርም:: ከዚህ በተጨማሪም፣ የእንግሊዝ እግር ኳስ ማኅበር፣ ፕሪየር ሊጉ እና ፊፋ ክለቡን በወጣት ተጫዋቾች ዝውውር ዙሪያ ሕጎችን ጥሷል በሚል እያካሄዷቸው ያሉት ምርመራዎች ክለቡ የተጫዋቺችን ዝውውር በተመለከተ ከእገዳ ጋር ሊፋጠጥ ይችላል::


ማንቸስተር ሢቲ ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ባወጣው ጋዜጣዊ መግለጫ፣ "የማንቸስተር ሲቲ እግር ኳስ ክለብ ከአውሮጳ እግር ኳስ ማኅበር የክለቦች ፋይናንስ ቁጥጥር መርማሪ አካል ጋር በሙሉ ልብ እየተባበረ ነው:: የክለቡ የፋይናንስ መዛግብት ግልጽ እና የተሟሉ ናቸው:: ውንጀላው ምንም ዓይነት ሕጋዊ መሠረት የለውም:: ይህንንም የሚያስረዳ ማስረጃ ለቦርዱ መርማሪዎች ቡድን አቅርበናል" ብሏል::

የኳታር ባለሀብት ንብረት የሆነው ፈረንሳዩ ፓሪ ሳን-ዠርሜን በአሁኑ ወቅት ማንቸስተር ሲቲ ከተወነጀበት ድርጊት ጋር በሚመሳሰል መልኩ የገንዘብ ቅጣት ተጥሎበት ነበር:: ፓሪ ሳን-ዠርሜን የእግር ኳስ ማኅበሩን ሕግ የጣሰው ክለቡ ከኳታር ቱሪዝም ባለሥልጣን ጋር በነበረው የ167 ሚሊዮን የእንግሊዝ ፓውንድ የስፖንሰርሺፕ ስምምነት ኪሳራውን ለመሸፈን መዋሉ ሕገ-ወጥ ሆ በመገኘቱ ነው:: በእግር ኳስ ማባሩ ሕግ መሠረት፣ የአንድ ክለብ ኪሳራ በሁለት ተከታታይ ዓመታት ከ37 ሚሊዮን የእንግሊዝ ፓውንድ መብለጥ የለበትም::

ፓሪ ሳን-ዠርሜን ከዚህ ጋር በተያያዘ የገንዘብ ቅጣት የተጣለበት ሲሆን፣ ለአንድ የውድድር ዘ፣መን ለቻምፒየንስ ሊጉ 21 ተጫዋቾችን ብቻ እንዲያስመዘግብ ተፈቅዶለታል:: ከዚህ በተጨማሪም፣ የፈረንሳዩ ክለብ ኔይማርን በ222 ሚሊዮን ዩሮ ከባርሴሎና፣ እንዲሁም ኪሊያን ምባፔን በ180 ሚሊዮን ዩሮ ከሞናኮ ማዛወሩን ተከትሎ፣ የ2017/18 (እ.አ.አ.) የሒሳብ መዛግብቱ እየተመረመሩ ይገኛሉ::

## በቻምፒየንስ ሊጉ የፍጻሜ ጨዋታ

## ዳሚር ስኮሚና ቶተንሃም እና ሊቨርፑልን በመኻል ዳኝነት እንዲያጫውቱ ታጩ




ስሎቬኒያዊው ዳሚር ስኮሚና በቶተንሃም ሆትስፐር እና በሊቨርፑል ካከል የሚካሄደውን የቻምፒየንስ ሊግ የፍጻሜ ጨዋታ በመኻል ዳኝነት እንዲመሩ ተመርጠዋል:: የ42 ዓመቱ አርቢትር ማነረቸስተር ዩናይትድ ባለፈው መጋቢት ወር በፓሪ ሳን-ዠርሜን ላይ ባገኘው ድል በመጨረሻዋ ደቂቃ አወዛጋቢ የሆነ ፍጹም ቅጣት ምት ለእንግሊዙ ክለብ መስጠታቸው ይታወሳል:: የፓሪ ሳን-ዠርሜኑ ብራዚላዊ አጥቂ፣ ኔይማር፣ የዳኛውን ውሳኔ በማኅበራዊ ሚዲያ "አሳፋሪ" ነው ብሎ በመግለጹ፣ የሦስት ጨዋታዎች እገዳ ተጥሎበት ነበር::

ስኮሚና በማንቸስተር የናይትድ አያክስ አምስተርዳምን ያሸነፈበትን የ2017 (እ.አ.አ.) የአውሮጳ ሊግ የፍጻሜ ጨዋታን በመኻል ዳኝነት መርተዋል:: ከዚህ በተጨማሪም፣ ከአምስት ዓመታት በፊት በቼልሲ እና በአትሌቲኮ ማድሪድ መካከል የተደረገውን የአውሮጳ እግር ኳስ ማኅበር ሱፐር ካፕ ጨዋታን በአርቢትርነት አጫውተዋል::

ስኮሚና በ2013 (እ.አ.አ.) ቦሩሲያ ዶርትሙንድ እና ባየር ሙኒክ በተገናኙበት የአውሮጳ ቻምፒየንስ ሊግ የፍጻሜ ጨዋታ አራተኛው ዳኛ ሆነው አገልግለዋል:: ከዚህ በተጨማሪም፣ በዘንድሮ የውድድር ዘመን አራት የቻምፒየንስ ሊግ ጨዋታዎችን በመኸሻል ዳኝነት መርተዋል፤ ከእነኝህ ጨዋታዎች መካከልም፣ ሊቨርፑል የጣልያኑን ናፖሊ አንድ ለባዶ በማሸነፍ፣ ወደጥሎ ማለፉ ምድብ የገባበት አንዱ ነው::

ቅዳሜ፣ ሰኔ 1/2019 (እ.አ.አ.) በማድሪድ ከተማ ኤስታዲዮ ሜትሮፖሊታኖ በሚካሔደው የቻምፒየንስ ሊጉ የፍጻሜ ጨዋታ፣ የስኮሚና ረዳት ዳኞች የሀገራቸው ልጆች የሆኑት ዡሬ ፕራፕሮትኒክ እና ሮበርት ቩካን ናቸው:: አራተኛው ዳኛ ደግሞ፣ ስፔናዊው አንቶኒዮ ማቲው ላሆዝ ይሆናሉ::

ጨዋታውን በቪዲዮ እየተከታተሉ የሚዳኙት አርቢትር ኔዘርላንዳዊው ዳኒ ማኬሊ ናቸው:: የማኬሊ ረዳቶች ሆነው የሚያገለግሉት ደግሞ፣ የሀገራቸው ልጅ የሆኑት ፖል ቫን ቦኬል እና ጀርመናውያኑ ፌሊክስ ዝዌየር እና ማርክ ቦሽ ናቸው::

በተያያዘ ዜና፣ ግንቦት 29/2019 (እ.አ.አ.) በቼልሲ እና በአርሰናል መካከል ባኩ ከተማ የሚካሄደውን የአውሮጳ ሊግ የፍጻ ጨዋታን በመኻል ዳኝነት የሚመሩት ጣልያናዊው አርቢትር፣ ጂያንሉካ ሮቺ፣ ይሆናሉ::

# አጫጭር ዜናዎች

ባየር ሙኒክ የ23 ዓመቱን ጀርመናዊ የክንፍ ተጫዋች፣ ለሮይ ሳኔ፣ በቀጣዩ የዝውውር መስኮት ወደክሉ ማዛወር በሚቻልበት መንገድ ዙሪያ ከማንቸስተር ዩናይትድ ጋር ውይይት ማድረግ ጀምሯል::

***

በርሴሎና በቻምፒየንስ ሊጉ በሊቨርፑል የደረሰበት ሽንፈት የ28 ዓመቱን የአትሌቲኮ ማድሪድ አጥቂ፣ አንቷን ግሪዝማን፣ እንዲያስፈርመው አስገድዶታል::

***

የላ ሊጋው ፕሬዚዳንት፣ ዣቪዬር ቴባስ፣ ፈረንሳዊው አጥቂ ግሪዝማን አትሌቲኮ ማድሪድን ሲቅ ለክለቡ መክፈል የሚገባውን ክፍያ ለመፈጸም ቡድን ከተገኘ የላ ሊጋውን ክለብ ለመልቀቅ ዝግጁ እንደሆነ ወደም ሲል ማስታወቁን አረጋገጠዋል::

***

ሪያል ማድሪድ የ26 ዓመቱን ፈረንሳዊ አማካይ፣ ፖል ፖግባ፣ ለማስፈረም ላይ ታች እያለ ነው፤ ማንቸስተር ዩናይትድ በበኩሉ፣ ለዝውውሩ 150 ሚሊዮን የእንግሊዝ ፓውንድ ከተከፈለው ተጫዋቹን ለመልቀቅ ዝግጁ እንደሆነ አስታውቋል::

***

ሪያል ማድሪድ ለ28 ዓመቱ የቼልሲ ተጫዋች፣ ኤደን ሃዛርድ፣ ዝውውር 86 ሚሊዮን የእንግሊዝ ፓውንድ ለመክፈል ቢስማማም፣ ሰማያዊዎቹ ክፍያው 100 ሚሊዮን የእንግሊዝ ፓውንድ እንዲሆን እየጠየቁ ነው::

***

የ29 ዓመቱ የዌልስ ብሔራዊ ቡድን ተሰላፊው፣ ጋሬት ቤል፣ ወደቀድሞ ክለቡ ቶተንሃም ሆትስፐር እንዲመለስ የቀረበለትን ጥያቄ ሳይቀበለው ቀርቷል፤ ተጫዋቹ ከሪያል ማድሪድ ጋር ያለው በሳምን 600000 የእንግሊዝ ፓውንድ ደመወዝ የሚያስገኝለት ኮንትራት የሚያበቃው ከሦስት ዓመታት በኋላ በመሆኑ፣ ክለቡን ለመልቀቅ ፍላጎት አላሳየም::

***

የእንግሊዝ ብሔራዊ ቡድን አሠልጣኝ፣ ጋሬት ቤል፣ በቀጣዩ የኔሽንስ ሊግ ውድድር የ25 ዓመት የቡድኑ አምበል፣ ሃሪ ኬን፣ ፖርቱጋል ለሚካሄደው ጨዋታ በጥሩ አቋም ላይ እንደሚሆን ሪፖርት ከደረሳቸው በኋላ ተጫዋቹን እንደሚያሰልፉት ተናግረዋል::

***

ጁቬንቱስ፣ ማንቸስተር ዩናይትድ እና ማንቸስተር ሲቲ ዓይናቸውን የጣሉበት የ24 ዓመቱን ፖርቱጋላዊ የቀኝ ተመላላሽ፣ ዦአዎ ቻንሴሎ፣ የሚለቀው ክለቦቹ ለዝውውሩ 60 ሚሊዮን ዩሮ ያህል ከከፈሉ እና ተጫዋቹ የሴሪ አ ቡድኑን ለመልቀቅ ጥያቄ እስካቀረበ ድረስ ብቻ እንደሆነ አስታውቋል::

***

የማንቸስተር ዩናይትድ አሠልጣኝ፣ ኦሌ ጉናር ሶልከሻየር፣ ቡድናቸው በካርዲፍ ሲቲ የተሸነፈበትን ጨዋታ ተከትሎ ከክለቡ ተጫዋቾች ግማሾቹን እንደሚሸጧቸው ዝተዋል::

***

የ23 ዓመቱ ፈረንሳዊ አጥቂ፣ አንቶኒ ማርሻል፣ ከማንቸስተር ዩናይትድ የዳይሬክተሮች ቦርድ ምክትል ሊቀ-መንበር፣ ጆኤል ግሌዘር፣ ተወዳጅ ተጫዋቾች መካከል አንዱ በመሆኑ በቀጣዩ የዝውውር መስኮት ለሌላ ክለብ አይሸጥም::

***

ማንቸስተር ዩናይትድ የ30 ዓመቱ ቺሊያዊ አጥቂ፣ አሌክሲስ ሳንቼዝ፣ ቀጣዩን የውድድር ዘመን በውሰት ከኢንተር ሚላን ጋር እንዲያሳልፍ ለተጫዋቹ 12 ሚሊዮን የእንግሊዝ ፓውንድ ሊከፍል ይችላል::

***

ባርሴሎና የ26 ዓመቱን ብራዚላዊ አማካይ፣ ፊሊፐ ኩቲንሆ፣ በቀጣዩ የዝውውር መስኮት መሸጥ ቢፈልግም፣ ከ100 ሚሊዮን ዩሮ በታች በሆነ ክፍያ ተጫዋቹን መልቀቅ እንደማይፈልግ አስታውቋል::